ለጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ከቆየሁ በኋላ ፥ ጕዞ
ዬን ለመቀጠል የሚያስችለኝን ዕርዳታ እንደም
ታደርጉልኝ ተስፋ አደርጋለሁ ። 25 አሁን ግን
ለአማኞች የሚሰጥ የገንዘብ ዕርዳታ ይዤ ወደ
ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ ። 26 ምክንያቱም የመቄዶ
ንያና የአካይያ አማኞች በኢየሩሳሌም አማኞች
መካከል ላሉት ድኾች የገንዘብ ዕርዳታ ለመላክ
ስለወሰኑ ነው ። 27 ይህንንም ዕርዳታ በፈቃደኝ
ነት የለገሡት ግዴታቸው በመሆኑ ነው ፤ ምክን
ያቱም አረማውያን ከአይሁዳውያን ጋር የመን
ፈስ በረከት ተካፋዮች ከሆኑ ፥ አረማውያንም
በሥጋዊ በረከታቸው አይሁዳውያንን የመርዳት
ግዴታ አለባቸው ። 28 ስለዚህ ይህን የተሰበሰበ
ውን የገንዘብ ዕርዳታ ወደ ኢየሩሳሌም ወስጄ
የማስረከብ ሥራዬን ከፈጸምሁ በኋላ ፥ ወደ
እስፓን እሄዳለሁ ፤ እግረ መንገዴንም እናንተን
እጐበኛችኋለሁ ። 29 ወደ እናንተ በምመጣበት
ጊዜም የክርስቶስን በረከት በሙላት ይዤላችሁ
እንደምመጣ ዐውቃለሁ ።
30 ወንድሞቼ ሆይ! ስለ እኔ ወደ እግዚአብ
ሔር በመጸለይ በትግሌ እንድትረዱኝ ፥ በጌታ
ችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ፍቅር
እለምናችኋለሁ ። 31 የምትጸልዩልኝም በይሁዳ
ካሉት ከማያምኑ ሰዎች እጅ እንድድንና በኢየ
ሩሳሌም ያለኝ አገልግሎትም በአማኞች ዘንድ
ደስ የሚያሰኝ እንዲሆን ነው ። 32 ይህም ከሆነ
በኋላ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ወደ እና
ንተ በደስታ መጥቼ ከእናንተ ጋር ማረፍ እወዳ
ለሁ ። 33 ሰላምን የሚሰጥ እግዚአብሔር ከሁላች
ሁም ጋር ይሁን ፤ አሜን ።

## ምዕራፍ 16

### ሰላምታ

1 ፌቤ በክንክሪያ ከተማ ፥ ቤተ ክርስቲያንን
የምታገለግል ታማኝ እኅታችን መሆንዋን እንድ
ታውቁ እወዳለሁ ። 2 እርስዋ እኔንና ሌሎችንም
ብዙ ሰዎች የረዳች ስለሆነች ፥ የእግዚአብሔር
ሰዎች እንግዶችን መቀበል እንደሚገባቸው ዐይ
ነት በጌታ ስም ተቀብላችሁ በሚያስፈልጋት
ነገር ሁሉ እንድትረዱአት ዐደራ እላችኋለሁ ።
3 በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ተባባሪዎቼ ለሆ
ኑት ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤
4 እነርሱ በእኔ ምትክ ለመሞት እንኳ የተዘጋጁ
ነበሩ ፤ በዚህም ዘወትር አመሰግናቸዋለሁ ፤
እኔም ብቻ ሳልሆን የአረማውያን አብያተ ክርስ
ቲያናት ጭምር ያመሰግኑዋቸዋል ። 5 በእነርሱ
ቤት ለጸሎት ለሚሰበሰቡት ምእመናንም ሰላ
ምታ አቅርቡልኝ ።
በእስያ ክፍለ ሀገር በመጀመሪያ በክርስቶስ
ላመነውና ለምወደው ለኤጴኔቶስ ሰላምታ አቅ
ርቡልኝ ። 6 ለእናንተ ብዙ ለደከመችው ለማር
ያም ሰላምታ አቅርቡልኝ ። 7 ከእኔ ጋር ታስ
ረው ለነበሩና በሐዋርያትም መካከል ታዋቂ
ዎች ለነበሩት አይሁዳውያን ዘመዶቼ ለአንድሮ
ኒቆስና ለዩኒያስ3* ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ እነርሱ
በክርስቶስ በማመን እኔን ይቀድሙኛል ።
8 በጌታ ለምወደው ለአምፕልያቶስ ሰላምታ
አቅርቡልኝ ፤ 9 በክርስቶስ ሥራ ተባባሪያችን
ለሆነው ለዑርባኖስና ለምወደውም ለእስጣኩስ
ሰላምታ አቅርቡልኝ ። 10 በክርስቶስ መሆኑ
ተፈትኖ ለተመሰገነው ለአፔሊስ ሰላምታ አቅር
ቡልኝ ፤ ከአርስጦቡሎስ ቤተ ሰብ ለሆኑትም
ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ 11 ለአይሁዳዊ ዘመዴ
ለሄሮድዮን ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ ከናርሲሰስ
ቤተ ሰዎች በጌታ ላመኑት ሰላምታ አቅርቡ
ልኝ ።
12 በጌታ አገልግሎት ለሚደክሙት ለትሩፋ
ይናና ለትሩፎሳ ሰላምታ አቅርቡልኝ ። በጌታ
አገልግሎት እጅግ ለደከመችውና በክርስቶስ
ለምወዳት ለጼርሲስ ሰላምታ አቅርቡልኝ ።
13 ጌታን በማገልገል በጣም ለታወቀው ለሩፎስ
ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ እኔን እንደ ልጅዋ ትወ
ደኝ ለነበረችው ለእናቱም ሰላምታ አቅርቡ
ልኝ ። 14 ለአስንክሪቶስና ለፍሌጎን ፥ ለሄርሜ
ስም ለፓትሮባስም ለሄርማስም ከእነርሱም ጋር
ላሉ አማኞች ወንድሞች ሰላምታ አቅርቡልኝ ።
15 ለፊሎሎጎስ ፥ ለዩልያ ፥ ለኔርያና ለእኅቱም
ሰላምታ አቅርቡልኝ ፤ እንዲሁም ለኦሉምፓስና
ከእርሱም ጋር ላሉ አማኞች ሁሉ ሰላምታ አቅ
ርቡልኝ ። 16 በወንድማማችነት ስሜት በመሳ
ሳም ሰላምታ ተሰጣጡ ። የክርስቶስ አብያተ
ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ።

### የመጨረሻ ምክር

17 ወንድሞቼ ሆይ! በመካከላችሁ መለያየ
ትን ከሚፈጥሩትና በእምነታችሁ እንዳትጠነ
ክሩ ከሚያደርጉት ሰዎች ተጠንቀቁ ፤ የተቀበላ
ችሁትን ትምህርት የሚቃወሙም ስለሆኑ ከእነ
ርሱ ራቁ ። 18 እንደእነዚህ ዐይነት ሰዎች የራሳ
ቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ናቸው እንጂ
ጌታችንን ክርስቶስን የሚያገለግሉ አይደሉም ፤
ጥሩ ቃል መስሎ በሚታይና በሚያቈላምጥ ንግ
ግር ተንኰል የሌለባቸውን የዋሆች ያታልላሉ ።
19 ለምሥራቹ ቃል ታዛዦች መሆናችሁ
በሰው ሁሉ ዘንድ ስለታወቀ ደስ ብሎኛል ፤
ነገር ግን ለመልካም ነገር ጥበበኞች ፥ ለክፉ
ነገር ግን የዋሆች እንድትሆኑ እፈልጋለሁ ።
20 ይህን ብታደርጉ ሰላምን የሚሰጥ እግዚአብ
ሔር ሰይጣንን በእግራችሁ ሥር ይቀጠቅጥ
ላችኋል ።

3* 16፡7 ዩኒያስ ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “ዩሊያ” ይላሉ ።
15፡25-26 ፦ 1ቆሮ. 16፡1-4 ። 15፡27 ፦ 1ቆሮ. 9፡11 ። 16፡3 ፦ ሐ.ሥ. 18፡2 ። 16፡13 ፦ ማር. 15፡21 ።



የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ
ጋር ይሁን ።
21 የሥራ ተባባሪዬ ጢሞቴዎስ ሰላምታ ያቀ
ርብላችኋል ፤ እንዲሁም አይሁዳውያን ዘመዶቻ
ችን የሆኑት ሉቂዮስና ኢያሶን ሶሲጳጥሮስም
ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ።
22 ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔም ጠርጥዮስ
በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ ።
23 እኔን አሁን የሚያስተናግደኝና እዚህ
ያሉት ምእመናን በቤቱ ለጸሎት እንዲሰበሰቡ
የሚያደርገው ጋይዮስ ሰላምታ ያቀርብላችኋል ፤
የከተማይቱ በጅሮንድ የሆነው ኤራስጦስ ፥ ወን
ድማችንም ቋርጦስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ።
[24 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ
ጋር ይሁን ፤ አሜን ።]

### የምስጋና ጸሎት

25 እንግዲህ ለእግዚአብሔር ምስጋና
ይሁን! እኔ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የማበሥረው
የምሥራች ቃልና ለብዙ ዘመናት ተደብቆ
አሁን በተገለጠው እውነት ፥ እግዚአብሔር
በእምነታችሁ ጸንታችሁ እንድትቆሙ ሊያደር
ጋችሁ ይችላል ። 26 ይህም እውነት አሁን በነ
ቢያት መጻሕፍት አማካይነት በግልጥ ታይቶ
አል ፤ ሁሉም አምነው እንዲታዘዙ በሕያው
አምላክ ትእዛዝ ሕዝቦች ሁሉ እንዲያውቁት
ተደርጎአል ።
27 እርሱ ብቻ ጥበበኛ ለሆነው ለአንድ አም
ላክ ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለዘላለም ምስጋና
ይሁን! አሜን ።

# የመጀመሪያው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት

# ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

## መግቢያ

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈላቸው የመጀመሪያው መልእክት የተጻፈው ጳውሎስ በቆሮን
ቶስ ባቋቋመው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስትናን ሕይወትና እምነት በሚመለከት ተነሥቶ
ስለነበረው ችግር መፍትሔ ለማስገኘት በማሰብ ነው ። በዚያን ጊዜ ቆሮንቶስ ዓለም አቀፋዊ የሆ
ነች የግሪክ ከተማ ከመሆንዋም በላይ አካይያ ለተባለ የሮም ግዛት ዋና ከተማ ነበረች ። ይህች
ከተማ ታላቅ በሆነ የንግድ እንቅስቃሴ ፥ በደረጀ ባሕል ፥ እጅግ በመስፋፋት ላይ በነበረ ስድነት
ወይም የሞራል ውድቀትና በሃይማኖቶች ብዛት የታወቀች ነበረች ።
ሐዋርያው በተለይ ያተኰረው በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ስለነበረው መከፋፈልና የስድነት
ሕይወት ፥ እንዲሁም ስለ ፍትወተ ሥጋና ስለ ጋብቻ ፥ ስለ ኅሊና ጥያቄዎች ፥ ስለ ቤተ ክርስቲ
ያን ሥርዓት ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና ስለ ትንሣኤ ነበር ፤ የምሥራቹ ቃል ስለነዚህ
ጥያቄዎች የሚናገረውን በጥንቃቄ ያቀርባል ።
ፍቅር እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሰጣቸው ስጦታዎች የበለጠ መሆኑን የሚገልጠው ምዕራፍ
ዐሥራ ሦስት ፥ ከዚህ መጽሐፍ እጅግ ታዋቂ የሆነው ክፍል እንደሆነ ይገመታል ።

## ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ
ሐዋርያ ለመሆን ከተጠራው ከጳውሎስና ከወን
ድማችንም ከሶስቴንስ ፤
2 ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ባላቸው ኅብረት
የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢ
የሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት
ክርስቲያኖች ጋር ፥ የእግዚአብሔር ቅዱስ
ሕዝብ ለመሆን ለተጠሩት ለቆሮንቶስ ክርስቲያ
ኖች ሁሉ ፦
3 ከአባታችን ከእግዚአብሔርና ከጌታ ከኢየ
ሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ።

### ምስጋና ለእግዚአብሔር

4 በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እግዚአብ
ሔር ጸጋውን ስለ ሰጣችሁ በእናንተ ምክንያት
ሁል ጊዜ አመሰግነዋለሁ ። 5 በሁሉ ነገር በቃ
ልም ሆነ በዕውቀት ፥ በክርስቶስ በልጽ
ጋችኋል ። 6 ስለ ክርስቶስ የነገርናችሁ ምስክር
ነት በእናንተ ዘንድ ጸንቶአል ። 7 ስለዚህ የጌታ
ችንና የኢየሱስ ክርስቶስን መገለጥ በመጠባበቅ

16፡21 ፦ ሐ.ሥ. 16፡1 ። 16፡23 ፦ ሐ.ሥ. 19፡29 ፥ 1ቆሮ. 1፡14 ፥ 2ጢሞ. 4፡20 ።
1፡2 ፦ ሐ.ሥ. 18፡1 ።

ስትኖሩ ምንም ዐይነት መንፈሳዊ ስጦታ አይጐ
ድልባችሁም፤ 8 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚ
መለስበት ቀን ያለነቀፋ ሆናችሁ እንድትገኙ፣
እርሱ እስከ መጨረሻ ጸንታችሁ እንድትኖሩ
ያደርጋችኋል። 9 ከልጁ ከጌታችን ከኢየሱስ ክር
ስቶስ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ የጠራችሁ
እግዚአብሔር የታመነ ነው።

### በክርስቲያኖች መካከል መለያየት አይኑር

10 ወንድሞቼ ሆይ! “መለያየት በመካከላ
ችሁ አይኑር፤ ሁላችሁም ተስማምታችሁ በአ
ንድ አሳብና በአንድ ዓላማ ጸንታችሁ ኑሩ”
ብዬ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለም
ናችኋለሁ። 11 ወንድሞቼ ሆይ! በመካከላችሁ
ክርክርና መለያየት መኖሩን ከቀሎኤ ቤተሰብ
ሰምቻለሁ። 12 ይኸውም እናንተ እያንዳንዳችሁ
“እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ እኔ የአጵሎስ ነኝ፤ እኔ
የጴጥሮስ ነኝ፤ እኔ የክርስቶስ ነኝ” ትላላችሁ።
13 ታዲያ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ
ስለ እናንተ ተሰቅሎአልን? ወይስ የተጠመቃች
ሁት በጳውሎስ ስም ነውን? 14 እኔ ከቀርስጶስና
ከጋይዮስ በቀር ከእናንተ ማንንም ስላላጠመቅሁ
እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። 15 ስለዚህ “በጳ
ውሎስ ስም ተጠምቃችኋል” ብሎ መናገር
የሚችል የለም። (16 እርግጥ ነው፣ የእስጢፋኖ
ስንም ቤተሰብ አጥምቄአለሁ፤ ከነዚህ ሌላ እኔ
ያጠመቅሁት ሰው መኖሩን አላስታውስም፤)
17 ምክንያቱም ክርስቶስ የላከኝ የምሥራቹን
ቃል እንዳበሥር ነው እንጂ እንዳጠምቅ አይደ
ለም፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞቱ
ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር፣ የምሥራቹን ቃል የማ
በሥረው ከሰው ጥበብ በተገኘ ንግግር አይደ
ለም።

### ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጥበብና ኀይል ነው

18 “ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ”
የሚለው ቃል ለሚጠፉት ሰዎች እንደ ሞኝነት
ይቈጠራል፤ ለምንድን ለእኛ ግን የእግዚአብ
ሔር ኀይል ነው። 19 ምክንያቱም፣
“የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፤
የሊቃውንትንም ዕውቀት
አስወግዳለሁ” ተብሎ ተጽፎአል።
20 ታዲያ ጥበበኛ የት አለ? ሊቅስ የት አለ?
ተመራማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚህን
ዓለም ጥበብ ሞኝነት አድርጎት የለምን?
21 የዚህ ዓለም ሰዎች በገዛ ጥበባቸው እግዚ
አብሔርን ማወቅ እንዳይችሉ፣ እግዚአብሔር
በጥበቡ ዘጋባቸው፤ ነገር ግን ለዓለም እንደ
ሞኝነት በሚቈጠረው የወንጌል መልእክታችን
የሚያምኑትን ለማዳን የእግዚአብሔር ፈቃድ
ሆኖአል። 22 መቼም አይሁዳውያን ተአምር
ማየትን ይፈልጋሉ፤ ግሪካውያን ደግሞ ጥበብን
ይሻሉ። 23 እኛ ግን ክርስቶስ ስለ እኛ መሰቀ
ሉን እንመሰክራለን፤ ይህም ምስክርነት ለአይሁ
ዳውያን መሰናከያ ነው፤ ለግሪካውያንም ሞኝ
ነት ነው። 24 ለተጠሩት ግን ለአይሁዳውያንም
ሆነ ለግሪካውያን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ኀይ
ልና የእግዚአብሔር ጥበብ ነው። 25 ምክንያ
ቱም የእግዚአብሔር ሞኝነት ነው ተብሎ የሚ
ታሰበው ነገር ከሰው ጥበብ ይበልጣል፤ የእግዚ
አብሔር ደካማነት ነው ተብሎ የሚታሰበውም
ነገር ከሰው ኀይል ይበልጣል።
26 ወንድሞቼ ሆይ! እግዚአብሔር በጠራ
ችሁ ጊዜ ምን ዐይነት ሰዎች እንደነበራችሁ
አስታውሱ፤ እንደ ሰው አስተሳሰብ ከእናንተ
መካከል ብዙዎች ጥበበኞች ወይም ብርቱዎች
ወይም ታላላቅ ሰዎች አልነበሩም። 27 እግዚአ
ብሔር ጥበበኞችን ለማሳፈር በዓለም እንደ
ሞኞች የሚቈጠሩትን ሰዎች መረጠ፤ ብርቱዎ
ችንም ለማሳፈር በዓለም እንደ ደካሞች የሚቈ
ጠሩትን መረጠ፤ 28 በዓለም ሰዎች ዘንድ ክቡር
ሆኖ የሚታየውን ነገር ለማጥፋት፣ በዓለም የተ
ዋረደና የተናቀ ከንቱም መስሎ የሚታየውን
ነገር መረጠ። 29 ይህንንም ያደረገው ማንም
ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ ነው።
30 እናንተን ግን እግዚአብሔር ከኢየሱስ ክርስ
ቶስ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ አደረገ፤ ስለዚህ
እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ጥበባችን፣
ጽድቃችን፣ ቅድስናችን፣ ቤዛችን እንዲሆን
አደረገው። 31 እንግዲህ መጽሐፍ እንደሚለው
“የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ።”

## ምዕራፍ 2

### የክርስቶስ ስቅለት

1 ወንድሞቼ ሆይ! እኔ ወደ እናንተ በመ
ጣሁ ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ምስጢር1* አስተ
ማርሁአችሁ እንጂ የንግግርን ችሎታና የፍልስ
ፍናን ጥበብ አላሳየሁም። 2 ምክንያቱም ከእና
ንተ ጋር በነበርሁበት ጊዜ ከኢየሱስ ክርስቶስ
በቀር በተለይም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ከመ
ሞቱ ጉዳይ ሌላ ምንም ነገር ላለማወቅ ወስኜ
ነበር። 3 ስለዚህ ከእናንተ ጋር በነበርሁበት ጊዜ
ደካማ ሆኜ በፍርሃትና በብዙ መንቀጥቀጥ ላይ
ነበርሁ። 4 የተናገርሁትም ሆነ ያስተማርሁት

1* 2፥1 የእግዚአብሔርን ምስጢር ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “ለእግዚአብሔር ምስክርነት” ይላሉ።
1፥12 ፦ ሐ.ሥ. 18፥24 ። 1፥14 ፦ ሐ.ሥ. 18፥8፤ 19፥29፤ ሮም 16፥23 ። 1፥16 ፦ 1ቆር. 16፥15 ።
1፥19 ፦ ኢሳ. 29፥14 ። 1፥20 ፦ ኢዮብ 12፥17፤ ኢሳ. 19፥12፤ 33፥18፤ 44፥25 ። 1፥31 ፦ ኤር. 9፥24 ።
2፥3 ፦ ሐ.ሥ. 18፥9 ።



ቃል፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ኀይል የተደገፈ
ነበር እንጂ በሰው ጥበብና ፍልስፍና ላይ ተመ
ሥርቶ ሰውን የሚያባብል ቃል አልነበረም።
5 ይህንንም ያደረግሁት እምነታችሁ በሰው
ጥበብ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በእግዚአብሔር
ኀይል የተደገፈ እንዲሆን ነው።

### የእግዚአብሔር ጥበብ

6 ነገር ግን በመንፈሳዊ ሕይወት ለበሰሉት
በጥበብ ቃል እንናገራለን፤ የምንናገረው የዚህን
ዓለም ጥበብ ወይም መጨረሻቸው ጥፋት የሚ
ሆነውን የዚህን ዓለም ገዥዎች ጥበብ አይደ
ለም። 7 እኛ የምንናገረው ግን እግዚአብሔር
አስቀድሞ ከዘመናት በፊት ለክብራችን ያዘጋጀ
ውንና ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔርን
ምስጢር ጥበብ ነው። 8 ከዚህ ዓለም ገዦዎች
መካከል ይህን ጥበብ ያወቀ ማንም የለም፤ ዐው
ቀውት ቢሆንማ ኖሮ የክብርን ጌታ ሰቅለው
ባልገደሉትም ነበር። 9 ይሁን እንጂ መጽሐፍ፣
“የሰው ዐይን ያላየውን፣
የሰው ጆሮ ያልሰማውን፣
የሰው ልብ ያላሰበውን፣
እግዚአብሔር ለሚወዱት
አዘጋጅቶአል” ይላል።
10 ለእኛ ግን እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካይ
ነት ምስጢሩን ገልጦልናል፤ ምክንያቱም የእግ
ዚአብሔር መንፈስ ጥልቅ የሆነውን የእግዚአብ
ሔርን ዕቅድ እንኳ ሳይቀር ሁሉን ነገር ይመረ
ምራል። 11 ስለ ሰው የሆነ እንደሆነ፣ ከገዛ
ራሱ መንፈስ በቀር በእርሱ ያለውን አሳብ የሚ
ያውቅ ሌላ ማንም የለም፤ እንዲሁም ከእግዚአ
ብሔር መንፈስ በቀር የእግዚአብሔርን አሳብ
የሚያውቅ ማንም የለም። 12 እኛ የዚህን ዓለም
መንፈስ አልተቀበልንም፤ እኛ የተቀበልነው
እግዚአብሔር የሰጠንን፣ ሁሉን ለማወቅ የሚያ
ስችለንን የእግዚአብሔርን መንፈስ ነው።
13 ስለዚህ እኛ መንፈሳዊውን ነገር ለመንፈሳ
ውያን ሰዎች የምናስተምረው ከሰው በሚገኘው
ጥበብ ሳይሆን ከእግዚአብሔር መንፈስ በሚገ
ኘው ጥበብ ነው። 14 የእግዚአብሔር መንፈስ
የሌለው ሥጋዊ ሰው ግን ከእግዚአብሔር መን
ፈስ የሚሰጠውን ስጦታ መቀበል አይችልም፤
ምክንያቱም የስጦታው ታላቅነት የሚመረመ
ረው በእግዚአብሔር መንፈስ አማካይነት ስለ
ሆነ ሊያስተውለው አይችልም፤ እንዲያውም
ለእርሱ ሞኝነት መስሎ ይታየዋል። 15 የእግዚአ
ብሔር መንፈስ ያለው ግን ሁሉን ነገር መመር
መር ይችላል፤ እርሱ ራሱ ግን በማንም አይመ
ረመርም። 16 ይህም፣
“የእግዚአብሔርን ልብ ማን ሊያውቀው
ይችላል?
ሊመክረውስ የሚችል ማን ነው?”
ተብሎ እንደ ተጻፈው ነው።
እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።

## ምዕራፍ 3

### የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሥራ

1 ወንድሞቼ ሆይ! እንደ እውነቱ ከሆነ፣
እኔ ያስተማርሁአችሁ ሥጋውያንና በክርስቶስ
ገና ያልጠነከራችሁ ሕፃናት እንደመሆናችሁ
መጠን ነው እንጂ መንፈሳውያን እንደመሆና
ችሁ መጠን ላስተምራችሁ አልቻልሁም።
2 ጠንካራ ምግብ መብላት የማትችሉ ስለሆና
ችሁ እኔ የመገብኋችሁ ወተት ነው እንጂ ጠን
ካራ ምግብ አይደለም፤ አሁንም ቢሆን ጠንካራ
ምግብ መመገብ ገና የማትችሉ ናችሁ። 3 ምክ
ንያቱም አሁንም ገና ሥጋውያን ናችሁ፤ እርስ
በርሳችሁ ስለምትቀናኑና ስለምትከራከሩ ሥጋ
ውያን መሆናችሁ አይደለምን? የእግዚአብሔር
ሰዎች መሆናችሁ ቀርቶ የዓለም ሰዎች መሆና
ችሁ አይደለምን? 4 አንዱ “እኔ የጳውሎስ
ነኝ” ሌላው ደግሞ “እኔ የአጵሎስ ነኝ”
ሲል፣ የእግዚአብሔር ሰዎች መሆናችሁ ቀርቶ
የዓለም ሰዎች መሆናችሁ አይደለምን?
5 ለመሆኑ አጵሎስ ምንድን ነው? ጳውሎስስ
ምንድን ነው? እነርሱ እኮ እናንተ እንድታምኑ
ያደረጉአችሁ አገልጋዮች ናቸው፤ እያንዳንዳ
ቸው የሚያገለግሉትም፣ ጌታ ለያንዳንዳቸው
በመደበላቸው ሥራ ነው፤ 6 እኔ ተከልሁ፤ አጵ
ሎስ ውሃ አጠጣ፤ ያሳደገው ግን እግዚአብሔር
ነው። 7 ስለዚህ ለሥራው ዋና የሆነው ተክሉን
ያሳደገው እግዚአብሔር ነው እንጂ የተከለም
ሆነ ውሃ ያጠጣ ምንም አይደለም። 8 የተከለም
ሆነ ውሃ ያጠጣ እኩል ናቸው፤ እያንዳንዱም
እንደ ሥራው መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበ
ላል። 9 ምክንያቱም እኛ ከእግዚአብሔር ጋር
አብረን የምንሠራ ነን፤ እናንተም የእግዚአብ
ሔር እርሻና የእግዚአብሔር ሕንጻ ናችሁ።
10 እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ መጠን እንደ
ብልህ ግንበኛ መሠረትን ጣልሁ፤ ሌላውም እኔ
በጣልሁት መሠረት ላይ ይገነባል፤ ነገር ግን
እያንዳንዱ እንዴት እንደሚገነባ መጠንቀቅ አለ
በት። 11 ምክንያቱም አንድ ጊዜ ከተመሠረተው
መሠረት በቀር ማንም ሌላ መሠረት መጣል
አይችልም፤ ይህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ
ነው። 12 በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ወይም
በብር በከበረ ድንጋይ ወይም በእንጨት፣ በሣር
ወይም በገለባ የሚገነባ ቢኖር፣ 13 እያንዳንዱ

2፥9 ፦ ኢሳ. 64፥4 ። 2፥16 ፦ ኢሳ. 40፥13 ። 3፥2 ፦ ዕብ. 5፥12-13 ። 3፥4 ፦ 1ቆር. 1፥12 ።
3፥6 ፦ ሐ.ሥ. 18፥4-11 ፡24-28 ።

በምን እንደሠራ የሚገለጥበት የፍርድ ቀን ይመ
ጣል፤ በዚያን ቀን የእያንዳንዱ ሰው ሥራ
በምን እንደተሠራ በእሳት ተፈትኖ ይገለጣል።
14 የግንበኛው ሥራ በእሳት ሳይደመሰስ ጸንቶ
ከቆመ፥ ግንበኛው ሽልማት ያገኛል።
15 ሥራው በእሳት ተቃጥሎ የተደመሰሰበት ግን
በኛ ግን ሽልማት ይቀርበታል፤ ይሁን እንጂ
እርሱ ራሱ፥ በእሳት ውስጥ አልፎ ሳይቃጠል
እንደሚቀር ሰው ይድናል።
16 የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆናችሁ
ንና የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ መኖ
ሩን ታውቁ የለምን? 17 እንግዲህ ሰው የእግዚአ
ብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ፥ እግዚአብ
ሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ ምክንያቱም የእግዚ
አብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነው፤ ይህም ቤተ
መቅደስ እናንተ ናችሁ።
18 ማንም ራሱን አያታልል፤ በዚህ ዓለም
የጥበብ ደረጃ ጥበበኛ መስሎ የሚታይ ቢኖር፥
የእግዚአብሔርን እውነተኛ ጥበብ እንዲያገኝ
ራሱን እንደ ሞኝ ይቍጠር። 19 ምክንያቱም
የዚህ ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት
ነው፤ ይህም፥

"እግዚአብሔር ጥበበኞችን
በተንኰላቸው ያጠምዳቸዋል"

እንደተባለው ነው። 20 እንዲሁም፥

"እግዚአብሔር የጥበበኞች አሳብ
ከንቱ መሆኑን ያውቃል" የሚል
ተጽፎአል።

21 ስለዚህ ሁሉ ነገር የእናንተ ስለሆነ ማንም
በሰው አይመካ። 22 ጳውሎስም ቢሆን፥ አጵሎ
ስም ቢሆን፥ ጴጥሮስም ቢሆን፥ ዓለምም ቢሆን፥
ሕይወትም ቢሆን፥ ሞትም ቢሆን፥ አሁን ያለ
ውም ቢሆን፥ በኋላ የሚመጣውም ቢሆን ሁሉም
የእናንተ ነው። 23 እናንተ ግን የክርስቶስ ናችሁ፤
ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።

## ምዕራፍ 4

### የክርስቶስ አገልጋዮች

1 እንግዲህ ሰው ሁሉ እኛን፥ የክርስቶስ አገ
ልጋዮች እንደሆንን፥ የእግዚአብሔርን ምስጢር
የመግለጥ ኀላፊነት የተሰጠንም ባለ ዐደራዎች
እንደሆንን አድርጎ ሊቈጥረን ይገባል። 2 ባለ ዐደ
ራዎችም ታማኞች ሆነው መገኘት አለባቸው።
3 ስለ እኔ የሆነ እንደሆን እናንተም ብትፈርዱ
ብኝ ወይም ሌላ ሰው ቢፈርድብኝ ምንም ግድ
የለኝም፤ በእውነቱ እኔ በራሴ ላይ እንኳ መፍ
ረድ አልችልም። 4 እኔ እንደማውቀው ከሆነ
ኅሊናዬ አይወቅሰኝም፤ ይህም እኔ ንጹሕ መሆ
ኔን አያስረዳም፤ ነገር ግን በእኔ ላይ የሚፈርድ
ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው። 5 ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ
ለፍርድ ከመምጣቱ በፊት በማንም ላይ አትፍ
ረዱ፤ እርሱ በሚመጣበት ጊዜ በጨለማ የተሰወ
ረውን ምስጢር ወደ ብርሃን ያወጣዋል፤ ሰዎች
በልባቸው የደበቁትንም አሳብ ይገልጠዋል፤ በዚ
ያን ጊዜ እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ተገቢውን
ምስጋና ያገኛል።
6 ወንድሞቼ ሆይ! እናንተን ለመጥቀም ብዬ
በዚህ ጉዳይ እኔንና አጵሎስን እንደ ምሳሌ አድ
ርጌ ተናገርሁ፤ ይህንንም ያደረግሁት "የተደነገ
ገውን አትጣስ" የሚለውን ምክር ከእኛ እንድት
ማሩ ብዬ ነው፤ ስለዚህ በአንድ ሰው መመካት፥
ሌላውን ሰው ግን መናቅ አይገባችሁም። 7 አንተ
ከሌሎች በምን ትበልጣለህ? ሁሉን ነገር የተቀበ
ልኸው ከሌላ ነው፤ የራስህ የሆነ ምንም ነገር
የለም፤ ታዲያ ሁሉን ነገር የተቀበልኸው ከሌላ
ከሆነ እንዳልተቀበለ ሰው ስለምን ትመካለህ?
8 አሁንማ የሚያስፈልጋችሁን ነገር ሁሉ
አግኝታችኋል! አሁንማ ሀብታሞች ሆናችኋል!
ከእኛም ተለይታችሁ ነግሣችኋል! በእርግጥ
ብትነግሡማ ኖሮ፥ እኛም ከእናንተ ጋር አብ
ረን ስለምንነግሥ መንገሣችሁ መልካም በሆነ
ነበር። 9 ምክንያቱም እግዚአብሔር እኛን ሐዋ
ርያቱን፥ ሞት ተፈርዶባቸው ወደሚገደሉበት
ቦታ ከሚወሰዱት ሰዎች መካከል የመጨረሻ
ዎቹ ያደረገን ይመስለኛል፤ ከዚህም የተነሣ
በዓለም ሁሉ፥ በመላእክትም ሆነ በሰዎች ፊት
እንደ መጫወቻና እንደ መሳቂያ ሆነን እንታያ
ለን፤ 10 እኛ ስለ ክርስቶስ ብለን ሞኞች ሆነ
ናል፤ እናንተ ግን በክርስቶስ ጥበበኞች
ሆናችኋል፤ እንዲሁም እናንተ ብርቱዎች
ሆናችኋል፤ እናንተ የተከበራችሁ ሆናችኋል፤
እኛ ግን የተዋረድን ሆነናል። 11 አሁንም
ቢሆን እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፤ እንጠ
ማለን፤ እንራቆታለን፤ እንደበደባለን፤ መጠለያ
በማጣት እንንከራተታለን። 12 በገዛ እጃችን እየ
ሠራን እንደክማለን፤ ሲረግሙን እንመርቃለን፤
ሲያሳድዱን እንታገሣለን፤ 13 ሲሰድቡንና ስማ
ችንን ሲያጠፉ በጥሩ ቃል እንመልስላቸዋለን፤
እስከ አሁን ድረስ የዚህ ዓለም ውዳቂና የምድር
ጥራጊ ጉድፍ ሆነናል።
14 እኔ ይህን የምጽፍላችሁ እንደ ተወደዳ
ችሁ ልጆቼ አድርጌ ልመክራችሁ አስቤ ነው
እንጂ ላሳፍራችሁ ብዬ አይደለም። 15 ምንም
እንኳ በሺ የሚቈጠሩ ሞግዚቶች በክርስቶስ
ቢኖሩአችሁም፥ ብዙ አባቶች የሉአችሁም፤
መልካሙን ዜና በማብሠር በክርስቶስ ኢየሱስ
የወለድሁአችሁ እኔ ብቻ ነኝ። 16 ስለዚህ የእ
ኔን ምሳሌነት እንድትከተሉ እለምናችሁአ
ለሁ። 17 በዚህ ምክንያት የተወደደውንና የታ
መነውን፥ በጌታ ልጄ የሆነውን ጢሞቴዎስን





ልኬላችኋለሁ፤ እኔ በየስፍራው በአብያተ ክር
ስቲያናት ሁሉ የማስተምረውንና በክርስቶስ
ያገኘሁትን የአዲስ ሕይወት መመሪያ እርሱ
ያሳስባችኋል።
18 ነገር ግን ከእናንተ አንዳንዶቹ እኔ እናን
ተን ለመጐብኘት የማልመጣ መስሎአቸው በት
ዕቢት ተሞልተዋል። 19 ይሁን እንጂ የጌታ
ፈቃድ ቢሆን በቅርብ ጊዜ ወደ እናንተ እመጣ
ለሁ፤ በዚያን ጊዜ የእነዚህን ትዕቢተኞች ንግግ
ራቸውን ብቻ ሳይሆን ኀይላቸውን ማወቅ እፈ
ልጋለሁ። 20 ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንግ
ሥት የወሬ ጉዳይ ሳይሆን የእግዚአብሔር
ኀይል ነው። 21 የምትፈልጉት ምንድን ነው?
የመቅጫ ዱላ ይዤ ወደ እናንተ እንድመጣ
ትፈልጋላችሁን? ወይስ በፍቅርና በደግነት መን
ፈስ እንድመጣ ትፈልጋላችሁ?

## ምዕራፍ 5

### በምእመናን መካከል የተደረገ አሳፋሪ ነገር

1 በመካከላችሁ አሳፋሪ የዝሙት ሥራ
መኖሩ ይወራል፤ እንዲህ ዐይነቱ የዝሙት
ሥራ በአረማውያን ዘንድ እንኳ የማይደረግ
ነው፤ ይኸውም የእንጀራ እናቱን እንደ ሚስት
አድርጎ የሚኖር አለ ተብሎአል። 2 ታዲያ እን
ዲህ ያለ አሳፋሪ ነገር በመካከላችሁ እያለ ለምን
ትታበያላችሁ? ይልቅስ በዚህ ነገር ማዘንና እን
ዲህ ዐይነቱን ሥራ የፈጸመውን ሰው ከመካከላ
ችሁ ማስወገድ በተገባችሁ ነበር። 3 ምንም
እንኳ እኔ በሥጋ አብሬአችሁ ባልሆንም በመን
ፈስ ከእናንተ ጋር ነኝ፤ ልክ አብሬአችሁ እንዳ
ለሁ ሆኜ እንዲህ ዐይነቱን የርኵሰት ሥራ በፈጸ
መው ሰው ላይ፥ በጌታ በኢየሱስ ስም ፈርጄበ
ታለሁ። 4 በምትሰበሰቡበት ጊዜ እኔም በጌታ
ችን በኢየሱስ ኀይል በመካከላችሁ በመንፈስ
ስለምገኝ፥ 5 በኃጢአት የተሞላው የዚህ ሰው
ሥጋ ይፈርስ ዘንድ ለሰይጣን አሳልፋችሁ ልትሰ
ጡት ይገባል። ይህንንም የምታደርጉት ጌታ
ለፍርድ በሚመጣበት ቀን የዚህ ሰው ነፍስ እን
ድትድን ነው።
6 እንግዲህ የምትታበዩት በከንቱ ነው፤
ትንሽ እርሾ ሊጡን ሁሉ እንደሚያቦካው
ታውቁ የለምን? 7 አሁን እንደሆናችሁት ሁሉ
እርሾ እንደሌለበት እንደ አዲስ ሊጥ እንድት
ሆኑ፥ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ፤ ምክንያቱም
የፋሲካችን በግ የሆነው ክርስቶስ ስለ እኛ ተሠ
ውቶአል፤ 8 ስለዚህ ዐመፅና ክፋት በሞላበት
በአሮጌ እርሾ ሳይሆን፥ እርሾ በሌለበት ቅንነ
ትና እውነት በሞላበት ቂጣ በዓላችንን እናክ
ብር።
9 ከዚህ በፊት በጻፍሁላችሁ መልእክት ከአ
መንዝራዎች ጋር አትተባበሩ ብያችሁ ነበር።
10 ይህንንም ስል ከዚህ ዓለም አመንዝራዎች
ወይም ከስግብግብ ግለሰቦች ወይም ከሌቦች
ወይም ከጣዖት አምላኪዎች ጋር አትተባበሩ
ማለቴ አይደለም፤ እንዲህማ ከሆነ ከዓለም
መውጣት ያስፈልጋችሁ ነበር ማለት ነው።
11 እኔ ግን የጻፍሁላችሁ ክርስቲያኖች ተብለው
ከሚያመነዝሩ ወይም ከሚስገበገቡ ወይም
ጣዖት ከሚያመልኩ ወይም የሰው ስም ከሚያ
ጠፉ ወይም ከሚሰክሩ ወይም ከሚሰርቁ ጋር
አትተባበሩ ብዬ ነው። እንደእነዚህ ካሉት
ሰዎች ጋር መብል አብራችሁ አትብሉ።
12 ከክርስቲያናዊ ማኅበር ውጪ ባሉት
ሰዎች ላይ መፍረድ የእኔ ጉዳይ አይደለም፤
በክርስቲያናዊ ማኅበር ውስጥ ስላሉት ሰዎች
ጉዳይ እናንተስ መፍረድ ትችሉ የለምን?
13 በውጪ ስላሉት ሰዎች ጉዳይ የሚፈርድ እግ
ዚአብሔር ነው፤ እንግዲህ መጽሐፍ እንደሚል
"ክፉውን ሰው ከመካከላችሁ አስወግዱ።"

## ምዕራፍ 6

### በክርስቲያኖች መካከል ያለውን አለመግባባት እንዴት ማስወገድ እንደሚገባ

1 ከእናንተ አንዱ፥ ክርስቲያን ከሆነው ወን
ድሙ ጋር ቢጣላ፤ ጉዳዩን የእግዚአብሔር
ሰዎች በፍርድ እንዲያዩለት በማድረግ ፈንታ
ለክስ ወደ አረማውያን የፍርድ ሸንጎ ለመሄድ
እንዴት ይደፍራል? 2 የእግዚአብሔር ሰዎች በዓ
ለም ላይ እንደሚፈርዱ አታውቁምን? ታዲያ
በዓለም ላይ የምትፈርዱ ሲሆን በዚህ በትንሽ
ነገር ላይ መፍረድ እንዴት አቃታችሁ? 3 በመላ
እክት ላይ እንኳ እንደምንፈርድ አታውቁምን?
ታዲያ በዚህ ዓለም ነገሮች ላይ በይበልጥ መፍ
ረድ እንዴት አንችልም? 4 እንግዲህ እርስ በርሳ
ችሁ ብትጣሉ ከክርስቲያናዊ ማኅበር ውጪ በሆ
ኑትና በተናቁት ሰዎች ፊት ቀርባችሁ እንዴት
ትካሰሳላችሁ? 5 ይህን የምለው እንድታፍሩ ብዬ
ነው፤ እረ ለመሆኑ፥ በመካከላችሁ ለአስታራቂ
ነት የሚበቃ ሽማግሌ አይገኝምን? 6 ታዲያ
አንድ ክርስቲያን ሌላውን ክርስቲያን ከስሶ ወደ
አረማውያን ፍርድ ቤት መውሰድ ይገባዋልን?
7 እንዲያውም እርስ በርሳችሁ መሟገት ራሱ
ለእናንተ ውርደት ነው፤ ይልቅስ እናንተ ብትበ
ደሉ አይሻልምን? እንዲሁም እናንተ
ብትጨቈኑ አይሻልምን? 8 እናንተ ግን ወንድ
ሞቻችሁ በሆኑት ክርስቲያኖች ላይ እንኳ በደ
ልና ግፍ ታደርጋላችሁ። 9 ዐመፀኞች የእግዚአ
ብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ ታውቁ የለ
ምን? በዚህ ነገር አትታለሉ፥ ሴሰኞች ወይም

ጣዖት አምላኪዎች ወይም አመንዝራዎች
ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚያደርጉ ወን
ዶች፥ 10ወይም ሌቦች ወይም ስግብግቦች
ወይም ሰካራሞች ወይም የሰው ስም አጥፊዎች
ወይም ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት
አይወርሱም። 11ከእናንተም አንዳንዶቻችሁ
እንዲሁ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስ ስምና በአምላካችን መንፈስ ከኃጢ
አት ታጥባችኋል፤ ለእግዚአብሔር የተለየ
ቅዱስ ሕዝብ ሆናችኋል፤ ጸድቃችኋልም።

### ሰውነታችሁን ለእግዚአብሔር ክብር አውሉት

12ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፤ ግን ሁሉም
ነገር ይጠቅመኛል ማለት አይደለም፤ ሁሉም
ነገር ተፈቅዶልኛል፤ ይሁን እንጂ ለማናቸውም
ነገር ባሪያ ሆኜ አልገዛም፤ 13ምግብ ለሆድ፥
ሆድም ለምግብ ነው፤ ታዲያ እኮ እግዚአብ
ሔር ምግብንም ሆድንም ያጠፋቸዋል፤ ነገር
ግን ሰውነታችን ለጌታ ኢየሱስ፥ ጌታ ኢየሱስም
ለሰውነታችን ስለሆነ፥ ሰውነታችንን ለዝሙት
ማዋል አይገባንም። 14እግዚአብሔር ጌታ ኢየ
ሱስን ከሞት እስነሥቶታል፤ እኛንም በኀይሉ
ከሞት ያስነሣል።
15ሰውነታችሁ የክርስቶስ አካል ክፍል መሆ
ኑን ታውቁ የለምን? ታዲያ የክርስቶስን አካል
ክፍል ወስጄ የአመንዝራ ሴት አካል ክፍል እን
ዲሆን ላደርገው ይገባልን? ከቶ አይገባም!
16ከአመንዝራ ሴት ጋር በግብረ ሥጋ የሚተባ
በር ሰው ከእርስዋ ጋር አንድ አካል መሆኑን
ታውቁ የለምን? ምክንያቱም፥

"ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ" ተብሎ
ተጽፎአል።

17ከጌታ ኢየሱስ ጋር የሚተባበር ሰው ግን ከእ
ርሱ ጋር በመንፈስ አንድ ይሆናል።
18ስለዚህ ከዝሙት ራቁ፤ ሰው የሚያደር
ገው ሌላው ኃጢአት ሁሉ ከሰውነቱ ውጪ
የሚደረግ ነው፤ ዝሙትን የሚፈጽም ሰው ግን
በገዛ ሰውነቱ ላይ ኃጢአት ያደርጋል፤ 19ሰውነ
ታችሁ፥ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትና በው
ስጣችሁም የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ
መቅደስ መሆኑን ታውቁ የለምን? እንግዲህ
እናንተ የእግዚአብሔር ናችሁ እንጂ የራሳችሁ
አይደላችሁም። 20ምክንያቱም እርሱ በዋጋ
ገዝቶአችኋል፤ ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብ
ሔርን አክብሩ።

## ምዕራፍ 7

### ስለ ጋብቻ የቀረበ ጥያቄና የተሰጠው መልስ

1ስለ ጻፋችሁልኝ ጥያቄ ሰው ከሴት ጋር
በግብረ ሥጋ ባይገናኝ ወይም ሚስት ባያገባ
መልካም ነው። 2ነገር ግን በዝሙት ኃጢአት
ላለመውደቅ፥ እያንዳንዱ ወንድ የራሱ ሚስት
ትኑረው፤ እያንዳንዱዋም ሴት የራስዋ ባል ይኑ
ራት። 3ባል ለሚስቱ ማድረግ የሚገባውን የጋ
ብቻ መብትዋን አይከልክላት፤ እንዲሁም
ሚስት ለባልዋ ማድረግ የሚገባትን የጋብቻ
መብቱን አትከልክለው። 4ሚስት በሰውነቷ
ላይ ሥልጣን የላትም፤ በእርስዋ ሰውነት ላይ
ሥልጣን ያለው ባልዋ ነው። እንዲሁም ባል
በሰውነቱ ላይ ሥልጣን የለውም፤ በእርሱ ሰው
ነት ላይ ሥልጣን ያላት ሚስቱ ነች። 5በጸሎት
ለመትጋት ሁለታችሁም ተስማምታችሁ ለተወ
ሰነ ጊዜ ካልሆነ በቀር በመለያየት አንዱ የሌላ
ውን የጋብቻ መብት አይከልክል። ራሳችሁን
መቈጣጠር አቅቶአችሁ ሰይጣን እንዳይፈታተና
ችሁ እንደገና አብራችሁ ሁኑ።
6ይህን ግን የምላችሁ እንደምክር ነው
እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም። 7ሰው ሁሉ
እንደ እኔ ሚስት ሳያገባ ቢኖር በወደድሁ
ነበር፤ ነገር ግን ለእያንዳንዱ እግዚአብሔር የተ
ለየ ስጦታ ሰጥቶታል፤ አንዱ አንድ ዐይነት
ስጦታ፥ ሌላውም ሌላ ዐይነት ስጦታ አለው።
8ላላገቡና እንዲሁም ባሎቻቸው ለሞቱባ
ቸው ሴቶች የምለው እንዲህ ነው፥ ሳያገቡ
እንደ እኔ ቢኖሩ መልካም ነው። 9ነገር ግን
ራሳቸውን መቈጣጠር ቢያቅታቸው ያግቡ፤
ምክንያቱም በሥጋ ምኞት ከመቃጠል ይልቅ
ማግባት የተሻለ ነው።
10ላገቡት ግን የምሰጠው ትእዛዝ ይህ ነው፤
ይህም ትእዛዝ የጌታ ነው እንጂ የእኔ አይደ
ለም፤ ያገባች ሴት ከባልዋ አትለይ፤ 11ብትለ
ይም ሳታገባ ለብቻዋ ትኑር፤ ወይም ከባልዋ
ጋር ትታረቅ፤ እንዲሁም ባል ሚስቱን አይ
ፍታ።
12ለሌሎቹ ግን ጌታ ሳይሆን እኔ ራሴ የም
ለው እንዲህ ነው፤ አንድ ክርስቲያን ሰው፥
ክርስቲያን ያልሆነች ሚስት ብትኖረውና አብ
ራው ለመኖር ብትፈልግ አይፍታት። 13ክርስቲ
ያን ሴት፥ ክርስቲያን ያልሆነ ባል ቢኖራትና
አብሮአት ለመኖር ቢፈልግ አትፍታው።
14ምክንያቱም ክርስቲያን ያልሆነ ባል፥ ክርስ
ቲያን በሆነች ሚስቱ ምክንያት እግዚአብሔር
ይቀበለዋል፤ ክርስቲያን ያልሆነች ሚስትም፥
ክርስቲያን በሆነው ባልዋ ምክንያት እግዚአብ
ሔር ይቀበላታል፤ እንደዚህ ካልሆነማ ልጆቻ
ችሁ የእግዚአብሔር ሰዎች ሊሆኑ አይችሉም፤
በዚህ ዐይነት ሁኔታ ከኖራችሁ ግን ልጆቻችሁ
የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው። 15ክርስቲያን
ያልሆነ ወገን መለየት ከፈለገ ይለይ፤ በዚህ
ጊዜ ግን ክርስቲያን የሆነው ወገን ባልም ሆነ

6፥12 ፦ 1ቆሮ. 10፥23። 6፥16 ፦ ዘፍ. 2፥24። 6፥19 ፦ 1ቆሮ. 3፥16፤ 2ቆሮ. 6፥16።
7፥10-11 ፦ ማቴ. 5፥32፤ 19፥9፤ ማር. 10፥11-12፤ ሉቃ. 16፥18።



ሚስት፥ በምንም ዐይነት ግዴታ አይያዝም።
ምክንያቱም እግዚአብሔር የጠራን እኮ በሰላም
እንድንኖር ነው። 16አንቺ ክርስቲያን ሴት፥
ክርስቲያን ያልሆነውን ባልሽን ምናልባት ታድ
ኚው እንደሆን ምን ታውቂያለሽ? አንተስ ክርስ
ቲያን ወንድ፥ ክርስቲያን ያልሆነች ሚስትህን
ምንአልባት ታድናት እንደሆንህ ምን ታውቃ
ለህ?

### እግዚአብሔር ሲጠራችሁ በነበራችሁበት ሁኔታ ኑሩ

17እያንዳንዱ እግዚአብሔር በሰጠው ስጦ
ታና እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ በነበረበት
ሁኔታ ይኑር፤ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሰ
ጠሁት ደንብ ይህንኑ ነው። 18ማንም ሰው ከተ
ገረዘ በኋላ የተጠራ ከሆነ እንዳልተገረዘ ለመሆን
አያስብ፤ ሳይገረዝ የተጠራ ከሆነም የመገረዝ
ግዴታ የለበትም። 19መገረዝም ሆነ አለመገረዝ
ዋጋ የለውም፤ ዋናው ነገር የእግዚአብሔርን
ትእዛዝ መፈጸም ነው። 20ስለዚህ እያንዳንዱ
ሰው እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ በነበረበት
ሁኔታ ይኑር። 21እግዚአብሔር በጠራህ ጊዜ
ባሪያ ነበርህን? ብትሆንም ግድ የለም፥ አትጨ
ነቅበት፤ ነፃ የመውጣት ዕድል ብታገኝ ግን
ይህ ዕድል አያምልጥህ። 22ምክንያቱም ባሪያ
ሆኖ ሳለ በጌታ የተጠራ ሰው በጌታ ነፃነትን
አግኝቶአል፤ እንዲሁም ነፃ ሆኖ ሳለ የተጠራ
ሰው የክርስቶስ ባሪያ ነው። 23እግዚአብሔር
በዋጋ ስለገዛችሁ የሰው ባሪያዎች አትሁኑ።
24ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ! እያንዳንዱ ሰው
በተጠራበት ጊዜ በነበረበት ሁኔታ በእግዚአብ
ሔር ፊት ይኑር።

### ስላላገቡና ስለ መበለቶች የቀረበ ጥያቄ

25ስላላገቡ ሰዎች ከጌታ ኢየሱስ የተቀበል
ሁት ትእዛዝ የለኝም፤ ነገር ግን በእግዚአብ
ሔር ምሕረት እምነት የሚጣልብኝ እንደመሆኔ
መጠን የራሴ አሳብ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው፤
26አሁን ያለንበት ጊዜ የችግር ጊዜ ስለሆነ
ሳያገቡ በብቸኝነት መኖር መልካም ይመስለ
ኛል፤ 27ሆኖም ሚስት አግብተህ እንደሆን፥
ለመፍታት አትፈልግ፤ ሚስት አላገባህ እንደ
ሆን ለማግባት አትፈልግ። 28ነገር ግን አንተ
ሚስት ብታገባ ኃጢአት ይሆንብሃል ማለት አይ
ደለም፤ እንዲሁም አንዲት ልጃገረድ ባል ብታ
ገባ ኃጢአት ይሆንባታል ማለት አይደለም፤
ይሁን እንጂ የሚያገቡ ሰዎች በዚህ ዓለም ብዙ
የኑሮ ችግር ይገጥማቸዋል፤ የእኔም ምኞት
ከዚህ ችግር እንድትድኑ ነው።
29ወንድሞቼ ሆይ! እኔ የምላችሁ እንዲህ
ነው፤ ዘመኑ አጥሮአል፤ ከእንግዲህ ወዲህ
ሚስት ያለው፤ ሚስት እንደሌለው ሆኖ
ይኑር። 30የሚያዝን እንደማያዝን፥ የሚደሰት
እንደማይደሰት ሆኖ ይኑር፤ ዕቃ የሚገዛ፥
ዕቃው የራሱ እንዳልሆነ አድርጎ ይቍጠር።
31በዓለም ሀብት የሚጠቀም፥ በሙሉ እንደማ
ይጠቀምበት ሆኖ ይኑር፤ ምክንያቱም የአሁኑ
ዓለም ሁኔታ አላፊ ነው።
32ስለዚህ በምንም አሳብ ሳትጨነቁ እንድት
ኖሩ እወዳለሁ፤ ሚስት ያላገባ ሰው፥ ጌታ ኢየ
ሱስ የሚደሰትበትን ነገር ስለሚፈልግ፥ አሳቡ
የሚያተኵረው ጌታ ኢየሱስን በሚመለከት ሥራ
ነው። 33ሚስት ያገባ ሰው ግን የሚያስበው ስለ
ዚህ ዓለም ነገርና ሚስቱንም የሚያስደስትበትን
ነገር ነው። 34በዚህ ሁኔታ አሳቡ በሁለት ተከ
ፍሎአል ማለት ነው። እንዲሁም ባል ያላገባች
ሴት ወይም ልጃገረድ በሥጋዋና በነፍስዋ ተቀ
ድሳ የእግዚአብሔር ለመሆን ስለምትፈልግ
አሳቧ የሚያተኵረው ጌታ ኢየሱስን በሚመለ
ከት ሥራ ነው። ያገባች ሴት ግን ባልዋን ለማስ
ደሰት ስለምትፈልግ የምታስበው የዓለምን ነገር
ነው።
35እኔ ይህን የምላችሁ በወጥመድ ውስጥ
ገብታችሁ እንድትቸገሩ ብዬ ሳይሆን እንድትጠ
ቀሙ ብዬ ነው፤ ምኞቴም እናንተ በተገቢው
ሁኔታ እንድትኖሩና አሳባችሁ ሳይባክን በሙሉ
ልባችሁ ጌታ ኢየሱስን እንድታገለግሉ ነው።
36አንድ ሰው ላለማግባት ወስኖ ሳለ እጮ
ኛው ለጋብቻ የደረሰች ብትሆንና የሥጋ ፍትወ
ቱን ለመቈጣጠር ባለመቻሉ ሊያገባት ቢያ
ስብ፥ ያግባት፤ ቢያገባት ምንም ኃጢአት የለበ
ትም። 37ነገር ግን ለማግባት የሚያስገድደው
ነገር ከሌለ፥ ላለማግባት ችሎታ ካለውና ላለማ
ግባትም ቍርጥ ውሳኔ ካደረገ፥ አለማግባቱ
መልካም ነው። 38ስለዚህ ሚስት የሚያገባ
መልካም ያደርጋል፤ የማያገባ ግን የተሻለ ያደ
ርጋል።
39ሚስት ባልዋ በሕይወት እስካለ ድረስ
በጋብቻ ሕግ የታሰረች ናት፤ ባልዋ ከሞተ ግን
የፈለገችውን ልታገባ ትችላለች፤ ሆኖም የምታ
ገባው ሰው ክርስቲያን መሆን አለበት። 40በእኔ
አስተያየት ግን ባል ሳታገባ ብቻዋን ብትሆን
ይበልጥ ተደስታ ትኖራለች፤ እኔም እኮ የእግዚ
አብሔር መንፈስ ያለኝ ይመስለኛል።

## ምዕራፍ 8

### ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ

1ለጣዖት ስለ ተሠዋ ሥጋ የሆነ እንደሆን፥
እርግጥ ነው "ሁላችንም ዕውቀት አለን፤"
ይሁን እንጂ ዕውቀት ያስታብያል፤ ፍቅር ግን
ያንጻል። 2"ዕውቀት አለኝ" ብሎ የሚያስብ
ሰው ቢኖር የሚገባውን ያህል ገና አላወቀም።
3እግዚአብሔርን የሚወድድ ሰው ግን በእግዚአ
ብሔር ዘንድ የታወቀ ይሆናል።

4 ስለዚህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለ መብ
ላት የሆነ እንደሆን ፥ ጣዖት በዚህ ዓለም ከም
ንም እንደማይቈጠር እናውቃለን ፤ እንዲሁም
ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ እን
ደሌለ እናውቃለን ። 5 ምንም እንኳ አምላክ ሳይ
ሆኑ አምላክ ተብለው የሚጠሩ ብዙ አማልክ
ትና ብዙ ጌቶች በሰማይም ሆነ በምድር አሉ
ቢባልም ፥ 6 የእኛ አምላክ ግን የሁሉ ነገር
ፈጣሪ የሆነና እኛም የእርሱ የሆንን አንዱ እግ
ዚአብሔር አብ ብቻ ነው ፤ እንዲሁም ፥ ሁሉ
ነገር በእርሱ የተፈጠረና እኛም በእርሱ የምን
ኖር አንዱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ።
7 ነገር ግን ይህን የሚያውቁ ፥ ሁሉም አይደ
ሉም ፤ አንዳንዶች እስከ አሁን ድረስ ጣዖትን
ማምለክ ስለለመዱ ሥጋን የሚበሉት ለጣዖት
እንደተሠዋ አድርገው ነው ፤ ስለዚህ ኅሊናቸው
ደካማ በመሆኑ ይረክሳሉ ። 8 ዳሩ ግን ወደ እግ
ዚአብሔር የሚያቀርበን መብል አይደለም ፤ ባን
በላም የሚጐድልብን ነገር የለም ፤ ብንበላም
የምናተርፈው ነገር የለም ።
9 ይሁን እንጂ ይህ ነፃነታችሁ በእምነት ላል
ጠነከሩ መሰናከያ እንዳይሆንባቸው ተጠንቀቁ ።
10 ምክንያቱም "ዕውቀት አለኝ" ብለህ ለጣዖት
የተሠዋውን በጣዖት ቤት ስትበላ በእምነቱ ያል
ጠነከረ ሰው ቢያይህ ፥ ይህ ድርጊትህ ሰውየው
ለጣዖት የተሠዋውን እንዲበላ ያደፋፍረው የለ
ምን? 11 ስለዚህ በአንተ "ዐዋቂ ነኝ" ባይነት
ክርስቶስ የሞተለትና በእምነቱ ያልጠነከረ ክርስ
ቲያን ይጠፋል ማለት ነው ። 12 በዚሁ ሁኔታ
ክርስቲያን ወንድሞቻችሁን በመበደልና ደካማ
ኅሊናቸውንም በማቊሰል ክርስቶስን ትበድላላ
ችሁ ። 13 ስለዚህ ምግብ ክርስቲያን ወንድሜን
የሚያሰናክለው ከሆነ ፥ ወንድሜን ላለማሰናከል
ስል ከቶ ሥጋ አልበላም ።

## ምዕራፍ 9

### የሐዋርያ መብትና ግዴታ

1 እኔ ነፃነት ያለኝ ሰው አይደለሁምን? እኔ
ሐዋርያ አይደለሁምን? እኔ ጌታችንን ኢየሱስን
አይቸው የለምን? እናንተስ በጌታ ኢየሱስ የሥ
ራዬ ውጤት አይደላችሁምን? 2 በጌታ የሐዋር
ያነቴ ማረጋገጫ ማኅተም እናንተ ስለሆናችሁ ፥
ለሌሎቹ እንኳ ሐዋርያ ባልሆን ለእናንተ ግን
በእርግጥ ሐዋርያ ነኝ ።
3 "የሐዋርያነት መብት የለህም" ብለው
የሚተቹኝ ቢኖሩ የምሰጠው መልስ ይህ ነው ፥
4 እኔ ምግብና መጠጥ የማግኘት መብት የለኝ
ምን? 5 እንደ ሌሎች ሐዋርያትና እንደ ጌታ
ኢየሱስ ወንድሞች እንደ ጴጥሮስም ክርስቲያን
ሚስት አስከትዬ የመዞር መብት የሌለኝ እኔ
ብቻ ነኝን? 6 ወይስ በሥራ እየጣርን መኖር
የሚገባን በርናባስና እኔ ብቻ ነንን? 7 ያለ ደመ
ወዝ በራሱ ገንዘብ በወታደርነት የሚያገለግል
ማነው? ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ
ማነው? መንጋ እየጠበቀ የመንጋውን ወተት
የማይጠጣ ማን ነው?
8 ይህን የምናገረው በሰው አስተሳሰብ ብቻ
ነውን? ሕግስ እንዲህ ይል የለምን? 9 ምክንያ
ቱም "የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር"
ተብሎ በሙሴ ሕግ ተጽፎአል ፤ ታዲያ እግዚአ
ብሔር ይህን ያለው ስለ በሬዎች በማሰብ
ነውን? 10 እግዚአብሔር ይህን ያለው ስለእኛ
በማሰብ አይደለምን? የሚያርስ በተስፋ እንዲያ
ርስ ፥ የሚያበራይም በተስፋ እንዲያበራይ ፥
በዚህ ዐይነት ሁሉም ድርሻውን እንዲያገኝ ይህ
የተጻፈው በእርግጥ ስለ እኛ ነው ። 11 እኛ መን
ፈሳዊውን ነገር የዘራንላችሁ ከሆነ ፥ የእናንተን
ሥጋዊ በረከት ብናጭድ ትልቅ ነገር መሆኑ
ነውን? 12 ሌሎች ይህን ነገር ከእናንተ የመካ
ፈል መብት ያላቸው ከሆነ ታዲያ እኛ ከዚህ
የሚበልጥ መብት እንዴት አይኖረንም? እኛ
ግን በዚህ መብት አልተጠቀምንም ፤ ይህን ማድ
ረጋችንም የክርስቶስ የምሥራች ቃል ከመስፋ
ፋት እንዳይገታ በማሰብ ሁሉን ነገር ታግሠን
እንቻል ብለን ነው ። 13 በቤተ መቅደስ የሚያገ
ለግሉ ምግባቸውን ከቤተ መቅደስ እንደሚያገ
ኙና በመሠዊያው ላይ መሥዋዕት የሚያቀርቡና
የሚያገለግሉ ከመሥዋዕት ተካፍለው እንደሚ
በሉ ታውቁ የለምን? 14 እንዲሁም ደግሞ መል
ካም ዜናን የሚያበሥሩ ቀለባቸውን ከዚሁ
ሥራቸው እንዲያገኙ ጌታ ኢየሱስ ደንግጎአል ።
15 እኔ ግን በእነዚህ መብቶች አልተጠቀም
ሁም ፤ ይህንንም የጻፍሁት "መብቴ ሳይከበር
ልኝ ለምን ቀረ?" በማለት አይደለም ። ሰው
ትምክሕቴን ከንቱ ከሚያደርግብኝ ይልቅ
ብሞት ይሻለኛል ። 16 የምሥራቹን ቃል ማብ
ሠር ግዴታዬ ስለሆነ የምመካበት ነገር አይደ
ለም ፤ እንዲያውም የምሥራቹን ቃል ሳላበሥር
ብቀር ወዮልኝ! 17 የምሥራቹን ቃል ያለ
ግዴታ በፈቃዴ ባበሥር የድካም ዋጋ ይኖረ
ኛል ፤ በግዴታ ባደርገው ግን በዐደራ የተሰጠ
ኝን ኀላፊነት ፈጸምሁ እንጂ ሌላ ያደረግሁት
ነገር አለ ማለት አይደለም ። 18 ታዲያ የድካሜ
ዋጋ ምንድን ነው? እንግዲህ የድካሜ ዋጋ ፥
የምሥራቹን ቃል በማብሠሬ ያለኝን መብት
ሳልጠቀምበት ፥ የምሥራቹን ቃል የማብሠር
ሥራዬን ያለ ደመወዝ መፈጸም ነው ።
19 እኔ እኮ የማንም ባሪያ ሳልሆን ነፃ ሰው
ነኝ ፤ ይሁን እንጂ በተቻለኝ መጠን ብዙዎቹን

9፡9 ፦ ዘዳ. 25፡4 ፤ 1ጢሞ. 5፡18 ። 9፡11 ፦ ሮም 15፡27 ። 9፡13 ፦ ዘዳ. 18፡1 ። 9፡14 ፦ ማቴ. 10፡10 ፤ ሉቃ. 10፡7 ።



በማዳን ለመጥቀም ብዬ የሁሉም ባሪያ ሆኜአ
ለሁ ። 20 ከአይሁዳውያን ጋር ስሆን አይሁዳውያ
ንን ለማዳን እንደ አይሁዳዊ ሆንሁ ፤ ምንም
እንኳ እኔ ከሙሴ ሕግ በታች ባልሆንም ፥
ከሙሴ ሕግ በታች ያሉትን ለማዳን ስል ከሙሴ
ሕግ በታች እንዳሉት ሰዎች ሆንሁ ። 21 ምንም
እንኳ እኔ የእግዚአብሔር ሕግ ያለኝና ከክርስ
ቶስ ሕግ ሥር ብሆንም ፥ ሕግ የሌላቸውን አረ
ማውያንን ለማዳን ስል ሕግ እንደሌለው ሰው
ሆንሁ ። 22 በእምነት ደካሞች የሆኑትን ለማዳን
ስል እንደ ደካሞች ደካማ ሆንሁ ፤ በተቻለ
መጠን አንዳንዶችን ለማዳን ከሁሉም ጋር
ሁሉን ነገር ሆንሁ ።
23 ይህን ሁሉ ማድረጌ የምሥራቹን ቃል በረ
ከት ለመካፈል ፥ ስለ ምሥራቹ ቃል ብዬ
ነው ። 24 በሩጫ ውድድር ሁሉም እንደሚሮ
ጡና ከእነርሱም አንዱ ብቻ ሽልማት እንደሚ
ቀበል ታውቁ የለምን? ስለዚህ እናንተም ሽል
ማትን ለመቀበል ሩጡ ። 25 በሩጫ የሚወዳደሩ
ሁሉ አድካሚ ልምምድ ያደርጋሉ ፤ እነርሱ
እንዲህ የሚደክሙት የሚጠፋውንና ጊዜያዊ
የሆነውን አክሊል ለማግኘት ነው ፤ እኛ ግን
የምንደክመው የማይጠፋውንና ዘላለማዊ የሆነ
ውን አክሊል ለማግኘት ነው ። 26 እኔ ግን ግብ
እንደሌለው ሰው በከንቱ አልሮጥም ፤ ከነፋስ
ጋር እንደሚታገል በከንቱ የምታገል ሰው አይ
ደለሁም ። 27 ስለዚህ ሌሎችን ወደ ውድድር
ከጠራሁ በኋላ እኔ ራሴ ከውድድሩ ውጭ ሆኜ
እንዳልገኝ ፥ ሰውነቴን እየተቈጣጠርሁ እንዲታ
ዘዝልኝ አደርገዋለሁ ።

## ምዕራፍ 10

### የማስጠንቀቂያ ምሳሌነት

1 ወንድሞቼ ሆይ! አባቶቻችን ደመና ከበላያ
ቸው ሆኖ ይመራቸው እንደነበረና ሁሉም ቀይ
ባሕርን እንደተሻገሩ ላስታውሳችሁ እወዳለሁ ።
2 የሙሴ ተባባሪዎች ለመሆንም በዚህ ደመናና
በዚህ ባሕር ተጠመቁ ። 3 ሁሉም አንድ ዐይነት
መንፈሳዊ ምግብ ተመገቡ ። 4 ሁሉም አንድ
ዐይነት መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ ፤ የጠጡትም
ይከተላቸው ከነበረው ከዚያ ከመንፈሳዊ አለት
ነበር ፤ ያም አለት ራሱ ክርስቶስ ነበር ።
5 ይህም ሆኖ እግዚአብሔር በአብዛኞቹ አልተደ
ሰተም ፤ ስለዚህ ሬሳቸው በበረሓ ወድቆ ቀረ ።
6 እነርሱ ክፉ ነገር እንደተመኙ ፥ እኛም
ክፉ ነገር እንዳንመኝ ይህ ሁሉ ለእኛ የማስጠን
ቀቂያ ምሳሌ ሆኖናል ። 7 "ሰዎች ሊበሉና
ሊጠጡ ተቀመጡ ፤ ሊዘፍኑም ተነሡ" ተብሎ
ስለ እነርሱ እንደተጻፈው ፥ እነርሱ ጣዖትን እን
ዳመለኩ እናንተም እንደእነርሱ ጣዖትን አታም
ልኩ ። 8 ከእነርሱ አንዳንዶቹ የዝሙት ኃጢአት
እንዳደረጉ ፥ እኛም የዝሙት ኃጢአት አናድ
ርግ ፤ ምክንያቱም እነርሱ ይህን በማድረጋቸው
ከእነርሱ ሃያ ሦስት ሺ ሰዎች በአንድ ቀን ሞተ
ዋል ። 9 ከእነርሱ አንዳንዶቹ ጌታ እግዚአብሔ
ርን2* እንደተፈታተኑትና በእባብ ተነክሰው
እንደ ሞቱ ፥ እኛም ጌታ እግዚአብሔርን አንፈ
ታተነው ። 10 ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳጕረመረ
ሙና በአጥፊውም እንደጠፉ ፥ እናንተም
አታጕረምርሙ ።
11 ይህ ሁሉ ነገር የደረሰባቸው ለእኛ የማስ
ጠንቀቂያ ምሳሌ እንዲሆን ነው ፤ የተጻፈውም
በዘመናት መጨረሻ ላይ ለምንገኘው ለእኛ
ትምህርት እንዲሆነን ነው ።
12 ስለዚህ የቆመ የሚመስለው ሰው ፥ እንዳይ
ወድቅ ይጠንቀቅ ። 13 በሰው ከሚደርሰው ፈተና
በቀር ሌላ ፈተና አልደረሰባችሁም ፤ እግዚአብ
ሔርም ታማኝ ነው ፤ ምክንያቱም ከአቅማችሁ
በላይ የሆነ ፈተና እንዲደርስባችሁ አይፈቅ
ድም ፤ በምትፈተኑበትም ጊዜ የምትታገሡበ
ትን ኀይል በመስጠት ከፈተናው የምትወጡበ
ትን መንገድ ያዘጋጅላችኋል ።
14 እንግዲህ ወዳጆቼ ሆይ! ጣዖትን ከማም
ለክ ራቁ ። 15 ይህንንም የምላችሁ አስተዋዮች
በመሆናችሁ ነው ፤ ስለዚህ እኔ የምናገረውን
እናንተ ራሳችሁ ፍረዱ ። 16 እግዚአብሔርን
አመስግነን የምንካፈለው የበረከት ጽዋ ከክርስ
ቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? አብ
ረን የምንቈርሰውስ ኅብስት ከክርስቶስ ሥጋ
ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? 17 ኅብስቱ
አንድ በመሆኑ ፥ እኛም ከዚህ ከአንዱ ኅብስት
የምንካፈል ስለሆንን ፥ ምንም እንኳ ብዙዎች
ብንሆን አንድ አካል ነን ።
18 እስቲ የእስራኤል ሕዝብ ያደረጉትን ተመ
ልከቱ ፤ መሥዋዕቱን የሚበሉ ከመሠዊያው ጋር
ኅብረት አልነበራቸውምን? 19 ታዲያ ይህን ስል
ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ የሚረባ ነገር ነው ማለቴ
ነውን? ወይስ ጣዖት የሚረባ ነገር ነው ማለቴ
ነውን? 20 አይደለም! አረማውያን መሥዋዕት
የሚያቀርቡት ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለአጋን
ንት ነው ፤ ስለዚህ እናንተ ከአጋንንት ጋር ኅብ
ረት እንዲኖራችሁ አልፈልግም ፤ 21 የጌታን
ጽዋ እየጠጣችሁ ደግሞ የአጋንንትን ጽዋ
መጠጣት አትችሉም ፤ የጌታ ማእድ ተካፋዮች

2* 10፡9 ጌታ እግዚአብሔርን ፦ አንዳንድ ቅጂዎች "ክርስቶስን" ይላሉ ። ❖
10፡1 ፦ ዘጸ. 13፡21-22 ፤ 14፡22-29 ። 10፡3 ፦ ዘጸ. 16፡35 ። 10፡4 ፦ ዘጸ. 17፡6 ፤ ዘኍ. 20፡11 ።
10፡5 ፦ ዘኍ. 14፡29-30 ። 10፡6 ፦ ዘኍ. 11፡4 ። 10፡7 ፦ ዘጸ. 32፡6 ። 10፡8 ፦ ዘኍ. 25፡1-18 ።
10፡9 ፦ ዘኍ. 21፡5-6 ። 10፡10 ፦ ዘኍ. 16፡41-49 ። 10፡16 ፦ ማቴ. 26፡26-28 ፤ ማር. 14፡22-24 ፤ ሉቃ. 22፡19-20 ።
10፡18 ፦ ዘሌ. 7፡6 ። 10፡20 ፦ ዘዳ. 32፡17 ።

ሆናችሁ፣ ደግሞ የአጋንንትን ማእድ ተካፋይ
መሆን አትችሉም፤ 22 ታዲያ ይህን በማድረግ
ጌታን እናስቀናውን? እኛ ከእርሱ ይበልጥ እን
በረታለንን?
23 ሁሉ ነገር ተፈቅዶአል፤ ነገር ግን ሁሉ
ነገር ጠቃሚ አይደለም፤ ሁሉ ነገር ተፈቅዶ
አል፣ ነገር ግን ሁሉ ነገር የሚያንጽ አይደ
ለም። 24 እያንዳንዱ ሰው የሌሎችንም ጥቅም
ያስብ እንጂ የራሱን ጥቅም ብቻ አይመልከት።
25 ከገሊናችሁ የሚነሣውን ጥርጣሬ አስወግ
ዳችሁ በገበያ የሚሸጠውን ሥጋ ሳታመነቱ
ብሉ። 26 ምክንያቱም "ምድርና በእርስዋም
ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር ነው።"
27 ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ቢጋብዛችሁና
ግብዣውንም ብትቀበሉ፣ የሚቀርብላችሁን
ማንኛውንም ምግብ ከኅሊናችሁ የሚነሣውን
ጥርጣሬ አስወግዳችሁ ሳታመነቱ ብሉ።
28 ነገር ግን አንድ ሰው "ይህ ሥጋ ለጣዖት የተ
ሠዋ ነው" ቢላችሁ፣ ይህን በነገራችሁ ሰው
ምክንያትና በኅሊናም ምክንያት ሥጋውን አት
ብሉ። 29 ኅሊናም ስላችሁ የሰውየውን ኅሊና
ማለቴ ነው እንጂ የእናንተን ኅሊና ማለቴ አይ
ደለም፤
ታዲያ በሌላው ሰው ኅሊና ምክንያት በእኔ
ነፃነት ላይ የሚፈረደው ለምንድን ነው? 30 እኔ
እግዚአብሔርን እያመሰገንሁ ብበላ፣ እግዚአብ
ሔርን በማመስግንበት ነገር ስለምን እወቀስበታ
ለሁ?
31 እንግዲህ ስትበሉም ሆነ፣ ስትጠጡ
ወይም ማናቸውንም ነገር ስታደርጉ፣ ሁሉንም
ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉ። 32 አይሁ
ዳውያንንም ቢሆን፣ ግሪካውያንንም ቢሆን የእ
ግዚአብሔርንም ቤተ ክርስቲያን ቢሆን ማንንም
አታሰናክሉ። 33 እኔ ሁሉም እንዲድኑ የሌሎ
ችን ጥቅም እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ
ሁሉን ሰው በሁሉ ነገር እንደማስደስት፣ እናን
ተም እንዲሁ አድርጉ።

## ምዕራፍ 11

1 እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እናንተም
እኔን ምሰሉ።

### በማኅበራዊ ጸሎት ጊዜ ሊኖር የሚገባው ሥነ ሥርዓት

2 ዘወትር ስለምታስታውሱኝና የሰጠኋችሁ
ንም ትምህርት አጥብቃችሁ ስለያዛችሁ አመሰ
ግናችኋለሁ። 3 ነገር ግን በወንድ ሁሉ ላይ
ሥልጣን ያለው ክርስቶስ መሆኑን፣ በሚስት
ላይ ሥልጣን ያለው ባል መሆኑንና በክርስቶ
ስም ላይ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር አብ
መሆኑን እንድታውቁ እወዳለሁ። 4 ራሱን ተከና
ንቦ የሚጸልይ ወይም የትንቢት ቃል የሚናገር
ወንድ ሁሉ፣ በወንድ ላይ ሥልጣን ያለውን
ክርስቶስን ያዋርዳል። 5 እንዲሁም ራስዋን ሳት
ከናንብ የምትጸልይ ወይም የትንቢት ቃል የም
ትናገር ሴት፣ በሴት ላይ ሥልጣን ያለውን
ወንድ ታዋርዳለች፤ ምክንያቱም ራስዋን የማት
ከናንብ ሴት እንደተላጨች ትቈጠራለች። 6 ሴት
ራስዋን የማትከናንብ ከሆነ ጠጕርዋን ትቈረጥ፤
ነገር ግን ጠጕርዋን መቈረጥ ወይም መላጨት
የሚያዋርዳት ነገር ከሆነ ራስዋን ትከናንብ።
7 ወንድ የእግዚአብሔር መልክና የእግዚአብ
ሔር ክብር የሚገለጥበት ስለሆነ ራሱን መከና
ነብ አይገባውም፤ ሴት ግን የወንድ ክብር
ናት። 8 ምክንያቱም ሴት ከወንድ ተገኘች
እንጂ ወንድ ከሴት አልተገኘም። 9 እንዲሁም
ሴት ለወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ለሴት አል
ተፈጠረም፤ 10 በዚህ ምክንያትና በመላእክትም
ምክንያት ሴት በወንድ ሥልጣን ሥር መሆን
ዋን ለማሳየት ራስዋን መከናነብ አለባት።
11 በጌታ ኢየሱስ ባለን ሕይወት ሴት ያለ ወንድ
አትኖርም፤ ወንድም ያለ ሴት አይኖርም።
12 ምክንያቱም ሴት ከወንድ እንደተገኘች፣ እን
ዲሁም ወንድ የሚወለደው ከሴት ነው፤ ነገር
ግን ወንድም ሆነ ሴት ሌላውም ነገር ሁሉ
የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው።
13 እስቲ ራሳችሁ ፍረዱ፤ ሴት ራስዋን ሳት
ከናንብ ወደ እግዚአብሔር መጸለይዋ ተገቢ
ነውን? 14 ወንድ ጠጕሩን ቢያስረዝም ነውር
እንደሚሆንበት ተፈጥሮ ራሱ ያስተምራችሁ
የለምን? 15 ሴት ግን ጠጕር የተሰጣት ራሷን
ልትሸፍንበት ስለሆነ ጠጕርዋን ብታስረዝም
ለእርስዋ ክብርዋ ነው። 16 ስለዚህ ጒዳይ መከ
ራከር የሚፈልግ ሰው ቢኖር፣ እኛም ሆንን
ወይም ሌሎች የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲ
ያናት ከዚህ የተለየ ልማድ የለንም።

### የቅዱስ ቊርባን ሥርዓት (የጌታ ራት)
(ማቴ. 26፡26-29፤ ማር. 14፡22-25፤
ሉቃ. 22፡14-20)

17 በምትሰበሰቡበት ጊዜ የምታደርጉት፣
የሚጐዳችሁን እንጂ የሚጠቅማችሁን ነገር ስላ
ልሆነ፣ በዚህ አሁን በምሰጣችሁ ትእዛዝ አላ
መሰግናችሁም። 18 ከሁሉ በፊት፣ በማኅበራ
ችሁ በምትሰበሰቡበት ጊዜ በመካከላችሁ መለያ
የት መኖሩን ሰምቻለሁ፤ የሰማሁትም ነገር በከ
ፊል እውነት መሆኑን አምናለሁ። 19 ትክክል
የሆኑት እነማን እንደሆኑ ተለይተው እንዲታ
ወቁ በመካከላችሁ መለያየት መኖሩ ግድ ነው።
20 በአንድነት በምትሰበሰቡበት ጊዜ የምትበሉት
የጌታን ራት አይደለም። 21 ምክንያቱም ስት
በሉ፣ አንዱ ሌላውን ሳይጠብቅ በመሽቀዳደም
ብቻውን ይበላል፤ በዚህ ሁኔታ አንዱ ሲራብ
ሌላው ይሰክራል። 22 እሺ ለመሆኑ የምትበሉበ
ትና የምትጠጡበት ቤት የላችሁምን? ወይስ
የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትንቃላች
ሁን? ወይስ ምንም የሌላቸውን ችግረኞች ታሳ
ፍራላችሁን? እንግዲህ ምን ልበላችሁ? ስለዚህ
ነገር ላመስግናችሁን? ከቶ አላመሰግናችሁም!
23 ከጌታ ኢየሱስ የተቀበልሁትና ለእናንተም
ያስተላለፍሁላችሁ ትምህርት ይህ ነው፤ ጌታ
ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት ሌሊት፣ ኅብስት
አንሥ፤ 24 የምስጋናም ጸሎት አድርጎ ቈረሰ
ውና፣ "እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ለእናንተ የሚ
ሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድር
ጉት" አለ። 25 እንዲሁም ከራት በኋላ ጽዋውን
አንሥቶ "ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን
ነው፤ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰ
ቢያዬ አድርጉት" አለ።
26 ምክንያቱም ይህን ኅብስት በምትበሉበት
ጊዜና ይህንንም ጽዋ በምትጠጡበት ጊዜ ሁሉ
ጌታ ኢየሱስ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ሞቱን
ትናገራላችሁ። 27 ማንም ሰው ያልተገባው ሆኖ
ሳለ የጌታን ኅብስት ቢበላና የጌታንም ጽዋ
ቢጠጣ፣ በጌታ ሥጋና ደም ባለ ዕዳ ይሆናል።
28 ስለዚህ ማንም ሰው ይህን ኅብስት ከመብላ
ቱና ይህንንም ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት ራሱን
መመርመር አለበት። 29 ማንም ሰው የጌታ
ሥጋ ምን መሆኑን ለይቶ ሳያውቅ የጌታን ኅብ
ስት ቢበላና የጌታን ጽዋ ቢጠጣ በራሱ ላይ
ፍርድን ያመጣል። 30 ከእናንተ መካከል ብዙ
ዎች የደከሙትና የታመሙት፣ አንዳንዶችም
የሞቱት በዚሁ ምክንያት ነው። 31 ራሳችንን
ብንመረምር እንዲህ ባልተፈረደብንም ነበር።
32 ነገር ግን በኋላ ከዓለም ጋር እንዳይፈረድብን
ጌታ አሁን ፈርዶ ይቀጣናል።
33 ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ! ለጌታ ራት በም
ትሰበሰቡበት ጊዜ እርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ።
34 በምትሰበሰቡበትም ጊዜ እንዳይፈረድባችሁ፣
ከመካከላችሁ የራበው ሰው ቢኖር በቤቱ
ይብላ። ስለቀረው ነገር እኔ እዚያ ስመጣ ተጨ
ማሪ መመሪያ እሰጣችኋለሁ።

## ምዕራፍ 12
### የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

1 ወንድሞቼ ሆይ! አሁን ደግሞ ስለ መንፈስ
ቅዱስ ስጦታዎች እውነተኛውን ነገር እንድታ
ውቁ እፈልጋለሁ። 2 አረማውያን በነበራችሁበት
ጊዜ በማታውቁት ነገር ተመርታችሁ፣ መናገር
ወደማይችሉ ጣዖቶች ትወሰዱ እንደነበር ታውቃ
ላችሁ። 3 ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ኢየሱ
ስን የሚረግም ማንም የለም፤ እንዲሁም በመን
ፈስ ቅዱስ ተመርቶ ካልሆነ በቀር "ኢየሱስ ጌታ
ነው!" የሚል ማንም እንደሌለ እነግራችኋለሁ።
4 ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች
አሉ፤ መንፈስ ቅዱስ ግን አንድ ነው። 5 ልዩ
ልዩ አገልግሎቶች አሉ፤ ጌታ ግን አንድ ነው።
6 ልዩ ልዩ የሥራ ዐይነቶችም አሉ፤ ነገር ግን
ሁሉንም በሁሉ የሚያከናውን አንዱ እግዚአብ
ሔር ነው። 7 ለእያንዳንዱ መንፈስ ቅዱስን የመ
ግለጥ ስጦታ የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው።
8 መንፈስ ቅዱስ ለአንዱ ሰው በጥበብ የመናገር
ችሎታን ይሰጠዋል፤ ለሌላው ሰው ደግሞ ያው
መንፈስ በዕውቀት የመናገርን ችሎታ ይሰጠ
ዋል፤ 9 ያው አንዱ መንፈስ ለአንዱ እምነትን
ይሰጠዋል፤ ለሌላውም የመፈወስ ስጦታን ይሰ
ጠዋል፤ 10 እንዲሁም ለአንዱ ተአምራትን የማ
ድረግ ኀይልን ይሰጠዋል፤ ለሌላው የትንቢ
ትን[3]* ቃል የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል፤ ለሌ
ላው ደግሞ፣ ስጦታዎች ከመንፈስ ቅዱስ መሆ
ናቸውን ወይም ከርኩሳን መናፍስት መሆናቸ
ውን ለይቶ የማወቅ ችሎታን ይሰጠዋል፤ እንዲ
ሁም ለአንዱ በአዲስ (ባልተለመዱ) ቋንቋዎች
የመናገር ችሎታን ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ
ባልተለመዱ ቋንቋዎች የተነገረውን የመ
ተርጐም ችሎታን ይሰጠዋል፤ 11 ይሁን እንጂ
ይህን ሁሉ የሚያደርገው ያው አንዱ መንፈስ
ነው፤ መንፈስ ቅዱስ እንደ ፍላጐቱ ለእያንዳ
ንዱ ሰው የተለየ ስጦታ ይሰጠዋል።

### በአንድ አካል የተለያዩ የአካል ክፍሎች አሉ

12 አካል ብዙ የአካል ክፍሎች አሉት፤ የአ
ካል ክፍሎች ብዙዎች ሆነው ሳሉ የሚገኙት
በዚያው በአንዱ አካል ነው። እንዲሁም ክርስ
ቶስ ብዙ የአካል ክፍሎች እንዳሉት እንደ
አንድ አካል ነው። 13 ምክንያቱም አይሁዳውያ
ንም ብንሆን፣ ግሪካውያንም ብንሆን፤ ባሪያዎ
ችም ብንሆን፣ ነፃ ሰዎችም ብንሆን፣ አንድ
አካል ለመሆን በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀናል፤
ሁላችንም ከዚሁ ከአንዱ መንፈስ ጠጥተናል።
14 አካል የተሠራው ከብዙ የአካል ክፍሎች
እንጂ ከአንድ የአካል ክፍል ብቻ አይደለም።
15 እግር "እኔ እጅ ስላልሆንሁ የአካል ክፍል
አይደለሁም" ቢል፣ ታዲያ እንዲህ በማለቱ የአ
ካል ክፍል መሆኑ ይቀራልን? 16 ጆሮም "እኔ
ዐይን ስላልሆንሁ የአካል ክፍል አይደለሁም"
ቢል፣ ታዲያ እንዲህ በማለቱ የአካል ክፍል
መሆኑ ይቀራልን? 17 አካል በሙሉ ዐይን ብቻ
ቢሆን ኖሮ፣ የመስማት ሕዋስ የት በሆነ ነበር፤
አካል በሙሉ ጆሮ ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ የማሽተት

---

10፡22 ፦ ዘጸ. 32፡21። 10፡23 ፦ 1ቆሮ. 6፡12። 10፡26 ፦ መዝ. 24፡1። 11፡1 ፦ 1ቆሮ. 4፡16፤ ፊል. 3፡17።
11፡7 ፦ ዘፍ. 1፡26-27። 11፡8-9 ፦ ዘፍ. 2፡18-23።

3* 12፡10 የትንቢት ቃል ፦ የእግዚአብሔርን ቃል መተርጐም ወይም ማብራራት ነው (ሮም 12፡6 ተመልከት)።
11፡25 ፦ ዘጸ. 24፡6-8፤ ኤር. 31፡31-34። 12፡4-11 ፦ ሮም 12፡6-8። 12፡12 ፦ ሮም 12፡4-5።

ሕዋስ የት በሆን ነበር! 18 አሁን ግን እግዚአብ
ሔር እንደፈለገው እያንዳንዱን የአካል ክፍል
በአካል ውስጥ ተገቢ ስፍራውን ይዞ እንዲገኝ
አድርጎታል። 19 አካል የተሠራው ከአንድ የአ
ካል ክፍል ብቻ ቢሆን ኖሮ ሙሉ አካል የት
በተገኘ ነበር! 20 አሁን ግን ብዙ የአካል ክፍ
ሎች ቢኖሩም፥ አካል ግን አንድ ብቻ ነው።
21 ዐይን እጅን “አንተ አታስፈልገኝም!”
ሊለው አይችልም፤ ራስም እግርን “አንተ አታ
ስፈልገኝም!” ሊለው አይችልም፤ 22 እንዲያ
ውም ደካሞች መስለው የሚታዩ የአካል ክፍ
ሎች ይበልጥ አስፈላጊ ናቸው። 23 አነስተኛ
ክብር ያላቸው መስለው ለሚታዩን የአካል ክፍ
ሎች ይበልጥ ክብር እንሰጣቸዋለን፤ የሚያሳ
ፍሩ መስለው የሚታዩንን የአካል ክፍሎች ይበ
ልጥ ክብር ሰጥተን እንጠነቀቅላቸዋለን፤
24 ክብር ላላቸው የአካል ክፍሎች ግን ይህ
ሁሉ አያስፈልጋቸውም፤ እግዚአብሔር ግን
የሚያሳፍሩ መስለው የሚታዩንን የአካል ክፍ
ሎች በበለጠ ክብር እንዲያዙ አድርጎ የአካል
ክፍሎችን አገጣጥሞአል። 25 ይህንንም ያደረ
ገው በአካል ክፍሎች መካከል መለያየት ሳይ
ኖር እርስ በርሳቸው እንዲተሳሰቡ ነው።
26 አንዱ የአካል ክፍል ሲሠቃይ፥ ሌሎችም
የአካል ክፍሎች በሙሉ አብረው ይሠቃያሉ፤
አንዱ የአካል ክፍል ሲከበር ሌሎቹም የአካል
ክፍሎች አብረው ከእርሱ ጋር ይደሰታሉ።
27 እናንተም እኮ የክርስቶስ አካል ናችሁ፤
እያንዳንዳችሁም የአካሉ ክፍሎች ናችሁ።
28 ስለዚህ እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው በቤተ
ክርስቲያን የተለያየ አገልግሎት እንዲኖረው
አድርጎአል፤ በዚህም መሠረት በመጀመሪያ
ሐዋርያትን፥ ሁለተኛ ነቢያትን፥ ሦስተኛ
መምህራንን ሾሞአል። ቀጥሎም ተአምራት
የሚያደርጉትን፥ ቀጥሎም የመፈወስ ስጦታ
ያላቸውን፥ ቀጥሎም ሰዎችን የመርዳት ስጦታ
ያላቸውን፥ ቀጥሎም የማስተዳደር ችሎታ ያላ
ቸውን፥ በመጨረሻም በአዲስ ቋንቋ የመናገር
ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መድቦአል። 29 ነገር
ግን ሁሉም ሐዋርያት አይደሉም፤ ሁሉም ነቢ
ያት አይደሉም፤ ሁሉም መምህራን አይደ
ሉም፤ ሁሉም ተአምራት የሚያደርጉ አይደ
ሉም፤ 30 ሁሉም የመፈወስ ስጦታ የላቸውም፤
ሁሉም በአዲስ ቋንቋ የመናገር ችሎታ የላቸ
ውም፤ ሁሉም በአዲስ ቋንቋ የተነገረውን የመ
ተርጐም ችሎታ የላቸውም። 31 ስለዚህ ከሁ
ሉም የሚበልጡትን ስጦታዎች ለማግኘት
ፈልጉ።
እሁን ደግሞ ከሁሉ የሚበልጠውን መንገድ
እሳያችኋለሁ።

## ምዕራፍ 13
### እውነተኛ ፍቅር

1 በሰዎች ወይም በመላእክት ቋንቋ የመናገር
ችሎታ ቢኖረኝ እንኳ ፍቅር ከሌለኝ እንደሚ
ጮኽ ናስና እንደሚንሿሿ ጸናጽል መሆኔ
ነው። 2 ትንቢት የመናገር ስጦታ ቢኖረኝና ምስ
ጢርንም ሁሉ ብረዳ፥ ዕውቀትም ሁሉ ቢኖረኝ
ተራራን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የሚያዛውር
እምነትም ሁሉ ቢኖረኝ፥ ፍቅር ከሌለኝ ከንቱ
ነኝ። 3 ያለኝን ሁሉ ለድኾች ባካፍል፥ ሥጋ
ዬም እንኳ ሳይቀር በእሳት እንዲቃጠል[4*] አሳ
ልፌ ብሰጥ፥ ፍቅር ከሌለኝ ምንም አይጠቅመ
ኝም።
4 ፍቅር ታጋሽ ነው፤ ፍቅር ደግ ነው፤
ፍቅር አይመቀኝም፤ ፍቅር አይታበይም፤
ፍቅር አይኩራም፤ 5 ፍቅር ሥርዓተቢስ አይደ
ለም፤ ፍቅር የራሱን ጥቅም ብቻ ፈላጊ አይደ
ለም፤ ፍቅር አይበሳጭም፤ ፍቅር ቢበደልም
በደልን እንደ በደል አይቈጥርም፤ 6 ፍቅር እው
ነት በሆነ ነገር ይደሰታል እንጂ ክፋት በሆነ
ነገር አይደሰትም፤ 7 ፍቅር ሁሉን ችሎ ይታገ
ሣል፤ ፍቅር በሁሉም ላይ እምነቱን ይጥላል፤
ፍቅር በሁሉም ላይ ተስፋ ያደርጋል፤ ፍቅር
በሁሉ ነገር ይጸናል።
8 ፍቅር ሁልጊዜ ይኖራል እንጂ አይጠ
ፋም፤ ትንቢትን የመናገር ስጦታም ቢሆን ጊዜ
ያዊ ስለሆነ ይጠፋል፤ በአዲስ ቋንቋ የመናገር
ችሎታ ቢሆን ጊዜያዊ ስለሆነ ይቀራል፤ ዕውቀ
ትም ቢሆን ይጠፋል። 9 ምክንያቱም የምናውቀ
ውም ሆነ ትንቢት የምንናገረው በከፊል ነው።
10 ነገር ግን ፍጹም የሆነው ነገር ሲመጣ ከፊል
የሆነው ነገር ይቀራል።
11 ሕፃን በነበርሁ ጊዜ እንደ ሕፃን እናገር
ነበር፤ እንደ ሕፃን አስብ ነበር፤ እንደ ሕፃን
እመራመር ነበር፤ ሙሉ ሰው በሆንሁ ጊዜ ግን
የሕፃንነቴን ጠባይ ተውሁ። 12 አሁን በመስተ
ዋት እንደምናየው ዐይነት በድንግዝግዝ እናያ
ለን፤ በዚያን ጊዜ ግን በግልጥ እናያለን፤ አሁን
የማውቀው በከፊል ነው፤ በዚያን ጊዜ ግን እግ
ዚአብሔር እኔን የሚያውቀኝን ያህል ሙሉ
ዕውቀት ይኖረኛል።
13 እንግዲህ እምነት፥ ተስፋ፥ ፍቅር፥ እነ
ዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ነገር ግን ከእነ
ዚህ መካከል ብልጫ ያለው ፍቅር ነው።

## ምዕራፍ 14
### የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና ጥቅማቸው

1 እንግዲህ ፍቅርን ተከታተሉ፤ የመንፈስ
ቅዱስ ስጦታዎችን ይልቁንም ትንቢት የመናገር

[4*] 13፥3 በእሳት እንዲቃጠል ፦ አንዳንድ ቅጂዎች “ለትምክሕት” ይላሉ።
12፥28 ፦ ኤፌ. 4፥11። 13፥2 ፦ ማቴ. 17፥20፤ 21፥21፤ ማር. 11፥23።



ስጦታን በብርቱ ፈልጉ። 2 በአዲስ ቋንቋ የሚና
ገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤
ምክንያቱም ምስጢር የሆነውን ነገር በመንፈስ
ቅዱስ ኀይል ስለሚናገር፥ የሚናገረውን ቃል
የሚያውቀው የለም። 3 ትንቢትን የሚናገር ግን
ሌላውን ለማነጽ፥ ለማበረታታት፥ ለማጽናናት
ለሰው ይናገራል። 4 በአዲስ ቋንቋ የሚናገር
ሰው ራሱን ብቻ ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር
ግን ማኅበሩን (ክርስቲያኖችን) ያንጻል።
5 ሁላችሁም በአዲስ ቋንቋ ብትናገሩ በወደ
ድሁ ነበር፤ ይበልጥ የምወደው ግን ትንቢትን
ብትናገሩ ነው፤ ምክንያቱም ማኅበሩ (ክርስቲ
ያን ሁሉ) እንዲታነጽ፥ በአዲስ ቋንቋ የተነገረ
ውን የሚተረጒም ከሌለ፥ በአዲስ ቋንቋ ከሚና
ገር ሰው ይልቅ ትንቢትን የሚናገር ሰው ይበል
ጣል። 6 እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ! ወደ እና
ንተ በምመጣበት ጊዜ በአዲስ ቋንቋ ብናገራ
ችሁ ምን እጠቅማችኋለሁ? ይልቅስ የምጠቅማ
ችሁ የእግዚአብሔርን ምስጢር መግለጥን፥
ዕውቀትን፥ ትንቢት መናገርን፥ ትምህርትን
ይዤላችሁ ብመጣ ነው።
7 እንደ ዋሽንትና እንደ ክራር ያሉት ነፍስ
የሌላቸው የሙዚቃ መሣሪያዎች እንኳ የተለየ
የድምፅ ቅኝት ከሌላቸው፥ የሚሰጡት ድምፅ
ምን መሆኑ እንዴት ይታወቃል? 8 መለከት በአ
ዲስ ድምፅ ቢነፋ፤ ለጦርነት ማን ይዘጋጃል?
9 እንዲሁም እናንተ ግልጥ በሆነ ቋንቋ ካልተና
ገራችሁ፥ የምትናገሩትን ማን ሊያውቀው ይች
ላል? ለነፋስ እንደምትናገሩ ትሆናላችሁ።
10 በዓለም ላይ ብዙ ቋንቋዎች አሉ፤ ትርጒም
የሌለው ቋንቋም የለም። 11 እንግዲህ እኔ የሚነ
ገረውን ቋንቋ ትርጒም የማላውቅ ብሆን ለተና
ጋሪው ሰው እንግዳ እሆናለሁ፤ እርሱም ለእኔ
እንግዳ ይሆናል። 12 እናንተም የመንፈስ ቅዱ
ስን ስጦታዎች በብርቱ ስለምትሹ በይበልጥ
መፈለግ የሚገባችሁ ክርስቲያኖች የሚታነጹባ
ቸው ስጦታዎች እንዲበዙላችሁ ነው።
13 ስለዚህ በአዲስ ቋንቋ የሚናገር ሰው የመ
ተርጐም ችሎታ እንዲኖረው ይጸልይ። 14 ምክ
ንያቱም በአዲስ ቋንቋ ብጸልይ መንፈሴ ይጸል
ያል እንጂ አእምሮዬ ፍሬአልባ ነው። 15 ታዲያ
ምን ማድረግ ይገባኛል? በመንፈሴ እጸልያ
ለሁ፤ በአእምሮዬም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመን
ፈሴ እዘምራለሁ፤ በአእምሮዬም ደግሞ እዘም
ራለሁ። 16 እንዲህማ ካልሆነ፥ አንተ በመንፈስ
እግዚአብሔርን ስታመሰግን፥ አንተ የምትለውን
የማያውቅ እንግዳ ሰው ለምስጋና ጸሎትህ
“አሜን” ሊል እንዴት ይችላል? 17 እርግጥ
አንተ ያቀረብኸው የምስጋና ጸሎት በጥሩ
ሁኔታ ነው፤ ነገር ግን ሌላው ሰው አይጠቀምበ
ትም።
18 እኔ ከሁላችሁ ይበልጥ በአዲስ ቋንቋ ስለ
ምናገር እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። 19 ነገር
ግን በአዲስ ቋንቋ ዐሥር ሺ ቃላት ከምናገር
ይልቅ ሌሎችን ለማስተማር ስል በክርስቲያኖች
መካከል አምስት ቃላትን በሚታወቅ ቋንቋ በአ
እምሮዬ መናገር እወዳለሁ።
20 ወንድሞቼ ሆይ! ለክፉ ነገር ሕፃናት ሁኑ
እንጂ በአስተሳሰባችሁስ እንደ ሕፃናት አት
ሁኑ፤ ይልቁንም በአስተሳሰባችሁ የበሰላችሁ
ሁኑ። 21 ይህም፥
“‘በአዲስ ቋንቋ በሚናገሩ ሰዎችና
በባዕድ ሰዎች አፍ ለዚህ ሕዝብ
እናገራለሁ፤
ይህም ሆኖ አይሰሙኝም’ ይላል ጌታ
እግዚአብሔር”
ተብሎ በሕግ ተጽፎአል።
22 ስለዚህ በአዲስ ቋንቋ መናገር ምልክት
የሚሆነው ለማያምኑ ሰዎች ነው እንጂ ለሚያ
ምኑ ሰዎች አይደለም፤ የትንቢት ቃል መናገር
ግን ምልክት የሚሆነው ለሚያምኑት ሰዎች
እንጂ ለማያምኑ ሰዎች አይደለም።
23 ክርስቲያኖች በሚሰበሰቡበት ጊዜ እያንዳ
ንዱ ክርስቲያን በአዲስ ቋንቋ ቢናገርና የማያ
ውቁ ወይም የማያምኑ ሰዎች ቢመጡ ተናጋሪ
ዎችን “እነዚህ ሰዎች አብደዋል!” አይሉ
ምን? 24 ነገር ግን እያንዳንዱ የትንቢት ቃል
ቢናገርና የማያምን ወይም የማያውቅ ሰው
ቢመጣ በሚሰማው ቃል ሁሉ ይወቀሳል፤ እን
ዲሁም በሚሰማው ቃል ሁሉ ይፈረድበታል።
25 በልቡ የተሰወረው ነገር ይገለጣል፤ በግንባ
ሩም ተደፍቶ “በእርግጥ እግዚአብሔር በመካከ
ላችሁ ነው!” በማለት ለእግዚአብሔር ይሰግ
ዳል።

### በማኅበር ጸሎት ጊዜ ሊኖር የሚገባው ሥነ ሥርዓት

26 ወንድሞቼ ሆይ! እንግዲህ ምን ማድረግ
ይገባል? ለጸሎት በምትሰበሰቡበት ጊዜ ከእና
ንተ አንዱ የመዘመር ስጦታ አለው፤ ሌላው
የማስተማር ስጦታ አለው፥ አንዱ ስውር የሆነ
ውን ነገር የመግለጥ ስጦታ አለው፤ አንዱ በአ
ዲስ ቋንቋ የመናገር ስጦታ አለው፤ ሌላው የመ
ተርጐም ስጦታ አለው። ታዲያ ይህ ሁሉ
ስጦታ ክርስቲያኖችን የሚያንጽ መሆን አለ
በት። 27 በአዲስ ቋንቋ የሚናገሩ ቢኖሩ ሁለት
ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በየተራ ይናገሩ፤ እነ
ርሱ የሚናገሩትንም ሌላ ሰው ይተርጒም።
28 የሚተረጒም ሰው ከሌለ ግን በአዲስ ቋንቋ
የሚናገሩት በስብሰባ ላይ ዝም ይበሉ፤ ለራሳቸ
ውና ለእግዚአብሔር ብቻ ይናገሩ። 29 ትንቢት
የሚናገሩ ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ፤

14፥21 ፦ ኢሳ. 28፥11-12።

ሌሎቹ ግን የተነገረውን አዳምጠው በጥንቃቄ
ያመዛዝኑ ። 30 በስብሰባ ላይ ለሚገኝ ሌላ ሰው
አንዳች ነገር ቢገለጥለት ፤ የመጀመሪያው ተና
ጋሪ ዝም ይበል ። 31 እያንዳንዱ እንዲማርና እን
ዲጽናና ሁላችሁም በየተራ የእግዚአብሔርን
ቃል መናገር ትችላላችሁ ። 32 የነቢያት የትን
ቢት መንፈስ ለነቢያት ይታዘዛል ። 33 ምክንያ
ቱም እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው እንጂ
የሁከት አምላክ አይደለም ።
በእግዚአብሔር ሕዝብ አብያተ ክርስቲያናት
ሁሉ እንደሚደረገው ፥ 34 ሴቶች በጸሎት ስብ
ሰባ ጊዜ ዝም ይበሉ ፤ ምክንያቱም የሙሴ ሕግ
እንደሚያዘው እንዲታዘዙ እንጂ እንዲናገሩ
አልተፈቀደላቸውም ። 35 አንዳንድ ነገርን
ማወቅ ቢፈልጉ ፥ ባሎቻቸውን በቤት ይጠይቁ ፤
ምክንያቱም በጸሎት ስብሰባ ጊዜ ሴት እንድት
ናገር ተገቢ አይደለም ።
36 የእግዚአብሔር ቃል የመጣው ከእናንተ
ነውን? ወይስ የእግዚአብሔር ቃል የደረሰው
ወደ እናንተ ብቻ ነውን? 37 "እኔ ነቢይ ነኝ
ወይም እኔ መንፈሳዊ ስጦታ አለኝ" የሚል
ሰው ቢኖር ፥ ይህ የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ
መሆኑን ይወቅ ። 38 ይህን የማያውቅ ቢኖር ፥
እርሱም አይታወቅ ።
39 ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ! ትንቢት ለመና
ገር በብርቱ ፈልጉ ፤ በአዲስ ቋንቋ መናገርንም
አትከልክሉ ። 40 ነገር ግን ሁሉ ነገር በአግባብና
በሥነ ሥርዓት ይሁን ።

## ምዕራፍ 15

### የክርስቶስ ከሞት መነሣት

1 አሁን ደግሞ ወንድሞቼ ሆይ!
ያበሠርሁላችሁን የምሥራች ቃል ላስታውሳ
ችሁ እፈልጋለሁ ፤ ይህም የምሥራች ቃል እና
ንተ የተቀበላችሁትና ጸንታችሁ የቆማችሁበት
ነው ። 2 እኔ ያበሠርሁላችሁን የምሥራች ቃል
አጥብቃችሁ ብትይዙ ፥ በዚህ የምሥራች ቃል
ትድናላችሁ ፤ አለበለዚያ ግን ያመናችሁት በከ
ንቱ ነው ።
3 እኔ የተቀበልሁትን ፥ በመጀመሪያ ደረጃ
ያለውን ነገር ለእናንተ አስተላለፍሁላችሁ ፤ ያስ
ተላለፍሁላችሁም ነገር "በቅዱሳት መጻሕፍት
እንደተጻፈው ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ፤
4 ተቀበረ ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ
ውም በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሣ" የሚል
ነው ። 5 እንዲሁም ለጴጥሮስ ታየ ፤ ኋላም ለዐ
ሥራ ሁለቱ ታየ ፤ 6 ከአምስት መቶ ለሚበልጡ
ተከታዮቹም በአንድ ጊዜ ታያቸው ፤ ከእነርሱ
አብዛኞቹ እስከ አሁን በሕይወት አሉ ፤ አንዳን
ዶቹ ግን ሞተዋል ። 7 ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ
ታየ ፤ ለሐዋርያትም በሙሉ ታያቸው ።
8 በመጨረሻም እንደ ጭንጋፍ ለሆንሁት
ለእኔ ደግሞ ታየኝ ። 9 እኔ ከሐዋርያት ሁሉ ያነ
ስሁና ሐዋርያም ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ
ነኝ ፤ ምክንያቱም እኔ የእግዚአብሔርን ቤተ
ክርስቲያን ያሳደድሁ ነኝ ። 10 ነገር ግን እኔ
አሁን የሆንሁትን የሆንሁት ፥ በእግዚአብሔር
ጸጋ ነው ፤ የተሰጠኝም ጸጋ ያለ ፍሬ አልቀ
ረም ፤ እንዲያውም ከሌሎቹ ይበልጥ በሥራ
ደክሜአለሁ ፤ ነገር ግን ይህን ያደረገው ከእኔ
ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ
አይደለሁም ። 11 እንግዲህ እኔም ሆንሁ እነርሱ
የምናስተምረው ይህንኑ ነው ፤ እናንተም ያመና
ችሁት ይህንኑ ነው ።

### የሰዎች ከሞት መነሣት

12 ነገር ግን ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ የም
ናስተምር ከሆነ ፥ ከእናንተ አንዳንዶቹ "ከሞት
መነሣት የለም" እንዴት ይላሉ? 13 ከሞት መነ
ሣት ከሌለማ ክርስቶስ ከሞት አልተነሣም
ማለት ነዋ! 14 ክርስቶስ ከሞት ካልተነሣ የእ
ኛም ትምህርት ሆነ የእናንተም እምነት ከንቱ
መሆኑ ነዋ! 15 ደግሞም እግዚአብሔር "ክርስ
ቶስን ከሞት አስነሥቶታል" ብለን በማስተማራ
ችን ሐሰተኞች የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነ
ናል ማለት ነዋ! እንግዲህ የሞቱት ሰዎች
ከሞት ካልተነሡ እግዚአብሔር ክርስቶስንም
ከሞት አላስነሣውም ማለት ነው ። 16 ምክንያ
ቱም የሞቱት ሰዎች ከሞት ካልተነሡ ፥ ክርስ
ቶስም ከሞት አልተነሣም ማለት ነው ። 17 ክር
ስቶስ ከሞት ያልተነሣ ከሆነ ፥ እምነታችሁ
ከንቱ ነዋ! ገና በኃጢአታችሁ እንደጠፋችሁ
ናችሁ ማለት ነዋ! 18 በክርስቶስ አምነው
በሞት ያንቀላፉትም ጠፍተዋል ማለት ነዋ!
19 በክርስቶስ ተስፋ የምናደርገው ለዚህ ዓለም
ሕይወት ብቻ ከሆነ ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የሚ
ታዘንልን መሆናችን ነዋ!
20 ነገር ግን ክርስቶስ ፥ ለሞቱት ከሞት የመ
ነሣት የመጀመሪያ ምሳሌ ሆኖ በእርግጥ ከሞት
ተነሥቶአል ። 21 ሞት የመጣው በአንዱ ሰው
በአዳም ምክንያት እንደሆነ ፥ ከሞት መነሣትም
የሚመጣው በአንዱ ሰው በክርስቶስ ምክንያት
ነው ። 22 በአዳም ምክንያት ሰው ሁሉ እንደሚ
ሞት ፥ እንዲሁም በክርስቶስ ምክንያት ሰው
ሁሉ ሕይወትን ያገኛል ። 23 ይህም የሚሆነው
በየተራ ነው ፤ ክርስቶስ ከሞት የመነሣት የመጀ
መሪያው ምሳሌ ነው ፤ በኋላም ክርስቶስ በሚ
መጣበት ጊዜ የእርሱ የሆኑት ከሞት ይነሣሉ ።

15፥3 ፦ ኢሳ. 53፥5-12 ። 15፥4 ፦ መዝ. 16፥8-10 ፤ ማቴ. 12፥40 ፤ ሐ.ሥ. 2፥24-32 ። 15፥5 ፦ ማቴ. 28፥16-17 ፤
ማር. 16፥14 ፤ ሉቃ. 24፥34 ፥36 ፤ ዮሐ. 20፥19 ። 15፥8 ፦ ሐ.ሥ. 9፥3-6 ። 15፥9 ፦ ሐ.ሥ. 8፥3 ።



24 ቀጥሎም እርሱ ግዛትንና ሥልጣንን ኀይል
ንም ሁሉ አጥፍቶ መንግሥትን ለእግዚአብሔር
አብ በሚያስረክብበት ጊዜ የዓለም ፍጻሜ ይሆ
ናል ። 25 ምክንያቱም ጠላቶቹን ሁሉ በሥል
ጣኑ ሥር እስኪያደርግለት ድረስ ክርስቶስ መን
ገሥ ይገባዋል ። 26 ተሸንፎ በመጨረሻ የሚደ
መሰሰው ጠላት ሞት ነው ። 27 ምክንያቱም
"እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር
አድርጎለታል" የሚል ተጽፎአል ፤ ነገር ግን
"ሁሉ ነገር በሥልጣኑ ሥር ሆኖአል" ሲባል ፥
ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር ያደረገለትን እግዚ
አብሔር አብን አይጨምርም ። 28 ሁሉ ነገር
በክርስቶስ ሥልጣን ሥር ከሆነ በኋላ ፥ እግዚአ
ብሔር አብ በሁሉ ላይ ሥልጣን እንዲኖረው ፥
ወልድ ራሱ ፥ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ ሥር በአ
ደረገለት በእግዚአብሔር አብ ሥልጣን ሥር
ይሆናል ።
29 እንግዲህ የሞቱ ሰዎች የማይነሡ ከሆ
ነማ ፥ ስለ ሞቱ ሰዎች የሚጠመቁ ሁሉ ትርፋ
ቸው ምንድን ነው? የሞቱ ሰዎች ከቶ የማይ
ነሡ ከሆነማ ፥ ሰዎች በእነርሱ ምትክ ስለምን
ይጠመቃሉ? 30 እኛስ ብንሆን በየሰዓቱ ለአደጋ
እየተጋለጥን የምንኖረው ለምንድን ነው?
31 ወንድሞቼ ሆይ! እኔን በየቀኑ ሞት ያጋጥመ
ኛል ፤ ይህንንም የምነግራችሁ በጌታችን በኢየ
ሱስ ክርስቶስ በእናንተ ላይ ያለኝ ትምክሕት
እርግጠኛ ስለሆነ ነው ። 32 በኤፌሶን እንደ አራ
ዊት ከሆኑት ሰዎች ጋር የታገልሁት በሥጋዊ
ምክንያት ከሆነ ትርፌ ምንድን ነው? የሞቱ
ሰዎች ከሞት የማይነሡ ከሆነ "ነገ ስለምን
ሞት ፥ እንብላ ፥ እንጠጣ" እንደተባለው መሆኑ
ነዋ!
33 አትታለሉ ፤ "መጥፎ ጓደኛ ጥሩውን
ጠባይ ያበላሻል ።" 34 ወደ ጽድቅ ሕይወት
ተመለሱ ፤ ኃጢአትንም አትሥሩ ፤ በእናንተ
መካከል እግዚአብሔርን የማያውቁ አንዳንዶች
አሉ ፤ ይህንንም የምለው እንድታፍሩ ብዬ
ነው ።

### ከሞት የተነሣ አካል ሁኔታ

35 አንድ ሰው "የሞቱ ሰዎች የሚነሡት እን
ዴት ነው? ከሞት ሲነሡ የሚኖራቸው አካልስ
ምን ዐይነት ነው?" ብሎ ይጠይቅ ይሆናል ፤
36 አንተ ሞኝ! የምትዘራው እህል ካልሞተ
ሕይወት አይኖረውም ፤ 37 አንተ ስትዘራም
ስንዴ ወይም ሌላ እህል ብቻ ትዘራለህ እንጂ
በኋላ የሚበቅለውን ተክል አይደለም ። 38 እግዚ
አብሔር ግን ለዘሩ እንደፈለገ አካልን ይሰጠ
ዋል ፤ ለእያንዳንዱም ዘር ልዩ ልዩ አካል ይሰ
ጠዋል ።
39 ሥጋ ሁሉ አንድ ዐይነት አይደለም ፤
የሰው ሥጋ አንድ ዐይነት ነው ፤ የእንስሳ ሥጋ
ሌላ ዐይነት ነው ፤ የወፎች ሥጋ ሌላ ዐይነት
ነው ፤ የዓሣ ሥጋ ሌላ ዐይነት ነው ።
40 እንዲሁም ሰማያዊ አካል አለ ፤ ምድራዊ
አካልም አለ ፤ ነገር ግን የሰማያዊው አካል
ክብር አንድ ዐይነት ነው ፤ የምድራዊውም
አካል ክብር ሌላ ዐይነት ነው ። 41 የፀሐይ
ክብር አንድ ዐይነት ነው ፤ የጨረቃ ክብር ሌላ
ዐይነት ነው ፤ የከዋክብትም ክብር ሌላ ዐይነት
ነው ፤ ምክንያቱም አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ
የተለየ ክብር አለው ።
42 ከሞት የሚነሡ ሰዎች ሁኔታ ይህንኑ
ይመስላል ፤ የሚጠፋ ሟች አካል ሆኖ የተዘ
ራው ፥ የማይጠፋ ሕያው አካል ሆኖ ይነሣል ።
43 በውርደት የተዘራው በክብር ይነሣል ፤ ደካማ
ሆኖ የተዘራው ኀይለኛ ሆኖ ይነሣል ፤
44 ሥጋዊ አካል ሆኖ የተዘራው ፥ መንፈሳዊ
አካል ሆኖ ይነሣል ። ሥጋዊ አካል ካለ ፥ መን
ፈሳዊ አካልም አለ ። 45 ስለዚህ "የመጀመሪያው
ሰው አዳም ሕያው ፍጡር ሆነ" ተብሎ ተጽፎ
አል ፤ የመጨረሻው አዳም ክርስቶስ ግን ሕይወ
ትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ ። 46 ነገር ግን በመጀ
መሪያ የመጣው ሥጋዊው ነው እንጂ መንፈሳ
ዊው አይደለም ፤ መንፈሳዊው የመጣው ከሥጋ
ዊው በኋላ ነው ። 47 የመጀመሪያው ሰው አዳም
የተፈጠረው ከመሬት ስለሆነ መሬታዊ ነው ፤
ሁለተኛው ሰው ክርስቶስ የመጣው ከሰማይ
ነው ። 48 ከመሬት የሆኑት ከመሬት እንደተፈጠ
ረው ናቸው ፤ ከሰማይ የሆኑት ፥ ከሰማይ እንደ
መጣው ናቸው ። 49 መሬታዊውን ሰው በመልክ
እንደመሰልነው ፥ ሰማያዊውንም ሰው በመልክ
እንመስለዋለን ።
50 ወንድሞቼ ሆይ! የምነግራችሁ ይህ
ነው ፤ ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት
አይወርሱም ፤ እንዲሁም የሚጠፋው ሟች
አካል ፥ የማይጠፋውን ሕያው አካል አይወር
ስም ።
51 እነሆ አንድ ምስጢር እነግራችኋለሁ ።
ሁላችንም አንሞትም ፤ ነገር ግን ሁላችንም እን
ለወጣለን ። 52 የምንለወጠውም የመጨረሻው
መለከት በሚነፋበት ጊዜ እንደ ዐይን ቅጽበት
በአንድ ጊዜ ነው ። መለከቱ ይነፋል ፤ የሞቱ
ትም ሰዎች የማይጠፉ ሕያዋን ሆነው ይነሣሉ ፤
እኛም እንለወጣለን ፤ 53 ምክንያቱም ይህ የሚጠ
ፋው የማይጠፋውን ፥ ይህም የሚሞተው የማይ
ሞተውን መልበስ አለበት ። 54 ይህ የሚጠፋው
የማይጠፋውን ፥ ይህም የሚሞተው የማይሞተ
ውን በሚለብስበት ጊዜ ፥ "ሞት በድል ተዋጠ"
ተብሎ የተጻፈው ይፈጸማል ። 55 እንዲሁም ፥

15፥25 ፦ መዝ. 110፥1 ። 15፥27 ፦ መዝ. 8፥6 ። 15፥32 ፦ ኢሳ. 22፥13 ። 15፥45 ፦ ዘፍ. 2፥7 ።
15፥51-52 ፦ 1ተሰ. 4፥15-17 ። 15፥54 ፦ ኢሳ. 25፥8 ። 15፥55 ፦ ሆሴዕ 13፥14 ።

"ሞት ሆይ! ድል መንሣትህ የት ነው?
ሞት ሆይ! ሰውን የምትጐዳበት
ኀይል የት ነው?" ተብሎአል።
56 የሞት መንደፊያ ኀይል ኃጢአት ነው፤
የኃጢአትም ኀይል ሕግ ነው። 57 ነገር ግን በጌ
ታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ድል መን
ሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና
ይሁን።
58 ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ!
ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ፤
ለጌታ ሥራ የምትደክሙት በከንቱ አለመሆኑን
ዐውቃችሁ፣ ሳታቋርጡ ዘወትር የጌታን ሥራ
ለመሥራት ትጉ።

## ምዕራፍ 16

### ለኢየሩሳሌም ምእመናን የተሰበሰበ የገንዘብ ዕርዳታ

1 ለምእመናን ስለሚደረገው የገንዘብ መዋጮ
ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት በሰጠሁት መመ
ሪያ መሠረት እናንተም እንዲሁ አድርጉ። 2 እኔ
በምመጣበት ጊዜ የገንዘብ መዋጮ እንዳይደ
ረግ፣ በየሳምንቱ እሑድ ከእናንተ እያንዳንዱ
በሚያገኘው ገቢ መጠን እያዋጣ ለይቶ ያስቀ
ምጥ። 3 እኔ ወደ እናንተ በምመጣበት ጊዜ እና
ንተ የምትመርጥዋቸውን ሰዎች፣ ያዋጣችሁ
ትን ገንዘብ ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄዱ
ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር እልካቸዋለሁ። 4 የእኔም
መሄድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፤ አብረውኝ ይሄ
ዳሉ።

### የጳውሎስ ዕቅዶች

5 በመቄዶንያ በኩል ለመሄድ ስለዐቀድሁ፣
በዚያ ሳልፍ እግረ መንገዴን ወደ እናንተ እመ
ጣለሁ። 6 ወደምሄድበት ወደ ማናቸውም
ስፍራ ለጕዞዬ የሚሆነኝን ዕርዳታ እንድታደር
ጉልኝ ምናልባት እናንተ ዘንድ እቆይ ይሆ
ናል፤ ምናልባትም ክረምቱን ከእናንተ ጋር አሳ
ልፍ ይሆናል፤ 7 አሁን ሳልፍ እግረ መንገዴን
ልጐበኛችሁ አልፈልግም፤ የጌታ ፈቃድ ቢሆን
ጥቂት ረዘም ያለ ጊዜ ከእናንተ ጋር ለመቆየት
ተስፋ አደርጋለሁ።
8 ነገር ግን እስከ ጰንጠቆስጤ በዓል በኤፌሶን
እቆያለሁ። 9 ምክንያቱም ብዙ ሥራ ያለበት
ሰፊ በር ተከፍቶልኛል፤ ተቃዋሚዎች ግን
ብዙዎች ናቸው።

10 ጢሞቴዎስ በሚመጣበት ጊዜ ያለ ሥጋት
ከእናንተ ጋር እንዲቀመጥ እርዱት፤ ምክንያ
ቱም እርሱም እንደ እኔ የጌታ ኢየሱስን ሥራ
ይሠራል። 11 ስለዚህ ማንም እንዳይንቀው እርሱ
ከወንድሞቹ ጋር ወደ እኔ እንዲመጣ ስለምጠብ
ቀው፣ ወደ እኔ በሰላም ተመልሶ እንዲመጣ
ለጕዞው የሚያስፈልገውን በመርዳት ደስ አሰኝ
ታችሁ ሸኙት።
12 ወንድማችን አጵሎስ ከሌሎች ወንድሞች
ጋር ወደ እናንተ እንዲሄድ በጥብቅ ለምኜው
ነበር፤ ነገር ግን እርሱ አሁን ወደ እናንተ ለመ
ምጣት አልፈቀደም፤ ሲመቸው ግን ይመጣል።

### የመጨረሻ ምክርና ሰላምታ

13 ንቁ፤ በእምነት ጸንታችሁ ቁሙ፤ በርቱ፤
ጠንክሩ። 14 የምታደርጉትን ሁሉ በፍቅር አድ
ርጉ።
15 ወንድሞቼ ሆይ! የእስጢፋኖስ ቤተ
ሰዎች በአካይያ አገር የመጀመሪያዎቹ አማኞች
እንደሆኑና የእግዚአብሔርን ሰዎች ለማገልገል
ራሳቸውን አሳልፈው እንደሰጡ ታውቃላችሁ።
16 እንደእነዚህ ላሉት ሰዎችና ከእነርሱም ጋር
በሥራ ለሚደክሙት ሁሉ እንድትታዘዙ አሳስ
ባችኋለሁ።
17 በእስጢፋኖስና በፈርዶናጥስ በአካይቆስም
ወደ እኔ መምጣት ደስ ብሎኛል፤ ምክንያቱም
እናንተ ከእኔ ጋር ባለመገኘታችሁ እነርሱ በእና
ንተ ምትክ የጐደለኝን አሟልተውልኛል።
18 እነርሱ የእኔን መንፈስና የእናንተንም መን
ፈስ አሳርፈዋል፤ ስለዚህ እንደእነዚህ ያሉት
ሰዎች መታወቅ ይገባቸዋል።
19 በእስያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ሰላ
ምታ ያቀርቡላችኋል፤ አቂላና ጵርስቅላ፣ በቤ
ታቸው የሚሰበሰቡ ክርስቲያኖችም ሁሉ ከፍ
ያለ ሰላምታ በጌታ ኢየሱስ ያቀርቡላችኋል።
20 እዚህ ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ሰላምታ ያቀር
ቡላችኋል፤ በወንድማማችነት ፍቅር እየተሳሳማ
ችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ።
21 እኔ ጳውሎስ ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ
ጽፌላችኋለሁ።
22 ጌታ ኢየሱስን የማይወድድ ቢኖር የተረ
ገመ ይሁን! ማራ ናታ! (ጌታችን ሆይ ና!)
23 የጌታ ኢየሱስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።
24 ፍቅሬ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሁላችሁ ጋር
ይሁን፤ አሜን።

16፥1 ፦ ሮም 15፥25-26። 16፥5 ፦ ሐ.ሥ. 19፥21። 16፥8 ፦ ዘሌ. 23፥15-21፤ ዘዳ. 16፥9-11።
16፥8-9 ፦ ሐ.ሥ. 19፥8-10። 16፥10 ፦ 1ቆሮ. 4፥17። 16፥15 ፦ 1ቆሮ. 1፥16። 16፥19 ፦ ሐ.ሥ. 18፥2።

# ሁለተኛው የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

## መግቢያ

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈላቸው ሁለተኛው መልእክት የተጻፈው፣ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበረው ግንኙነት እጅግ አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ ነው፤ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባሎች ከበድ ያሉ ነቀፋዎችን የሰነዘሩበት ቢሆኑም ጳውሎስ እርቅ ለመፍጠር ታላቅ ናፍቆት እንዳለው በማሳየት፣ ይህም በሚሆንበት ጊዜ ታላቅ ደስታ ሊሰማው እንደሚችል ይገልጣል።

በመልእክቱ መጀመሪያ ክፍል ላይ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጋር ስላለው ግንኙነት በመግለጥ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ነቀፋዎችና ተቃውሞዎች ከረር ባለ ሁኔታ ለምን መልስ እንደሰጣቸው ያስረዳል፤ ከዚህም በማያያዝ ይህ የእርሱ ተግሣጽ ወደ ንስሓና ወደ እርቅ የመራቸው በመሆኑ የተሰማውን ደስታ ይገልጥላቸዋል፤ ቀጥሎም በይሁዳ ያሉትን ክርስቲያኖች ለመርዳት በለጋሥነት እንዲሰጡ ያሳስባቸዋል፤ በመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ጳውሎስ በሐዋርያነቱ ላይ ስለቀረበበት ክስ መከላከያ ይሰጣል፤ ምክንያቱም በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ ሰዎች ራሳቸውን እውነተኞች ሐዋርያት በማድረግ "ጳውሎስ ሐሰተኛ ሐዋርያ ነው" በማለት ያንኳስሱት ነበር።

---

## ምዕራፍ 1

1 በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ
ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስና ከወንድማችንም
ከጢሞቴዎስ፣
በቆሮንቶስ ለምትገኘው የእግዚአብሔር ቤተ
ክርስቲያንና እንዲሁም በመላው አካይያ ለሚ
ገኙ ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ፣
2 ከአባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢ
የሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

### ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ያቀረበው ምስጋና

3 የምሕረት አባትና የመጽናናት ሁሉ አም
ላክ ለሆነውና እንዲሁም የጌታችን የኢየሱስ
ክርስቶስ አባት ለሆነው አምላክ* ምስጋና
ይሁን። 4 እኛ ከእግዚአብሔር በምናገኘው
መጽናናት በመከራ ላይ ያሉትን ሁሉ ማጽና
ናት እንድንችል፣ እግዚአብሔር እኛን በመከራ
ችን ሁሉ ያጽናናናል። 5 የክርስቶስን መከራ
በብዛት እንደመካፈላችን መጠን፣ እንዲሁም
በክርስቶስ አማካይነት መጽናናትን በብዛት እና
ገኛለን። 6 እኛ መከራ ስንቀበል እናንተ መጽና
ናትና ደኅንነት ታገኛላችሁ፤ እኛ ስንጽናና
ደግሞ እናንተም እኛ የምንቀበለውን መከራ
በትዕግሥት ተቀብላችሁ ትጽናናላችሁ፤ 7 መከ
ራችንን በምትካፈሉበት መጠን መጽናናታችን
ንም እንደምትካፈሉ ስለምናውቅ በእናንተ ላይ
ያለን ተስፋ ጽኑ ነው።
8 ወንድሞቼ ሆይ! በእስያ ክፍለ ሀገር በነበ
ርንበት ጊዜ የደረሰብንን መከራ እንድታውቁ
እንወዳለን፤ ይህም የደረሰብን መከራ ልንሸከ
መው ከምንችለው በላይ ስለነበር በሕይወት
ለመኖር የነበረን ተስፋ እንኳ ተቋርጦ ነበር።
9 እንዲያውም ሞት እንደተፈረደብን ያህል ተሰ
ምቶን ነበር፤ ይህም ሁሉ የደረሰብን ትምክሕ
ታችን ሙታንን በሚያስነሣ በእግዚአብሔር
እንጂ በራሳችን ኀይል አለመሆኑን እንድንገነ
ዘብ ነው። 10 ስለዚህ እርሱ ለሞት ከሚያደርስ
አደጋ አድኖናል፤ ያድነናልም፤ ደግሞም እንደ
ሚያድነን ተስፋችን በእርሱ ነው። 11 እናንተም
እኛን በጸሎት ልትረዱን ይገባል፤ ምክንያቱም
በብዙ ጸሎት እኛ የእግዚአብሔርን ዕርዳታ ስና
ገኝ፣ ብዙ ሰዎች በእኛ ምክንያት እግዚአብሔ
ርን ያመሰግናሉ።

### የጳውሎስ የጕዞ ዕቅድ መለወጥ

12 የምንመካበት ነገር ይህ ነው፤ ይህም
እውነት መሆኑን ኅሊናችን ይመሰክርልናል፣

1* 1፥3 አዲስ ኪዳን መጀመሪያ በተጻፈበት በግሪክኛው ቋንቋ "የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይመስገን" ይላል።
1፥1 ፦ ሐ.ሥ. 18፥1። 1፥8 ፦ 1ቆሮ. 15፥32።

ከሌሎች ሰዎችና በተለይም ከእናንተ ጋር የነበ
ረን ግንኙነት ከእግዚአብሔር ባገኘነው ቅድስ
ናና ቅንነት ተመርተን ነው ፤ ይህም የሆነው
በእግዚአብሔር ጸጋ ነበር እንጂ በሰው ጥበብ
አልነበረም ። 13 እንብባችሁ ማስተዋል የምትች
ሉትን ነገር ካልሆነ ሌላ ምንም አንጽፍላች
ሁም ፤ 14 አሁን ስለ እኛ በከፊል የምታውቁትን
በኋላ በሙላት እንደምታስተውሉት ተስፋ አደ
ርጋለሁ ፤ በዚህም ምክንያት በጌታ ኢየሱስ ቀን
እኛ በእናንተ እንደምንመካ ፥ እናንተም በእኛ
ትመካላችሁ ።

15 በዚህ ነገር እርግጠኛ ስለነበርሁ ሁለት
ጊዜ እንድትጠቀሙ ብዬ እናንተን በመጀመሪያ
ለመጐብኘት ዐቅጄ ነበር ፤ 16 ልጐበኛችሁ ያቀ
ድሁትም ወደ መቄዶንያ ሳልፍና ከዚያም በም
መለስበት ጊዜ ነበር ፤ በዚህም ሁኔታ ወደ
ይሁዳ በማደርገው ጉዞዬ ትረዱኛላችሁ ብዬ
አስቤ ነበር ። 17 ይህንንም ባቀድሁ ጊዜ የማደር
ገውን የማላውቅ ወላዋይ የሆንሁ ይመስላችኋ
ልን? ወይስ ይህን በማቀዴ በአንድ ጊዜ "አዎ
ንና አይደለም" እያልሁ በማወላወል በሰው አስ
ተሳሰብ ያደረግሁት ይመስላችኋልን? 18 እግዚአ
ብሔር ታማኝ ስለሆነ እኛም የምንነግራችሁ
"አዎንና አይደለም" የሚል የማወላወል ቃል
አይደለም ። 19 ምክንያቱም እኔና ሲላስ ጢሞቴ
ዎስም የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶ
ስን የሰበክንላችሁ "አዎን" በሚል ቃል ብቻ
እንጂ "አዎንና አይደለም" በሚል አወላዋይ
ቃል አልነበረም ። 20 እግዚአብሔር የሰጠን
ተስፋ ሁሉ "አዎን" የሚሆነው በክርስቶስ
ነው ፤ ስለዚህ ነው ፥ ለእግዚአብሔር ክብር በክ
ርስቶስ "አሜን" የምንለው ። 21 እኛንም ሆነ
እናንተን በክርስቶስ እንድንጸና ያደረገን እግዚአ
ብሔር ነው ፤ የቀደሰንም እርሱ ነው ፤ 22 የእ
ርሱ ለመሆናችን ማስረጃ የሚሆን ማኅተሙን
በእኛ ላይ ያደረገና ወደ ፊት ለእኛ ስለሚሰጠን
ሀብት በልባችን መንፈስ ቅዱስን እንደ ዋስትና
አድርጎ የሰጠን እርሱ ነው ።

23 እኔ ወደ ቆሮንቶስ ተመልሼ ያልመጣሁ
በት ምክንያት እናንተን እንዳላሳዝናችሁ ፥ ለእ
ናንተ በመራራት ነው ፤ ለዚሁም እግዚአብሔር
ምስክሬ ነው ፤ 24 እናንተ በእምነታችሁ የጸና
ችሁ ስለሆናችሁ ፥ እናንተን ደስ እንዲላችሁ
አብረናችሁ እንሠራለን እንጂ በእምነታችሁስ
አናዛችሁም ።

## ምዕራፍ 2

1 እንግዲህ እናንተን እንዳላሳዝናችሁ በማ
ሰብ ወደ እናንተ ተመልሼ ላለመምጣት ቍርጥ
ውሳኔ አደረግሁ ። 2 እኔ አሳዝኛችሁ ይሆናል ፤
ታዲያ እኔ ባሳዝናችሁም እንኳ ከእናንተ በቀር
ሌላ ደስ የሚያሰኘኝ ማን ነው? 3 እንደዚያ የጻ
ፍሁላችሁም ወደ እናንተ ስመጣ ደስ ሊያሰ
ኙኝ የሚገባቸው ሰዎች እንዳያሳዝኑኝ ብዬ
ነው ፤ ምክንያቱም የእኔ ደስታ የሁላችሁም
ደስታ መሆኑን ታውቃላችሁ ብዬ አምናለሁ ።
4 በትልቅ ሐዘንና በልብ ጭንቀት ፥ በብዙ እን
ባም ሆኜ የጻፍሁላችሁ ፥ በጣም የምወዳችሁ
መሆኔን እንድታውቁ ብዬ ነው እንጂ ላሳዝና
ችሁ ብዬ አይደለም ።

### ለበደለኛ ይቅርታ ማድረግ

5 ሰውን ያሳዘነ ማንም ቢኖር ያሳዘነው እኔን
ሳይሆን በደሉን ማጋነን አይሁንብኝ እንጂ
በሌላ በኩል ፥ ከእናንተ ብዙዎቹን አሳዝኖ
አል ። 6 ለእንዲህ ዐይነቱ ሰው ከእናንተ አብዛኛ
ዎቹ የፈረዱበት ቅጣት ይበቃዋል ። 7 ስለዚህ
ይህ ሰው በጣም ከማዘኑ የተነሣ ተስፋ እን
ዳይቈርጥ ይልቅስ ይቅርታ እንድታደርጉለትና
እንድታጽናኑት ይገባል ። 8 እንዲሁም እርሱን
የምትወድዱት መሆናችሁን ለማስረዳት እውነ
ተኛ ፍቅራችሁን በሥራ አሳዩት ። 9 ያንንም
መልእክት የጻፍሁላችሁ ተፈትናችሁ በሁሉ
ነገር ታዛዦች መሆናችሁን ለመረዳት ብዬ
ነው ። 10 እናንተ ይቅርታ ለምታደርጉለት
ሰው ፥ እኔም ይቅርታ አደርግለታለሁ ፤ ይቅር
የምልለት በደል ካለ እኔ በክርስቶስ ፊት ይቅ
ርታ የማደርግለት ስለ እናንተ ብዬ ነው ።
11 ይህንንም የማደርገው የሰይጣንን የተንኰል
ሥራ ስለምናውቅ ፥ ሰይጣን እንዳያታልለን ብዬ
ነው ።

### የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ድል አድራጊነት

12 ከዚህ በኋላ የክርስቶስን መልካም ዜና
ለማብሠር ወደ ጢሮአዳ በሄድሁ ጊዜ ጌታ ሰፊ
የአገልግሎት በር ከፍቶልኝ ነበር ፤ 13 ነገር ግን
ወንድሜን ቲቶን ባለማግኘቴ መንፈሴ አላረ
ፈም ፤ ስለዚህ እዚያ ያሉትን ክርስቲያኖች ተሰ
ናብቼ ወደ መቄዶንያ ሄድሁ ።

14 ነገር ግን እኛን ዘወትር በክርስቶስ ድል
አድራጊዎች አድርጎ ለሚመራንና መልካም
መዓዛ እንዳለው ሽቶ ስለ ክርስቶስ ያለንን ዕው
ቀት በየስፍራው ሁሉ እንድናዳርስ ለሚያደር
ገን አምላክ ምስጋና ይሁን ። 15 ምክንያቱም
እኛ ለሚድኑትም ሆነ ለሚጠፉት መልካም
ሽታ እንዳለው ዕጣን በክርስቶስ ለእግዚአብሔር
የቀረብን ነን ። 16 ለሚጠፉት የሚገድል የሞት
ሽታ ነን ፤ ለሚድኑት ግን ሕይወትን የሚሰጥ
የሕይወት መዓዛ ነን ፤ ታዲያ ለዚህ አገልግሎት
ብቁ የሚሆን ማን ነው? 17 እኛ እኮ የእግዚአብ
ሔርን ቃል እንደ ንግድ ዕቃ እንደሚቸረችሩት

1፥16 ፦ ሐ.ሥ. 19፥21 ። 1፥19 ፦ ሐ.ሥ. 18፥5 ። 2፥12-13 ፦ ሐ.ሥ. 20፥1 ።



እንደ ብዙዎቹ አይደለንም ፤ ነገር ግን ከእግዚአ
ብሔር የተላክን የክርስቶስ አገልጋዮች ሆነን
በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት እንናገራለን ።

## ምዕራፍ 3

### የአዲስ ኪዳን አገልጋዮች

1 እንደገና ራሳችንን ልናመሰግን እንጀምራለ
ንን? ወይስ አንዳንዶች እንደሚያደርጉት ለእና
ንተ ወይም ከእናንተ የምስጋና ደብዳቤ ያስፈል
ገን ይሆን? 2 ሰው ሁሉ የሚያያችሁና የሚያነባ
ችሁ የምስጋና መልእክታችን እናንተ ራሳችሁ
ናችሁ ። 3 እናንተስ በእኛ አገልግሎት የመጣ
ችሁ የክርስቶስ መልእክት መሆናችሁ የታወቀ
ነው ፤ ይህም መልእክት የተጻፈው በሕያው እግ
ዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም ፤
እንዲሁም በሰው ልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ
ጽላት የተጻፈ አይደለም ።

4 ይህንን የምንልበት ምክንያት በክርስቶስ
አማካይነት በእግዚአብሔር ዘንድ እምነት ስላ
ለን ነው ። 5 አገልግሎታችንን መፈጸም እንድን
ችል ብቃት የሚሰጠን እግዚአብሔር ነው
እንጂ እኛስ በገዛ ራሳችን ምንም ለማድረግ
ብቃት የለንም ። 6 ፊደልን ሳይሆን መንፈስ
ቅዱስ ያለበትን አዲስ ኪዳንን እንድናገለግል
ያበቃንም እግዚአብሔር ነው ፤ ምክንያቱም
ፊደል ሞትን ያመጣል ፤ መንፈስ ቅዱስ ግን
ሕይወትን ይሰጣል ።

7 ሕግ የተቀረጸው በድንጋይ ጽላት በፊደል
ነበር ፤ ሕግ በተሰጠበትም ጊዜ የእግዚአብሔር
ክብር በማንጸባረቅ ተገልጦአል ፤ ምንም እንኳ
በሙሴ ፊት ላይ ያንጸባርቅ የነበረው ብርሃን
እየተወገደ የሚሄድ ቢሆንም እስራኤላውያን
የሙሴን ፊት ትኵር ብለው ሊመለከቱት አልቻ
ሉም ፤ እንግዲህ ሞትን ያመጣ ሕግ በእንዲህ
ዐይነት ክብር ከተገለጠ ፥ 8 ታዲያ በመንፈስ
ቅዱስ አማካይነት የሚገኘው አገልግሎት እን
ዴት የበለጠ ክብር ይኖረው! 9 ሰዎች የተኰነኑ
በት አገልግሎት ይህን ያህል ክብር ካለው ፥
ሰዎች የሚጸድቁበት አገልግሎትማ እንዴት የበ
ለጠ ክብር ይኖረው! 10 የአሁኑ ታላቅ ክብር
ካለፈው ክብር ጋር ሲወዳደር ፥ ያለፈው ክብር
እንዳልነበር ሆኖ ይቈጠራል ። 11 ያ ጠፊ የነበ
ረው ነገር ይህን ያህል ክብር ከነበረው ፥ ለዘላ
ለም ጸንቶ የሚኖረው ነገርማ የበለጠ ክብር
አለው ማለት ነው ።

12 እንዲህ ዐይነቱ ተስፋ ስላለን ፥ ያለ ፍር
ሃት በድፍረት እንናገራለን ። 13 ሙሴ ፥ የፊቱ
መንጸባረቅ በሚወገድበት ጊዜ እስራኤላውያን
እንዳያዩ ፊቱን ይሸፍን ነበር ፤ እኛ ግን እንደ
እርሱ አናደርግም ። 14 የእነርሱ ልቦና በእርግጥ
ደንዝዞአል ፤ እስከ ዛሬም ድረስ የብሉይ ኪዳንን
መጻሕፍት ሲያነቡ ልቦናቸው በዚያው መሸ
ፈኛ እንደተሸፈነ ነው ። ምክንያቱም ያ መሸ
ፈኛ የሚወገደው በክርስቶስ ብቻ ነው ።
15 ዛሬም እንኳ ቢሆን የሙሴን ሕግ ባነበቡ
ቍጥር ልቦናቸው በመሸፈኛው ይሸፈናል ።
16 ነገር ግን ሰው ወደ ጌታ ሲመለስ "መሸፈ
ኛው ይወገዳል ።" 17 ጌታ መንፈስ ነው ፤ የጌ
ታም መንፈስ ባለበት ነፃነት አለ ። 18 ስለዚህ
ሁላችንም የጌታን ክብር ባልተሸፈነ ፊታችን
እናንጸባርቃለን ፤ መንፈስ ከሆነው ጌታ የሚገ
ኘው ይህ ክብር ፥ በክብር ላይ ክብርን እየጨ
መረ ፥ ልክ ጌታን እንድንመስል ያደርገናል ።

## ምዕራፍ 4

### የጳውሎስ ታማኝነት በአገልግሎቱ

1 እግዚአብሔር በምሕረቱ ይህን አገልግሎት
ስለ ሰጠን ፥ ተስፋ አንቈርጥም ። 2 ስውርና አሳ
ፋሪ የሆነውን ነገር አስወግደናል ፤ በተንኰልም
አንሠራም ፤ የእግዚአብሔርንም ቃል ከውሸት
ጋር አንቀይጥም ፤ ይልቅስ እውነትን በይፋ እና
ሳያለን ፤ ራሳችንንም በሰው ሁሉ ኅሊና ግልጥ
እያደረግን በእግዚአብሔር ፊት እንኖራለን ።
3 ያበሠርነው የምሥራች ቃል ምናልባት የተሰ
ወረ ቢሆንም ፥ የተሰወረው ለሚጠፉት ነው ።
4 እነርሱ የማያምኑበት ምክንያት የዚህ ዓለም
አምላክ የሆነው ሰይጣን ልቦናቸውን ስላሳወ
ረው ነው ፤ በእግዚአብሔር መልክ ስለተገለ
ጠው ስለ ክርስቶስ ክብር ከተነገረው መልካም
ዜና የሚመጣላቸውን ብርሃን እንዳያዩ ያደረጋ
ቸው እርሱ ነው ። 5 እኛ የምናስተምረው ኢየ
ሱስ ክርስቶስ ጌታ መሆኑንና እኛም ራሳችን
በኢየሱስ ምክንያት የእናንተ አገልጋዮች መሆና
ችንን ነው እንጂ ስለ ራሳችንስ አንሰብክም ።
6 ምክንያቱም "ብርሃን በጨለማ ውስጥ
ይብራ!" ብሎ የተናገረ እግዚአብሔር ፥ በክርስ
ቶስ መልክ የሚያበራውን የእግዚአብሔርን
ክብር የማወቅ ብርሃን እንዲሰጠን ብርሃኑን በል
ባችን አብርቶአል ።

7 ነገር ግን ይህ ታላቅ ኀይል የእግዚአብሔር
እንጂ የእኛ አለመሆኑ እንዲታወቅ ፥ ይህን
ክቡር ነገር እንደ ሸክላ ዕቃ ሆነን ይዘነዋል ።
8 በየአቅጣጫው መከራ ይደርስብናል ፤ ግን አን
ሸነፍም ፤ ብዙ ጊዜ ግራ ይገባናል ፥ ግን ተስፋ
አንቈርጥም ፤ 9 ጠላቶች ያሳድዱናል ፥ ግን ወዳ
ጆች አጥተን አናውቅም ፤ ተመትተን እንወድቃ
ለን ፥ ግን አንሞትም ፤ 10 የኢየሱስ ሕይወት
በእኛ ሰውነት እንዲገለጥ ፥ ዘወትር የኢየሱስን
ሞት በሰውነታችን ተሸክመን እንዞራለን ።

3፥3 ፦ ዘጸ. 24፥12 ፤ ኤር. 31፥33 ፤ ሕዝ. 11፥19 ፤ 36፥26 ። 3፥6 ፦ ኤር. 31፥31 ። 3፥7 ፦ ዘጸ. 34፥29 ።
3፥13 ፦ ዘጸ. 34፥33 ። 3፥16 ፦ ዘጸ. 34፥34 ። 4፥6 ፦ ዘፍ. 1፥3 ።

[11]የእርሱ ሕይወት በሚሞተው ሰውነታችን እን
ዲገለጥ ብለን ፣ እኛ አሁን በሕይወት ያለነው
ዘወትር ስለ ኢየሱስ በሞት አደጋ ላይ እንገኛ
ለን ። [12]ስለዚህ እኛ በሞት አደጋ ላይ ስንገኝ ፣
እናንተ በሕይወት ትኖራላችሁ ።
[13]ይሁን እንጂ "አመንሁ ፣ ስለዚህ ተናገ
ርሁ" ተብሎ እንደተጻፈው ፣ እኛም ያው
አንዱ የእምነት መንፈስ ስላለን እናምናለን ፣
ስለዚህ እንናገራለን ። [14]ጌታ ኢየሱስን ከሞት
ያስነሣ አምላክ እኛንም ከኢየሱስ ጋር እንደሚ
ያስነሣንና ከእናንተም ጋር በፊቱ እንደሚያቀር
በን እናውቃለን ። [15]ይህ ሁሉ ለእናንተ ጥቅም
የሆነው ጸጋ ተትረፍርፎ ለብዙ ሰዎች በደረሰ
መጠን ፣ ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆነውን
ምስጋና እንዲያበዛ ነው ።

### በእምነት መኖር

[16]ስለዚህ ተስፋ አንቈርጥም ፤ ምንም እንኳ
ውጫዊው ሰውነታችን ቢጠፋ ፣ ውስጣዊው
ሰውነታችን በየቀኑ ይታደሳል ። [17]ይህም ቀላ
ልና ጊዜያዊ የሆነ መከራችን ፣ ወደር የሌለውን
እጅግ ታላቅ የሆነ ዘላለማዊ ክብር ያስገኝል
ናል ። [18]እኛ የምንመለከተው የማይታየውን
ነገር እንጂ የሚታየውን አይደለም ፤ ምክንያ
ቱም የሚታየው ነገር ጊዜያዊ ነው ፤ የማይታ
የው ግን ዘላለማዊ ነው ።

## ምዕራፍ 5

[1]ይህ እንደ ድንኳን ጊዜያዊ የሆነው ሥጋ
ችን ሲፈርስ በሰው እጅ ሳይሆን በእግዚአብሔር
የታነጸ ዘላለማዊ መኖሪያ በሰማይ እንዳለን እና
ውቃለን ። [2]በሰማይ ወዳለው መኖሪያችን ለመግ
ባት በመመኘት እንቃትታለን ፤ [3]ወደዚያም
ወደ መኖሪያችን በምንገባበት ጊዜ ራቁታችንን
አንገኝም ። [4]በዚህ ድንኳን በሆነው ሥጋችን
ውስጥ ስንኖር ከብዶን እንቃትታለን ፤ የምንቃ
ትተውም ሞት በሕይወት እንዲለወጥ ወደ ሰማ
ያዊው መኖሪያችን ለመግባት ፈልገን ነው
እንጂ ከዚህ ከምድራዊ ሥጋችን ለመለየት በመ
ፈለግ ብቻ አይደለም ። [5]ለዚህም ለውጥ ያዘጋ
ጀን እግዚአብሔር ነው ፤ በኋላ ለሚሰጠን ነገር
ሁሉ መያዣ እንዲሆን መንፈሱን የሰጠንም
እርሱ ነው ።
[6]እንደ መኖሪያችን በሆነው ሥጋችን እስካ
ለን ድረስ ፤ ከጌታ ርቀን መኖራችንን እናውቃ
ለን ፤ ስለዚህም ዘወትር ያለ ፍርሃት በመተማ
መን እንኖራለን ። [7]የምንኖረውም በእምነት
እንጂ በማየት አይደለም ። [8]ከዚህ እንደ መኖሪ
ያችን ከሆነው ሥጋችን ተለይተን ከጌታ ጋር
መሆን እንመኛለን ፤ ስለዚህ ያለ ፍርሃት በመተ
ማመን እንኖራለን ። [9]ከዚህ ከሥጋችን ጋር ብን
ሆንም ወይም ከእርሱ ብንለይም ዓላማችን
ጌታን ማስደሰት ነው ። [10]ምክንያቱም እያንዳ
ንዱ በሥጋው ሳደረገው ክፉም ሆነ ደግ ነገር
እንደየሥራው ብድራቱን ለመቀበል ፣ ሁላች
ንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት መቅረብ
አለብን ።

### በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን

[11]እግዚአብሔርን መፍራት ምን መሆኑን
ስለምናውቅ ፣ ሰዎችን እናስረዳለን ፤ እኛ ምን
መሆናችንንም እግዚአብሔር ያውቃል ፤ እናን
ተም በልቦናችሁ ምን መሆናችንን እንደምታ
ውቁ ተስፋ አደርጋለሁ ። [12]በልብ ባለው ነገር
ሳይሆን በውጭ በሚታየው ነገር ለሚመኩት
መልስ እንድትሰጡ ፣ በእኛ እንድትመኩ ለእና
ንተ ምክንያት እንሆናለን እንጂ እንደገና የእ
ኛን ማንነት ልናስረዳ አንጀምርም ። [13]እብዶች
ብንሆን ለእግዚአብሔር ስንል ነው ፤ ባለ አእም
ሮዎች ብንሆንም ለእናንተ ስንል ነው ።
[14]አንድ ጊዜ ክርስቶስ ለሁሉም መሞቱንና
ሁሉም የእርሱ ሞት ተካፋዮች መሆናቸውን
ስለተረዳን ፣ የክርስቶስ ፍቅር ለሥራ ይገፋፋ
ናል ። [15]በሕይወት ያሉት ሁሉ ፣ ለእነርሱ
ለሞተውና ከሞትም ለተነሣው እንዲኖሩ እንጂ
ከእንግዲህ ወዲህ ለራሳቸው ሲሉ እንዳይኖሩ
ክርስቶስ ለሁሉም ሞተ ።
[16]ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ማንንም ቢሆን
በሥጋዊ አመለካከት አናይም ፤ ከዚህ በፊት ክር
ስቶስን ያየነው በሥጋዊ አመለካከት ቢሆንም
እንኳ ፤ ከእንግዲህ ወዲህ የምንመለከተው በዚህ
ዐይነት አይደለም ። [17]ስለዚህ ማንም ከክርስቶስ
ጋር ቢተባበር አዲስ ፍጥረት ነው ፤ አሮጌው
ፍጥረት አልፎአል ፤ በእርሱም ስፍራ አዲስ
ፍጥረት ተተክቶአል ። [18]ይህም ሁሉ የሆነው
እኛን ከራሱ ጋር በክርስቶስ አማካይነት ባስታረ
ቀንና የማስታረቅንም አገልግሎት በሰጠን በእግ
ዚአብሔር ነው ። [19]ይህም እግዚአብሔር በክር
ስቶስ አማካይነት ሰዎችን ሁሉ ከራሱ ጋር አስ
ታረቀ ማለት ነው ፤ በደላቸውንም አልቈጠረባ
ቸውም ፤ ለእኛም የማስታረቂያ ቃል ሰጠን ።
[20]እግዚአብሔር ሰዎችን በእኛ አማካይነት
ስለሚጠራ ፣ እኛ በክርስቶስ ስም አምባሳደሮች
ነን ፤ ስለዚህ "ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ"
ብለን በክርስቶስ ስም እንለምናችኋለን ። [21]እኛ
ከክርስቶስ ጋር በመተባበር የእግዚአብሔር
ጽድቅ እንድንሆን ፣ እግዚአብሔር ኃጢአት
የሌለበትን ክርስቶስን የእኛን ኃጢአት እንዲሸ
ከም አደረገው ።

4:13 ፡- መዝ. 116፡10 ። 5:10 ፡- ሮም 14፡10 ።



## ምዕራፍ 6

[1]ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ እን
ደመሆናችን መጠን "የተቀበላችሁትን ጸጋ በከ
ንቱ አታስቀሩት" ብለን እንለምናችኋለን ።
[2]እግዚአብሔር ፤
"በመረጥሁት ሰዓት ሰማሁህ ፤
በደኅንነትም ቀን ረዳሁህ" ስለሚል ፣
"እነሆ የተመረጠው ሰዓት አሁን ነው ፤
የደኅንነትም ቀን አሁን ነው ።"
[3]አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ በምንም ነገር
ለማንም መሰናከያ አንሆንም ። [4]ይልቅስ መከራ
ንና ችግርን ጭንቀትንም እየታገሥን ፣ የእግዚአ
ብሔር አገልጋዮች መሆናችንን በሁሉ በኩል
እንገልጣለን ። [5]የእግዚአብሔር አገልጋዮች
መሆናችንን የምንገልጠውም በመገረፍ ፣ በመታ
ሰር ፤ በመታወክ ፣ በሥራ በመድከም ፤ እንቅ
ልፍ በማጣትና በመራብ ነው ፤ [6]እንዲሁም በን
ጽሕና ፣ በዕውቀት ፣ በትዕግሥት ፣ በደግነት ፣
በመንፈስ ቅዱስና ግብዝነት በሌለበት ፍቅር ፣
[7]በእውነት ቃልና በእግዚአብሔር ኀይል አገል
ግሎታችንን እንገልጣለን ፤ የማጥቂያም ሆነ
የመከላከያ መሣሪያችንም ጽድቅ ነው ፤ [8]ለክ
ብር ወይም ለውርደት ለመወቀስ ወይም ለመ
መስገን የተዘጋጀን ነን ፤ እውነተኞች ስንሆን
አታላዮች ተብለን ፣ [9]ዝነኞች ስንሆን እንዳልታ
ወቅን ሆነን ፣ ሞተዋል ስንባል ሕያው ሆነን
እንገኛለን ፤ የተደበደብን ስንሆን አልተገደል
ንም ፤ [10]ሐዘን ቢደርስብንም ዘወትር እንደሰታ
ለን ፤ ድኾች ሆነን ሳለ ፣ ብዙዎችን ሀብታሞች
እናደርጋለን ፤ ምንም የሌለን ስንሆን ፣ ሁሉ
የእኛ ነው ።
[11]እናንተ በቆሮንቶስ የምትኖሩ ሰዎች
ሆይ! እነሆ በግልጥ ተናግረናችኋል ፤ ልባችን
ንም በሰፊው ከፍተንላችኋል ። [12]እናንተ ልባች
ሁን አጠበባችሁብን እንጂ እኛስ ልባችንን አላ
ጠበብንባችሁም ። [13]ልጆቼ እንደመሆናችሁ
መጠን "እኛ ልባችንን በሰፊው ከፍተን ስሜታ
ችንን እንደገለጥንላችሁ ፣ እናንተም ልባችሁን
ከፍታችሁ ስሜታችሁን ግለጡልን" እላችኋ
ለሁ ።

### ከማያምኑ ሰዎች ጋር አለመተባበር

[14]በማይመች ሁኔታ ከማያምኑ ሰዎች ጋር
አትጣመሩ ፤ ጽድቅና ኃጢአት እንዴት ሊተባ
በሩ ይችላሉ? ብርሃንና ጨለማ እንዴት አብ
ረው ሊኖሩ ይችላሉ? [15]ክርስቶስና ዲያብሎስ[a*]
እንዴት ሊስማሙ ይችላሉ? የሚያምንና የማያ
ምንስ በምን ሊተባበሩ ይችላሉ? [16]የእግዚአብ
ሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖት ጋር ምን ስምምነት
አለው? እግዚአብሔርም ፤
"መኖሪያዬን በሕዝቤ መካከል
አደርጋለሁ ፤
ከእነርሱም ጋር እመላለሳለሁ ፤
እኔ አምላካቸው እሆናለሁ ፤
እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ"
ብሎ እንደተናገረው እኛ የሕያው እግዚአብ
ሔር ቤተ መቅደስ ነን ። [17]ደግሞም እግዚአብ
ሔር እንዲህ ብሎአል ፤
"ከእነርሱ መካከል ተለይታችሁ ውጡ ፤
ርኩስ የሆነውንም ነገር አትንኩ ፤
እኔም እቀበላችኋለሁ ፤
[18]እኔ አባታችሁ እሆናለሁ ፤
እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆቼ
ትሆናላችሁ ፤
ይላል ኀያሉ እግዚአብሔር ።"

## ምዕራፍ 7

[1]እንግዲህ ወዳጆቼ ሆይ! ይህ ሁሉ ተስፋ
የተሰጠው ለእኛ ስለሆነ ሥጋንና መንፈስን ከሚ
ያረክስ ከማናቸውም ነገር ራሳችንን እናንጻ ፤
እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችን
ፍጹም እንዲሆን እናድርግ ።

### የጳውሎስ ደስታ

[2]ልባችሁን በሰፊው ከፍታችሁ ስፍራ
ስጡን ፤ ማንንም አልበደልንም ፤ ማንንም
አልጐዳንም ፤ ማንንም አልበዘበዝንም ። [3]ይህን
ንም የምለው እናንተን ልወቅሳችሁ ብዬ አይደ
ለም ፤ ምክንያቱም ከዚህ በፊት እንዳልናችሁ
ልባችንን በሰፊው ከፍተንላችኋል ፤ በሕይወትም
ሆነ በሞት ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነን ። [4]በእና
ንተ ላይ ያለኝ መተማመን ትልቅ ነው ፤ በእና
ንተ ላይ ያለኝ ትምክሕት ትልቅ ነው ፤ በመከ
ራችን ሁሉ እጽናናለሁ ፤ ለደስታዬም ወሰን የለ
ውም ።
[5]መቄዶንያ በደረስን ጊዜ እንኳ ከብዙ አቅ
ጣጫ ችግር ደረሰብን እንጂ ምንም ዕረፍት አላ
ገኘንም ፤ በውጭ ጠብ ፤ በውስጥም ፍርሃት ነበ
ረብን ። [6]ነገር ግን ሐዘንተኞችን የሚያጽናና
አምላክ በቲቶ መምጣት አጽናናን ። [7]የተጽናና
ነውም በእርሱ መምጣት ብቻ ሳይሆን ፣ እና
ንተ እርሱን ያጽናናችሁት መሆኑን በመስማታ
ችንም ጭምር ነው ፤ ስለ እኔ ያላችሁን ናፍቆ
ትና ሐዘን ጭንቀትም በነገረን ጊዜ ይበልጥ ደስ
አለኝ ።
[8]ምንም እንኳ ከዚህ በፊት የጻፍሁላችሁ
መልእክት ያሳዘናችሁ ቢሆንም መልእክቱን

[a*] 6፡15 ዲያብሎስ ፡- በግሪክ "ቤልያር" በዕብራይስጥ "በሊየዐል" ይባላል ።
6፡2 ፡- ኢሳ. 49፡8 ። 6፡5 ፡- ሐ.ሥ. 16፡23 ። 6፡16 ፡- ዘሌ. 26፡12 ፤ ሕዝ. 37፡27 ፤ 1ቆሮ. 3፡16 ፤ 6፡19 ።
6፡17 ፡- ኢሳ. 52፡11 ። 6፡18 ፡- 2ሳሙ. 7፡14 ፤ 1ዜ.መ. 17፡13 ፤ ኢሳ. 43፡6 ፤ ኤር. 31፡9 ። 7፡5 ፡- 2ቆሮ. 2፡13 ።

በመጻፌ እልጸጸትም ፤ ተጸጽቼም ብሆን
እንኳ ፥ የተጸጸትሁት መልእክቴ ለጥቂት ጊዜ
ስላሳዘናችሁ ነው ። 9አሁን ግን ደስ ብሎኛል ፤
የተደሰትሁበትም ምክንያት እናንተን ስላሳዘንሁ
አችሁ ሳይሆን በሐዘናችሁ ምክንያት ንስሓ ገብ
ታችሁ በመለወጣችሁ ነው ፤ እንግዲህ ሐዘና
ችሁ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለሆነ እኛ
ምንም አልበደልናችሁም ማለት ነው ። 10እንደ
እግዚአብሔር ፈቃድ የሚሆን ሐዘን ወደ ደኅን
ነት የሚያመጣ በንስሓ የሚገኘውን ለውጥ ስለ
ሚያስገኝ ጸጸት የለበትም ፤ የዓለም ሐዘን ግን
ሞትን ያመጣል ። 11ይህ እንደ እግዚአብሔር
ፈቃድ የሆነው ሐዘን በትጋት እንድታስቡና ከበ
ደል ንጹሕ መሆናችሁን እንድታረጋግጡ አድር
ጎአችኋል ፤ እንዲሁም በኃጢአት ላይ ቍጣች
ሁን እንድትገልጡ ፥ ተግሣጼን እንድትፈሩ ፤
እኔን እንድትናፍቁ ፥ በመንፈሳዊ ቅንአት በትክ
ክል እንድትፈርዱና በደለኛውንም እንድትቀጡ
አድርጎአችኋል ፤ በሁሉ በኩል በዚህ ነገር ንጹ
ሐን መሆናችሁን አስረድታችኋል ።

12እንግዲህ እኔ የጻፍሁላችሁ ስለ እኛ ያላ
ችሁ ትጋት በእግዚአብሔር ፊት ለእናንተ
ግልጥ እንዲሆን ብዬ ነው እንጂ በደል ስለ ሠራ
ውና በደል ስለተፈጸመበት ሰው ብዬ አይደ
ለም ። 13የተጽናናነውም በዚሁ ምክንያት
ነው ።

ከመጽናናታችንም በላይ በቲቶ ደስታ ምክን
ያት ይበልጥ ተደስተናል ፤ ምክንያቱም ሁላች
ሁም ቲቶን ስላጽናናችሁትና መንፈሱንም ስላሳ
ረፋችሁት ነው ። 14በእናንተ የነበረኝን ትምክ
ሕት ለቲቶ ነግሬው ነበር ፤ እናንተም አላሳፈራ
ችሁኝም ፤ ሁልጊዜ እውነትን እንነግራችሁ
ነበር ፤ ይህም ስለ እናንተ ለቲቶ የነገርነው
ትምክሕት እውነት በመሆኑ ተረጋግጦአል ።
15ሁላችሁም ታዛዦች እንደ ሆናችሁና በፍርሃ
ትና በመንቀጥቀጥም እንደተቀበላችሁት ቲቶ
ሲያስታውስ ፥ ለእናንተ ያለው ፍቅር በጣም
የበዛ ሆኖአል ። 16እኔም በሁሉ መንገድ በእና
ንተ ለመተማመን በመቻሌ ይበልጥ ደስ ብሎ
ኛል ።

## ምዕራፍ 8

### የክርስቲያኖች ልግስና

1ወንድሞቼ ሆይ! እግዚአብሔር በመቄዶ
ንያ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት የሰጠውን ጸጋ
እንድታውቁ እንወዳለን ። 2እነርሱ ብዙ መከ
ራና ፈተና ደርሶባቸዋል ፤ ይሁን እንጂ ደስታ
ቸው ታላቅ ስለሆነ ምንም እንኳ በጣም ድኾች
ቢሆኑ ከፍ ያለ ልግስና አድርገዋል ። 3የሚቻላ
ቸውን ያህል ብቻ ሳይሆን ከሚቻላቸውም በላይ
በፈቃደኛነት እንደሰጡ እኔ እመሰክርላቸዋ
ለሁ ፤ 4በይሁዳ ያሉትን ክርስቲያኖች የመር
ዳት ዕድል እንዳይነፈጋቸውም አጥብቀው ለመ
ኑን ፤ 5እነርሱ ያደረጉት እኛ ከጠበቅነው በላይ
ነው ፤ በመጀመሪያ ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ ፤
ቀጥሎም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን
ለእኛ ሰጥተዋል ። 6ይህን ሥራ አስቀድሞ የጀ
መረው ቲቶ ስለነበረ አሁንም ይህንኑ የልግስና
ሥራችሁን ወደ ፍጻሜ እንዲያደርስ እርሱኑ
ለምነነዋል ። 7እናንተ በእምነትም ሆነ ፥ በንግ
ግርም ሆነ ፥ በዕውቀትም ሆነ ፥ ሰውን ለመር
ዳት ባላችሁ ትጋትም ሆነ ፥ ለእኛ ባላችሁ ፍቅ
ርም ሆነ ፥ በሁሉ ነገር ትበልጣላችሁ ፤ በዚህ
በልግስና ሥራም እንድትበልጡ ይሁን ።

8ታዲያ ይህን የምላችሁ በማዘዝ አይደለም ፤
ነገር ግን የሌሎችን የመስጠት ትጋት ከእናንተ
ትጋት ጋር በማወዳደር የእናንተን ፍቅር እውነ
ተኛነት ለማወቅ ብዬ ነው ። 9እናንተ የጌታች
ንን የኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅ ልግስና ታውቃላ
ችሁ ፤ እርሱ ምንም እንኳ ሀብታም ቢሆን ፥
በእርሱ ድኽ መሆን እናንተ ሀብታሞች እንድት
ሆኑ ስለ እናንተ ብሎ ድኻ ሆነ ።

10በዚህ ጉዳይ ለእናንተ መልካም መስሎ
የታየኝን ምክር እሰጣችኋለሁ ፤ ባለፈው
ዓመት ፥ ለመስጠት ብቻ ሳይሆን ይህን ለማድ
ረግ በመጀመሪያ የፈለጋችሁት እናንተ ነበራ
ችሁ ። 11ስለዚህ የመስጠት ፈቃደኛነታችሁ
አሳብ በሥራ ላይ ውሎ ወደ ፍጻሜ እንዲደርስ
ባላችሁ መጠን ያንን ያሰባችሁትን አሁን አድ
ርጉ ። 12ለመስጠት መልካም ፈቃድ ካለ ፥
የሰው ልግስና ተቀባይነት የሚያገኘው ፤ ባለው
መጠን ሲሰጥ እንጂ በሌለው መጠን ሲሰጥ አይ
ደለም ።

13ይህንንም ስል ሁላችሁም እኩል እንድት
ሆኑ እንጂ እናንተ በመስጠት ስትቸገሩ ሌሎች
እንዲያርፉ ብዬ አይደለም ። 14እናንተ በምትቸ
ገሩበት ጊዜ የእነርሱ ሀብት ለእናንተ ችግር እን
ዲውል ፥ አሁን የእናንተ ሀብት ለእነርሱ ችግር
ይዋል ፤ በዚህ ዐይነት በመካከላችሁ እኩልነት
ይኖራል ። 15ይህም ፥

“ብዙ የሰበሰበ አልተረፈለትም ፤
ትንሽ የሰበሰበም አልጐደለበትም”
ተብሎ እንደተጻፈው ነው ።

### ቲቶና ጓደኞቹ

16እኔ ለእናንተ የማስበውን ያህል ቲቶም
ለእናንተ እንዲያስብ ያደረገ አምላክ ይመስገን ።
17ቲቶ ወደ እናንተ የሚመጣው በራሱ ፈቃድ
ተነሣሥቶ በደስታ ነው እንጂ እኛ ስለለመን
ነው ብቻ አይደለም ። 18በወንጌል ስብከቱ በአ
ብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰገነውን ወን
ድም ከእርሱ ጋር እንልካለን ። 19ከዚህም





በላይ ይህ ወንድም እኛ ይህን በጎ ሥራ ለጌታ
ክብር ስንፈጽምና ለማገልገል ያለንንም መል
ካም ፈቃድ ስንገልጥ አብሮን በመሄድ የሥራ
ተካፋያችን እንዲሆን በአብያተ ክርስቲያናት
የተመረጠ ነው ።

20ይህን በልግስና የተሰጠውን ገንዘብ ስናስተ
ዳድር ምንም ዐይነት ነቀፌታ እንዳይደርስብን
እንጠነቀቃለን ። 21ምክንያቱም ዓላማችን በጌታ
ፊት ብቻ ሳይሆን በሰዎችም ፊት መልካም የሆ
ነውን ነገር ማድረግ ነው ።

22ብዙ ጊዜ በብዙ መንገድ ተፈትኖ ትጉህ
ሆኖ የተገኘውን ወንድማችንን ከነቲቶ ጋር የላ
ክነውም በዚሁ ምክንያት ነው ፤ እርሱ በእና
ንተ ላይ ያለው እምነት ትልቅ ስለሆነ አሁን
እናንተን ለመርዳት ያለው ትጋት ከምንጊዜ
ውም የበለጠ ነው ። 23ስለ ቲቶ ማወቅ ቢያስፈ
ልግ ፥ እናንተን ለመርዳት አብሮኝ የሚሠራ
የሥራ ጓደኛዬ ነው ፤ ከእርሱ ጋር ስለሚመ
ጡት ስለ ሌሎች ወንድሞች የሆነ እንደሆነ ፤
የአብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ፥ የክርስቶስ
ክብር ናቸው ። 24ስለዚህ ፍቅራችሁን ግለጡላ
ቸው ፤ በዚህ ዐይነት ፍቅራችሁንና በእናንተ ላይ
ያለን ትምክሕት ከንቱ አለመሆኑን ለአብያተ
ክርስቲያናት ሁሉ ታሳያላችሁ ።

## ምዕራፍ 9

### ለክርስቲያኖች የተደረገ መዋጮ

1በይሁዳ ላሉት ክርስቲያኖች ስለሚደረገው
መዋጮ ልጽፍላችሁ አያስፈልግም ፤ 2እናንተ
በአካይያ ያላችሁ ሰዎች ለመርዳት ያላችሁን
በጎ ፈቃድ በማወቄ “የአካይያ ሰዎች ከአምና
ጀምሮ ለመርዳት ዝግጁዎች ናቸው” ብዬ ለመ
ቄዶንያ ሰዎች በትምክሕት ተናግሬአለሁ ፤ እን
ዲያውም እናንተን ለመርዳት ያላቸው ፍላጎት
አብዛኞቻቸውም እንዲረዱ አድርጎአቸዋል ።
3በዚህ ነገር በእናንተ ላይ ያለን ትምክሕት
ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር እነዚህን ወንድሞች እል
ካለሁ ፤ እናንተም ልክ እኔ ከዚህ በፊት እንዳል
ኩት ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ ። 4የመቄዶንያ
ሰዎች ከእኔ ጋር ወደ እናንተ መጥተው ያልተዘ
ጋጃችሁ ሆናችሁ ቢያገኙዋችሁ በእናንተ በመ
መካታችን እናፍራለን ፤ እናንተማ በጣም ታፍ
ራላችሁ ። 5ስለዚህ ልትሰጡ ቃል የገባችሁበ
ትን በቅድሚያ እንድታዘጋጁ እንዲያስታውሱአ
ችሁ በማለት እነዚህ ወንድሞች ከእኔ ቀድመው
ወደ እናንተ እንዲመጡ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ
አግኝቼዋለሁ ፤ በዚህ ዐይነት እኔ በምመጣበት
ጊዜ ስጦታችሁ ዝግጁ ይሆናል ፤ እናንተም የም
ትሰጡት በግድ ሳይሆን በፈቃደኛነት መሆኑን
ያሳያል ።

6“ጥቂት የዘራ ፥ ጥቂት መከር ይሰበስባል ፤
ብዙ የዘራ ብዙ መከር ይሰበስባል” የሚለውን
ቃል አስታውሱ ። 7ስለዚህ እግዚአብሔር የሚ
ወድደው በደስታ የሚሰጠውን ሰው ስለሆነ እያ
ንዳንዱ ለመስጠት የፈለገውን በልቡ ፈቅዶ በደ
ስታ ይስጥ እንጂ እየተጸጸተ ወይም በግዴታ
አይስጥ ። 8ሁልጊዜ በሁሉ ነገር የሚበቃችሁን
አግኝታችሁ ለመልካም ሥራ ሁሉ የምታው
ሉት እንዲተርፋችሁ እግዚአብሔር በብዛት በረ
ከቱን ሊሰጣችሁ ይችላል ። 9ይህም ፥

“ለድኾች በልግስና ሰጠ ፤
ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል”
ተብሎ እንደተጻፈው ነው ።

10ለዘሪ ዘርን ፥ ለምግብ እንጀራን የሚሰጥ
አምላክ የምትዘሩትን ዘር አበርክቶ ይሰ
ጣችኋል ፤ የልግስናችሁንም ፍሬ ያበዛላችኋል ።
11ልግስናችሁ በእኛ አማካይነት የሚደርሳቸው
ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ ፥
ሁልጊዜ እንድትለግሱ እግዚአብሔር በሁሉ
ነገር ያበለጽጋችኋል ። 12ይህ የምትፈጽሙት
የልግስና አገልግሎት የክርስቲያኖችን ችግር
ከማስወገዱም በላይ ሰዎች ለእግዚአብሔር ብዙ
ምስጋና እንዲያቀርቡ ያደርጋቸዋል ። 13ይህ
የእናንተ የልግስና አገልግሎት ፥ እናንተ የክርስ
ቶስን ወንጌል ተቀብላችሁ ታማኞች መሆናችሁ
ንና ለእነርሱና ለሌሎችም መለገሳችሁን የሚያ
ስረዳ ስለሆነ ሁሉም እግዚአብሔርን ያመሰግ
ናሉ ። 14እነርሱም እግዚአብሔር ለእናንተ በሰ
ጣችሁ እጅግ ትልቅ በሆነው ጸጋ ምክንያት
ስለሚያፈቅሩአችሁ ይጸልዩላችኋል ። 15በሰው
ቃል ሊነገር ስለማይቻለው ስጦታው ፤ እግዚአ
ብሔር የተመሰገነ ይሁን ።

## ምዕራፍ 10

### የጳውሎስ መከላከያ መልስ

1እኔ ጳውሎስ በእናንተ ፊት ሳለሁ ዐይነ
አፋር የተባልሁ ፥ ከእናንተ ስርቅ ግን በእናንተ
ላይ ደፋር የተባልሁ ፥ በክርስቶስ ገርነትና ደግ
ነት እለምናችኋለሁ ፤ 2የምለምናችሁም ወደ
እናንተ በምመጣበት ጊዜ በድፍረት እንድናገር
እንዳታደርጉኝ ነው ፤ በሥጋ አስተሳሰብ እንደ
ምንመላለስ አድርገው በሚገምቱን በአንዳንድ
ሰዎች ፊት ግን በድፍረት ለመናገር እችላለሁ ።
3ምንም እንኳ በዓለም ብንኖር ፥ የምንዋጋው
እንደ ዓለም ሰዎች አይደለም ። 4የጦር መሣሪያ
ዎቻችንም ምሽግ ለማፍረስ የሚያስችል መለኮ
ታዊ ኀይል ያላቸው ናቸው እንጂ እንደ ዓለም
የጦር መሣሪያዎች አይደሉም ። 5በእግዚአብ
ሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣውን ክርክ
ርና ከንቱ አሳብ እናፈርሳለን ፤ አእምሮን ሁሉ

[37] እግዚአብሔርም ሕዝቡን እንዲህ ሲል
ይጠይቃል ፣
‘የምትተማመኑባቸው እነዚያ
ብርቱዎች አማልክት የት አሉ?
[38] የመሥዋዕታችሁን ስብ መገባችኋቸው ፤
የሚጠጡትንም የወይን ጠጅ
አቀረባችሁላቸው ፤
እስቲ አሁን እነርሱ መጥተው
ይርዱአችሁ!
ተነሥተውም ይታደጉአችሁ!

[39] “‘አምላክ እኔ ብቻ ነኝ
ከእኔ በቀር ሌላ እውነተኛ አምላክ
የለም ፤
የምገድልም ሕይወትንም የምሰጥ እኔ
ነኝ ።
አቈስላለሁ ፤ እፈውሳለሁም ፤
እኔ የማደርገውንም መቋቋም
የሚችለው የለም ።
[40] እኔ በእርግጥ ሕያው አምላክ እንደመሆኔ
እጄን ወደ ላይ በማንሣት ፣
[41] የሚያብለጨልጭ ሰይፌን እንደምስልና
ትክክለኛ ፍትሕ መስጠቴን
እንደምመለከት እምላለሁ ፤
በጠላቶቼ ላይ የበቀል እርምጃ
እወስዳለሁ ፤
የሚጠሉኝንም እቀጣለሁ ።
[42] ፍላጻዎቼ በእነርሱ ደም ይጠመቃሉ ፤
ሰይፌም ተቃዋሚዎቼን ሁሉ
ይገድላል ፤
እኔን የሚቃወሙኝን ሁሉ አልምርም ፤
ቍስለኞችና ምርኮኞች የሆኑት እንኳ
ይሞታሉ ።’

[43] “አሕዛብ ሆይ! የእግዚአብሔርን ሕዝብ
ማመስገን ይገባችኋል ፤
እርሱ የእነርሱን ገዳዮች ሁሉ
ይቀጣል ፤
እርሱ በጠላቶቹ ላይ የበቀል እርምጃ
ይወስዳል ፤
የሕዝቡንም ኃጢአት ይቅር ይላል ።”

[44] ሙሴና የነዌ ልጅ ኢያሱም የእስራኤል
ሕዝብ እንዲሰሙት በማድረግ ይህን ቅኔ ተና
ገሩ ።

### ሙሴ የሰጠው የመጨረሻ ምክር

[45] ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ትእ
ዛዝ ለሕዝቡ አሰምቶ ከጨረሰ በኋላ እንዲህ
አለ ፣ [46] “ዛሬ የሰጠኋችሁን ትእዛዝ ሁሉ ለመ
ፈጸም ዝግጁዎች ሁኑ ፤ የእግዚአብሔርን ትእ
ዛዝ በታማኝነት መፈጸም ይችሉ ዘንድ ለልጆቻ
ችሁም አስተምሩአቸው ። [47] ይህ ትምህርት
የባዶ ቃላት ቅንብር አይደለም ፤ እርሱ የሕይወ
ታችሁ መሠረት ነው ፤ ስለዚህ ለዚህ ቃል ታዛ
ዦዎች ሁኑ ፤ ይህን ብታደርጉ ዮርዳኖስን ተሻ
ግራችሁ በምትወርሱአት ምድር ለረዥም ዘመን
ትኖራላችሁ ።”
[48] በዚያኑ ቀን እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ
አለው ፣ [49] “በሞአብ ምድር በኢያሪኮ ከተማ
ፊት ለፊት ወደሚገኙት የዐባሪም ተራራዎች
ሂድ ፤ ወደ ነቦ ተራራም ውጣ ፤ ከዚያም ለእስ
ራኤል ሕዝብ የማወርሳትን የከነዓን ምድር አሻ
ግረህ ተመልከት ፤ [50] ወንድምህ አሮን በሆር
ተራራ ላይ እንደሞተ አንተም በዚሁ በነቦ
ተራራ ላይ ትሞታለህ ፤ [51] ምክንያቱም እናንተ
ሁለታችሁም በእስራኤል ሕዝብ ፊት ለእኔ
ታማኞች ሆናችሁ አልተገኛችሁም ፤ በጺን
ምድረ በዳ በቃዴስ ከተማ አጠገብ በምትገኘው
በመሪባ ውሃ ምንጮች አጠገብ በነበራችሁበት
ጊዜ በእስራኤል ሕዝብ ፊት እንድከበር አላደረ
ጋችሁም ። [52] ከሩቅ ሆነህ ምድሪቱን ባሻገር
ታያለህ ፤ ነገር ግን እኔ ለእስራኤል ልጆች ወደ
ማወርሳት ወደዚያች ምድር አትገባም ።”

## ምዕራፍ 33

### ሙሴ የእስራኤልን ነገድ ሁሉ ባረከ

[1] የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ከመሞቱ በፊት
የእስራኤልን ሕዝብ የመረቀበት ቃለ በረከት
ይህ ነው ፦
[2] እግዚአብሔር ከሲና ተራራ መጣ ፤
በኤዶም ላይ እንደ ፀሐይ ወጣ ፤
ከፋራንም ተራራ ለሕዝቡ አበራ ፤
በሺ የሚቈጠሩ መላእክት ከእርሱ ጋር
አሉ ፤
በስተቀኙም የእሳት ነበልባል አለ ።
[3] እግዚአብሔር ሕዝቡን ይወዳል ፤
የእርሱ የሆኑትንም ወገኖች ሁሉ
ይጠብቃል ፤
ስለዚህ በእግሩ ሥር ተንበርክከን
እንሰግዳለን ፤
ትእዛዛቱንም እንጠብቃለን ፤
[4] ሙሴ የሰጠንንም ሕግ እንጠብቃለን ፤
ይህም ሕግ ለሕዝባችን እጅግ የከበረ
ውርስ ነው ።
[5] ነገዶቻቸውና መሪዎቻቸው በተሰበሰቡ
ጊዜ
እግዚአብሔር በሕዝቡ በእስራኤል ላይ
ነገሠ ።





[6] ሙሴ ስለ ሮቤል ነገድ እንዲህ አለ ፣
“ሮቤል የሕዝቡ ቍጥር አነስተኛ
ቢሆንም ፣
ሕዝቡ በሕይወት ይኑሩ እንጂ
አይሙቱ ።”

[7] ስለ ይሁዳም ነገድ እንዲህ አለ ፣
“እግዚአብሔር ሆይ!
የአንተን ዕርዳታ ለማግኘት
የሚያሰሙትን ጩኸት አድምጥ ፤
ከሌሎችም ነገዶች ጋር እንዲተባበሩ
አድርግ ፤
ራሳቸውን እንዲከላከሉ አድርግ ፤
ከጠላቶቻቸው ጋር በሚዋጉበትም ጊዜ
እርዳቸው ።”

[8] ስለ ሌዊም ነገድ እንዲህ አለ ፣
“እግዚአብሔር ሆይ!
ታማኞች የሆኑት ሌዋውያን
በሚያገለግሉባቸው ፣
በኡሪምና በቱሚም አማካይነት
ፈቃድህን ግለጥላቸው ፤
እነርሱን በማሳህ ፈትነሃል ፤
በመሪባም የውሃ ምንጮች አጠገብ
እውነተኛነታቸውን አረጋግጠሃል ።
[9] ከወላጆቻቸው ፣ ከወንድሞቻቸው ወይም
ከልጆቻቸው ይልቅ
ለአንተ ያላቸው ታማኝነት ይበልጣል ፤
ትእዛዛትህን ፈጽመዋል ፣
ለቃል ኪዳንህም ታማኞች ሆነዋል ።
[10] ለሕግህ ታዛዦዎች እንዲሆኑ ሕዝብህን
ያስተምራሉ ፤
በፊትህ ዕጣን ያጥናሉ ፤
በመሠዊያህ ላይ መሥዋዕትን
ያቀርባሉ ።
[11] እግዚአብሔር ሆይ! ኀይላቸው
እንዲበረታ ባርካቸው ፤
በሚሠሩትም ነገር ሁሉ ደስታህን
ግለጥላቸው ፤
ጠላቶቻቸውን ሁሉ ሰባብረህ ጣል ፤
ዳግመኛም እንዲነሡ አታድርግ ።”

[12] ስለ ብንያምም ነገድ እንዲህ አለ ፣
“እግዚአብሔር የሚወድደውና
የሚጠብቀው ነገድ ይህ ነው ፤
እግዚአብሔር እነርሱን ቀኑን ሙሉ
ይጠብቃቸዋል ፤
በመካከላቸውም ይኖራል ።”

[13] ስለ ዮሴፍም ነገድ እንዲህ አለ ፣
“እግዚአብሔር ዝናም በመስጠት ፣
ከምድርም ጥልቀት ውሃን በማፍለቅ ፣
ምድራቸውን ይባርክ ።
[14] ምድራቸው ፀሐይ በሚያበስለው ፍሬ
የተሞላ ይሁን ፤
በየወቅቱም በምርጥ ፍሬ የበለጸገ
ይሁን ።
[15] ከጥንት ጀምሮ የነበሩ ተራራዎቻቸውና
ኮረብታዎቻቸው
በምርጥ ፍሬ የተሸፈኑ ይሁኑ ፤
[16] ምድራቸው መልካም በሆነ ነገር ሁሉ
የተሞላ ይሁን ፤
በሚቃጠል ቍጥቋጦ ውስጥ ሆኖ
ከተናገረው
ከእግዚአብሔር በሚገኝ በረከት ሁሉ
የተሞላ ይሁን ፤
እነዚህ በረከቶች ሁሉ ለዮሴፍ ነገድ
ይድረሱት ፤
ምክንያቱም እርሱ በወንድሞቹ
መካከል መሪ ነው ።
[17] ዮሴፍ እንደ ኰርማ ብርቱ ነው ፤
እንደ ጐሽ ቀንድም ጠንካራ ነው ፤
ቀንዶቹም በሺ የሚቈጠሩት የምናሴ ፣
በዐሥር ሺ የሚቈጠሩትም የኤፍሬም
ዘሮች ናቸው ።
በእነርሱም አሕዛብን ይወጋል ፤
እስከ ምድር ዳርቻም ይገፋቸዋል ።”

[18] ስለ ዛብሎንና ስለ ይሳኮር ነገዶችም እን
ዲህ አለ ፣
“የዛብሎን ዘሮች በባሕር ላይ
በሚያካሂዱት ንግዳቸው ፣
የበለጸጉ ይሁኑ ።
የይሳኮርም ብልጽግና በሀገሩ ውስጥ
ይብዛ ።
[19] እነርሱ የውጭ አገር ሰዎችን
ወደ ተራራዎቻቸው ይጋብዛሉ ፤
ትክክለኛ የሆነውንም መሥዋዕት በዚያ
ያቀርባሉ ፤
ሀብታቸውንና ብልጽግናቸውንም
ከባሕርና በባሕር ጠረፍ ካለው አሸዋ
ያገኛሉ ።”

[20] ስለ ጋድ ነገድም እንዲህ አለ ፣
“ግዛታቸውን ያሰፋላቸውን
እግዚአብሔርን ያመስግኑ ፤
ጋድ የጠላትን ክንድ ወይም ግንባር
ለመስበር
እንደ አንበሳ ያደባል ።
[21] ምርጥ የሆነውን መሬት ለራሳቸው
ወሰዱ ፤
አመራር በመስጠት ድርሻ
ይኖራቸዋል ፤
የእስራኤል መሪዎች በአንድነት
በተሰበሰቡበት ጊዜ

ሸክም ሳልሆን ከመቅረቴ በቀር ፥ ከሌሎች አብ
ያተ ክርስቲያናት እናንተን ያሳነስሁአችሁ በም
ንድን ነው? ይህም ጥፋት ሆኖ ከተቈጠረ ይቅር
በሉኝ ።
14 ወደ እናንተ ለመምጣት ስዘጋጅ አሁን
ሦስተኛዬ ነው ፤ እኔ ሸክም ልሆንባችሁ አልፈ
ልግም ፤ ምክንያቱም እኔ የምፈልገው እናንተን
እንጂ ገንዘባችሁን አይደለም ። ለልጆቻቸው ገን
ዘብ ማከማቸት የሚገባቸው ወላጆች ናቸው
እንጂ ልጆች ለወላጆቻቸው ገንዘብ አያከማ
ቹም ። 15 ስለ እናንተ እንኳን ገንዘቤን ፥ ራሴ
ንም አሳልፌ ብሰጥ ደስ ይለኛል ፤ ታዲያ እኔ
ይህን ያህል ብዙ ስወዳችሁ ፥ እናንተ የምትወ
ዱዱኝ እንዲህ በጥቂቱ ነውን?
16 ያም ሆነ ይህ ሸክም አልሆንሁባችሁም ፤
እናንተ እንደምትሉትም በተንኰልና በማታለል
የያዝሁአችሁ ይመስላችኋል ። 17 ከላክሁአቸው
ሰዎች በአንዱ እንኳ አማካይነት በዘበዝሁአች
ሁን? 18 ቲቶ ወደ እናንተ እንዲመጣ ለመን
ሁት ፤ ያንን ወንድማችንንም ከእርሱ ጋር ላክ
ሁት ፤ ታዲያ ቲቶስ በዘበዛችሁን? እኛና እርሱ
ያገለገልናችሁ በአንድ መንፈስ አልነበረምን?
አካሄዳችንስ አንድ አልነበረምን?
19 እስከ አሁን የምታስቡት እኛ በእናንተ
ፊት ስለ ራሳችን እንደምንከላከል አድርጋችሁ
ነውን? እኛ በክርስቶስ ሆነን የምንናገረው በእ
ግዚአብሔር ፊት ነው ፤ ወዳጆቼ ሆይ! እኛ
ይህን ሁሉ የምንናገረው እናንተን ለማነጽ ብለን
ነው ። 20 እኔ ወደዚያ በምመጣበት ጊዜ ምናል
ባት ልትሆኑ እንደምፈልገው ሳትሆኑ ፥ እኔም
እናንተ እንደምትፈልጉት ሳልሆን እንገናኝ
ይሆናል ብዬ እፈራለሁ ፤ እንዲሁም በእናንተ
ዘንድ ጥል ፥ ቅንአት ፥ ቍጣ ፥ አድመኛነት ፥
የሰው ስም ማጥፋት ፥ ሐሜት ፥ ትዕቢት ፥
ሁከት ይኖሩ ይሆናል ብዬ እፈራለሁ ። 21 እንደ
ገና ወደ እናንተ ስመጣ አምላኬ ምናልባት በእ
ናንተ ፊት ያዋርደኛል ብዬ እፈራለሁ ፤ ከዚህ
ቀደም ኃጢአት ሠርተው ፥ በዚሁ በሠሩት ብል
ግናቸውና ዝሙታቸው ፥ በመዳራታቸውም
ንስሓ ስላልገቡት ሰዎች ሐዘን ላይ እወድቃለሁ
ብዬ እፈራለሁ ።

## ምዕራፍ 13

### የመጨረሻ ምክርና ሰላምታ

1 እንግዲህ ወደ እናንተ ስመጣ ይህ ሦስተ
ኛዬ ነው ፤ መቼም ሁሉ ነገር የሚረጋገጠው
በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ነው ። 2 በሁ
ለተኛው ጒብኝቴ ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ
በማስጠንቀቅ ተናግሬ ነበር ፤ አሁንም ደግሞ
በሩቅ ሆኜ ከዚህ ቀደም ኃጢአት ለሠሩትና
ለሌሎችም በማስጠንቀቅ እናገራለሁ ፤ አሁን
ወደ እናንተ ተመልሼ በምመጣበት ጊዜ ለማ
ንም አልራራም ፤ 3 በዚህ ዐይነት በእኔ አማካይ
ነት የሚናገረው ክርስቶስ መሆኑን ትረዳላችሁ ፤
በእናንተ ዘንድ የሚታየው የእርሱ ኀይል ነው
እንጂ ድካሙ አይደለም ። 4 እርሱ በመስቀል
ላይ ተሰቅሎ የሞተው በደካማነት ቢሆንም ፥
አሁን በእግዚአብሔር ኀይል በሕይወት ይኖ
ራል ፤ እኛም ከእርሱ ጋር ደካሞች ሆነናል ፤
ከእናንተ ጋር ባለን ግንኙነት ግን ከእርሱ ጋር
በእግዚአብሔር ኀይል እንኖራለን ።
5 በእምነት መሆናችሁን ለማረጋገጥ ራሳች
ሁን መርምሩ ፤ ራሳችሁን ፈትኑ ፤ ኢየሱስ ክር
ስቶስ በውስጣችሁ መሆኑን አልተገነዘባችሁ
ምን? አለበለዚያማ በፈተና ወድቃችኋል ማለት
ነው! 6 እኛ በፈተና አለመውደቃችንን እንደም
ትገነዘቡ ተስፋ እናደርጋለን ። 7 ከቶ ምንም
ክፉ ነገር እንዳታደርጉ ወደ እግዚአብሔር እን
ጸልያለን ፤ የምንጸልየውም ምንም እንኳ እኛ
ብቁዎች ሆነን ሳንታይ ብንቀርም ፥ እናንተ ዘወ
ትር መልካም የሆነውን ነገር እንድታደርጉ
ነው እንጂ የእኛን ብቃት ለማሳየት አይደለም ።
8 ምክንያቱም እኛ ስለ እውነት እንሠራለን
እንጂ የእውነት ተቃራኒ የሆነ ምንም ነገር አን
ሠራም ። 9 እኛ ደካሞች ስንሆን እናንተ ግን
ብርቱዎች ስትሆኑ ፥ ደስ ይለናል ፤ የእኛ
ጸሎት እናንተ ፍጹሞች እንድትሆኑ ነው ።
10 ይህን መልእክት ከእናንተ ርቄ ሳለሁ የጻፍሁ
ላችሁ በዚሁ ምክንያት ነው ፤ በዚህ ዐይነት
ወደ እናንተ በምመጣበት ጊዜ ጌታ በሰጠኝ
ሥልጣን አላስጨንቃችሁም ፤ ምክንያቱም ጌታ
ሥልጣን የሰጠኝ እናንተን ለማነጽ እንጂ እናን
ተን ለማፍረስ አይደለም ።
11 በተረፈውስ ወንድሞቼ ሆይ! ደህና ሁኑ ፤
ፍጹሞች ለመሆን ተጣጣሩ ፤ ምክሬን ስሙ ፤
እርስ በእርሳችሁ ተስማሙ ፤ በሰላምም ኑሩ ፤
የፍቅርና የሰላም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆ
ናል ።
12 በወንድማማችነት ስሜት እየተሳሳማችሁ
ሰላምታ ተሰጣጡ ፤
13 ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል ።
14 የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ፥ የእግዚእ
ብሔር ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ኅብረት ከሁላ
ችሁ ጋር ይሁን ።

13፥1 ፦ ዘዳ. 17፥6 ፤ 19፥15 ።

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት
# ወደ ገላትያ ሰዎች

### መግቢያ

ስለ ኢየሱስ አዳኝነት የሚናገረው የምሥራች ቃል በየቦታው እየተበሠረና አይሁዳውያን ያል ሆኑ ሰዎች እየተቀበሉት በሄዱ መጠን "ክርስቲያን ለመሆን የሙሴን ሕግ መፈጸም ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም?" የሚለውም ጥያቄ አብሮ ተነሣ ፤ በዚህ ጊዜ ጳውሎስ "ክርስቲያን ለመ ሆን የሙሴን ሕግ መፈጸም አያስፈልግም ! እንዲያውም በክርስቶስ አዲስ ሕይወት ለማግኘት መሠረቱ እምነት ነው ፤ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ሊጸድቁ የሚችሉት በእምነት ብቻ ነው" በማለት ያስረዳ ጀመር ፤ ነገር ግን በታናሽቱ እስያ የሮም ግዛት በሆነችው በገላትያ ባሉ አብ ያተ ክርስቲያናት መካከል "ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዲጸድቅ በኢየሱስ ማመን ብቻ ሳይ ሆን የሙሴንም ሕግ መፈጸም አለበት" በማለት ጳውሎስን የሚቃወሙ ሰዎች ነበሩ ።

ጳውሎስ ይህን የገላትያን መልእክት የጻፈው በዚህ በስሕተት ትምህርት የተወናበዱትን ሰዎች ወደ ትክክለኛው እምነትና የክርስትና ሕይወት ለመምራት ነው ፤ ጳውሎስ የኢየሱስ ክር ስቶስ ሐዋርያ መሆኑን በማረጋገጥ ይጀምራል ፤ ለሐዋርያነት የጠራው እግዚአብሔር እንጂ ሰው እንዳልሆነና የእርሱም ተልእኮ አይሁዳውያን ወዳልሆኑ ሰዎች እንደሆነ በመዘርዘር ያስረዳል ፤ ከዚህም በማያያዝ ፥ ሰዎች ሊጸድቁ የሚችሉት በእምነት ብቻ መሆኑን ይገልጣል ፤ በመጨረሻ ዎቹ ምዕራፎች ውስጥ ክርስቲያናዊ ጠባይ በኢየሱስ ላይ ከሚደረገው እምነት ከሚወጣ ፍቅር የሚመነጭ መሆኑን ያስረዳል ።

## ምዕራፍ 1

1 በሰዎች ወይም በሰው አማካይነት ሳይሆን
በኢየሱስ ክርስቶስና እርሱንም ከሞት ባስነሣው
በእግዚአብሔር አብ ሐዋርያ ለመሆን ከተመ
ረጠ ከጳውሎስ ፥ 2 ከእርሱም ጋር ካሉት ወንድ
ሞች ሁሉ ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት የተ
ላከ ።
3 ከአባታችን ከእግዚአብሔር ፥ ከጌታችንም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ
ይሁን ።
4 ከዚህ ከክፉ ዓለም ያድነን ዘንድ አባታችን
በሆነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ፥ ክርስቶስ ስለ
ኃጢአታችን ራሱን አሳልፎ ሰጠ ። 5 ከዘላለም
እስከ ዘላለም ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን ፤
አሜን ።

### የወንጌል እውነት
### አንድ ብቻ ነው

6 በክርስቶስ ጸጋ ከጠራችሁ አምላክ እንዲህ
ፈጥናችሁ መለየታችሁና ወደ ሌላ ወንጌል
መሄዳችሁ ያስደንቀኛል ። 7 ይህንንም ያልሁት
ግራ የሚያጋቡአችሁና የክርስቶስንም ወንጌል
ለመለወጥ የሚፈልጉ አንዳንድ ሰዎች ስላሉ
ነው እንጂ ወንጌልማ በመሠረቱ አንድ ብቻ
ነው ። 8 ይሁን እንጂ እኛም ብንሆን ወይም የሰ
ማይ መልአክም እንኳ ቢሆን እኛ ከሰበክንላ
ችሁ የተለየ ሌላ ወንጌል ቢሰብክላችሁ የተረ
ገመ ይሁን ። 9 ከዚህ በፊት እንዳልሁት አሁ
ንም ደግሜ እላለሁ ፤ እናንተ ከተቀበላችሁት
የተለየ ሌላ ወንጌል ማንም ቢሰብክላችሁ የተረ
ገመ ይሁን ።
10 ታዲያ እኔ የምፈልገው ሰው እንዲያመሰግ
ነኝ ነውን? ወይስ እግዚአብሔር እንዲያመሰግ
ነኝ? ወይስ ሰውን ደስ ለማሰኘት የምፈልግ
መስሎአችሁ ይሆን? ሰውን ለማስደሰት የምፈ
ልግ ከሆንሁማ የክርስቶስ አገልጋይ ባልሆንሁም
ነበር ።

### የጳውሎስ ሐዋርያነት

11 ወንድሞቼ ሆይ! እኔ የሰበክሁላችሁ ወን
ጌል ሰው ሠራሽ አለመሆኑን አስታውቃችኋ
ለሁ ። 12 ምክንያቱም ለእኔ የገለጠልኝ ኢየሱስ
ክርስቶስ ነው እንጂ ከማንም ሰው አልተቀበል
ሁትም ፤ ወይም ማንም ሰው አላስተማረኝም ።
13 ቀድሞ የአይሁድ እምነት ተከታይ በነበር
ሁበት ጊዜ እንዴት እንደኖርሁ ሰምታችኋል ፤
የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ያለ ርኅራኄ

1፥13 ፦ ሐ.ሥ. 8፥3 ፤ 22፥4-5 ፤ 26፥9-11 ።